የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝም  የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ  ቋንቋ ስነጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# በደብብህክመ ት/ቢሮ በተዘጋጀው የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የአፍልቆት ክሂሎችን ለማዳበር የቀረቡ መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት ትንተና

በ

ተሰማ ተስፋዬ

መስከረም /2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝም  የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ  ቋንቋ ስነጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# በደብብህክመ ት/ቢሮ በተዘጋጀው የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የአፍልቆት ክሂሎችን ለማዳበር የቀረቡ መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት ትንተና

አማርኛን በማስተማር ለኤምኤ ዲግሪ የቀረበ ጥናት

በ

ተሰማ ተስፋዬ

አማካሪ

ግርማ ገብሬ (ዶር)

መስከረም /2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

## የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝም የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ ስነጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

## የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# በደብብህክመ ት/ቢሮ በተዘጋጀው የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የአፍልቆት ክሂሎችን ለማዳበር የቀረቡ መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት ትንተና

### የፈተና ቦርድ

ስም ፊርማ

አማካሪ

---

ፈታኝ

---

ፈታኝ

---

2016 ዓ.ም

# ምስጋና

ከሁሉ በማስቀደም በብዙ ፈተናዎች መካከል በማለፍ ዛሬን እንዳይ ከጎኔ ቆሞ ብርታት ለሆነኝ ልዑል እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይሁን፡፡ በመቀጠልም ይህ ጥናት በዚህ ቅርጽ ይታይ ዘንድ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ያቀረብኩት ግርድፍ ስራ ተጣርቶ የጥናታዊ ጽሁፍ ቅርጽ እንዲይዝ መወገድና መጨመር ያለበትን በማሳየትና በመከታተል ለደገፉኝ አማካሪዬ ዶክተር ግርማ ገብሬ ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡

ውድ ባለቤቴ ወ/ሮ በቀለች ሔሴቦ እግዚአብሄር በሰጣት ልዩ ትዕግስት የጤና ዕክል ክፍተቴን በሙሉ መሰጠት በመሙላት፣ እያንዳንዱ የትምህርት ጉዞዬ የቀና እንዲሆን የትምህርትና የጥናት ጽሁፎችን በጥንቃቂ በማንበብ፣ ይህን ሁሉ ርቀት አብራኝ በመጓዝ ለዚህ ስኬት እንድበቃ ምክንያት ሆነኛለችና እግዝአብሄር ዕድሜ ከጤና ጋር ያጥግብሽ ከማለት ሌላ የለኝም፡፡

የእኔ የእይታ ችግር በቅርቡ ስራ ከጀመርኩ በኋላ የተከሰተ በመሆኑ እንደ ሌሎች አይነስውራን ብቻዬን መንቀሳቀስ እፈራለሁ፡፡ ከባለቤቴ በተጨማሪ ልዩ ድጋፍ በመሆን ችግርን በልበ ሙሉነት እንድጋፈጥ በመሪነትና እኔና ባለቤቴ በትምህርቴ ምክንያት ለረጅም ጊዜ ከቤቴ ውጪ ስንሆን የቤታችንን ጣጣ ብቻዋን በመሸፈን ከፍተኛ ዋጋ ለከፈለችው ውዷ ልጄ እልልታ ተሰማ እግዚአብሄር ውለታሽን በእጥፍ ይክፈልሽ እላለሁ፡፡

በመጨረሻም ትምህርት ነክ በሆኑ ጉዳዮች ዙሪያ ድጋፍ ባስፈለገኝ ጊዜ ሁሉ ከጎኔ ላልተለዩኝ መምህራን ባጠቃላይ ለመምህር ተረፈ ኤርሰዶና ለመምህርት ጽጌ ግርማ በተለይ ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡

# ማረጋገጫ

በአዲሱ የስምንተኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የአፍልቆት ክህሎችን ለማዳበር የቀረቡ መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት ትንተና በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የስነሰብ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር፣ የሁለተኛ ድግሪ ማሟያ ይሆን ዘንድ ያቀረብኩት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በሌላ በማንኛውም አካል ያልተሰራ የራሴ ወጥ ስራ መሆኑንና የተጠቀምኳቸው ድርሳናትም በትክክል ዋቤዎች የተደረጉ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲም የጥናቱ ህጋዊ የባለቤትነት መብት ያለው መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም________________________________

ፊርማ______________________________

ቀን_________________________________

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዓላማ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ትምህርት ቢሮ አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ በሚል ርዕስ ለስምንተኛ ክፍል አዲስ በተዘጋጀው የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡትን የአፍልቆት ክህሎችን ለማዳበር የቀረቡ መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት በመፈተሽ፣ የታዩ ጠንካራ ጎኖች ይበልጥ ተጠናክረው እንዲቀጥሉ፣ ድክመቶችም መጽሀፉ ሲሻሻል ትኩረት አግኝተው የሚሻሻሉበትን ሀሳብ ለመስጠትና አሁን በማስተማር ላይ ሆነው ይህን ጥናት ሊያገኙ የሚችሉ የክፍሉ መምህራን ሲያስተምሩ የታዩ ክፍተቶችን በራሳቸው ሊሞሉ የሚያስችላቸውን የማሻሻያ ሀሳብ ለመስጠት ነው፡፡ የጥናቱ ዓላማ ከግብ ይደርስ ዘንድ የመረጃ ምንጮቹን የሰነድ ፍተሻና ለክፍሉ መምህራን የሚቀርብ የጽሁፍ መጠይቅ አድርጓል፡፡ በሰነድነት የሚፈተሸውም የስምንተኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ነው፡፡ ለጽሁፍ መጠይቅ የመረጃ ምንጭ የሆኑ መምህራን በከምባታ ጠምባሮ ዞን፣በዱራሜ ከተማ አስተዳደር ስር ባሉት አራት የመጀመሪያ ደረጃ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ አማርኛ ቋንቋ ከሚያስተምሩት መምህራን መካከል ተመርጠው የቀረቡ ናቸው፡፡ ከሁለቱም የመረጃ ምንጮች የተሰበሰቡ መረጃዎች በአይነታዊና በመጠናዊ ዘዴዎች በመተንተን በማብራሪያዎች ተደግፈው ቀርበዋል፡፡ ትንታኔው የሚያሳየው ለአፍልቆት ክሂሎች ማዳበሪያነት የቀረቡት መልመጃዎች ከይዘት ምርጫ አንጻር ወቅታዊነት፣ ተገቢነትና ተተግባሪነት ያላቸው ይዘቶች እንደሆኑ ጥናቱ አረጋግጧል፡፡ ጥናቱ ከአደረጃጀትም አንጻር ተከታታይነቱ በጥንካሬ የተገመገመ ነው፡፡ የመናገር ክሂል በይዘት የታጨቀ ነው፡፡ ከክፍል ትምህርቱ ይዘት 33.3% የሚሆነውን የተሸፈነው በንግግር ነው፡፡ ስለዚህ ዝግጅቱ የአደረጃጀት ችግር እንዳለበት ለንግግር ክሂል የተሰጠው ሰፊ ሽፋን ማሳያ ነው፡፡ በተቻለ ፍጥነት መሻሻል ካለባቸው ችግሮች ዋነኛው የንግግርን ሽፋን ማስተካከል ነው፡፡ በተጨማሪም ጥናቱ የመጽሀፉ ዝግጅት የተለጣጣቂነት ችግር እንዳለበት ያሳያል፡፡ ይዘቱ ከቀላል ወደ ውስብስብና ከባድ ስፋትና ጥልቀት እየጨመረ መሄድ ሲገባው ከአደረጃጀትም ሆነ ከአቀራረብ አንጻር ወጥነት የጎደለው አካሄድ ተከትሏል፡፡ ይህም ክፍተት በሚመለከተው አካል ሊስተካከል ይገባል የሚል አመለካከት ያላቸው የመፍትሄ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡

## የየይዘት ማውጫ


| ርእስ | ገጽ |
|---|---|
| ምስጋና | I |
| ማረጋገጫ | II |
| አጠቃሎ | III |
| ማውጫ | IV |
| የሠንጠረዥ ማውጫ | VIII |
| **ምዕራፍ አንድ** | |
| መግቢያ | 1 |
| 1.1 የጥናቱ ዳራ | 1 |
| 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት | 3 |
| 1.3 የጥናቱ አላማ | 4 |
| 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ | 4 |
| 1.5 የጥናቱ ወሰን | 5 |
| **ምዕራፍ ሁለት** | |
| ክለሳ ድርሳናት | 6 |
| 2.1 የመናገር ክሂል ምንነት | 6 |
| 2.1.1 የመናገር ክሂልን የማስተማር አላማ | 7 |
| 2.1.2 የንግግር ክሂል የመማር አስፈላጊነት | 8 |
| 2.1.3 የመናገር ክሂል ደረጃዎች | 9 |
| 2.1.4 የመናገር መልመጃ አዘገጃጀት | 9 |
| 2.1.5 የመናገር ክሂል አቀራረብ መልኮች | 13 |
| 2.2 የመጻፍ ክሂል ምንነት | 16 |
| 2.2.1 የመጻፍ ክሂል ትምህርት ዓላማ | 19 |
| 2.2.2 የመጻፍ ትምህርት አስፈላጊነት | 20 |
| 2.2.3 የመጻፍ ትምህርት ባህርይ | 22 |

2.2.3.1 ሥነ ልቡናዊ ባህርይ ........ 22
2.2.3.2 ስነልሳናዊ ባህርይ ........ 22
2.2.3.3 አእምሮታዊ ባህርይ ........ 23
2.2.4 የመጻፍ ክሂል ይዘቶች ........ 23
2.2.4.1 የመጻፍ ክሂል ይዘት ከአላማ ጋር ያለው ቁርኝት ........ 23
2.2.4.2 የመጻፍ ክሂል ይዘት ከዘዴ ጋር ያለው ትስስር ........ 24
2.2.4.3 የመጻፍ ክሂል ይዘት ተነሳሽነት (Motivation) ጋር ያላቸው ተዛምዶ ........ 25
2.2.5 የመጻፍ ክሂል ይዘቶች አደረጃጀት ........ 25
2.2.5.1 ተዋረዳዊ አደረጃጀት (Vertical Organization) ........ 26
2.2.5.2 ጎናዊ አደረጃጀት (Horizontal Organization) ........ 28
2.3 የመልመጃ ምንነት ........ 28
2.3.1 የመጻፍ ክሂል መልመጃ አይነቶችና አቀራረቦች ........ 29
2.3.1.1 ውስን የጽህፈት ክሂል መልመጃ ........ 30
2.3.1.2 ጠቋሚ የጽህፈት ክሂል መልመጃ ........ 30
2.3.1.3 ልቅ የጽህፈት ክሂል መልመጃ ........ 31
2.3.2 ለመፃፍ የሚያነሳሱ መልመጃዎች (ተግባራት) ........ 31
2.3.2.1 ተግባራዊ የጽህፈት መልመጃዎች ........ 31
2.3.2.2 የስሜት መግለጫ መልመጃዎች ........ 32
2.3.2.3 ትምህርት ቤት ተኮር የጽህፈት ክሂል መልመጃዎች ........ 32
2.3.3 የመናገር ክሂል መልመጃዎች አቀራረብ ........ 33
2.3.3.1 ጨዋታዎች ........ 35
2.3.3.2 ችግሮችን አፍለቆ መፍትሄ መሻት ........ 35
2.3.3.3 ታሪክ መናገር ........ 36
2.3.3.4 ሚና ጨዋታ ........ 36
2.3.3.5 ጭውውት ........ 37

2.3.3.6 ቃላዊ ርፖርት ....................................................................................37

2.3.3.7 ውይይት ....................................................................................37

2.4 ቀደምት ጥናቶች ቅኝት ....................................................................................38

*ምዕራፍ ሦስት*

የአጠናን ዘዴ ....................................................................................41

3.1 የጥናቱ ንድፍ ....................................................................................41

3.2 የክፍል ናሙና አመራረጥ ....................................................................................41

3.3 የት/ቤቶች ናሙና አመራረጥ....................................................................................42

3.4 የመምህራን ናሙና አመራረጥ....................................................................................42

3.5 መረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች....................................................................................42

3.5.1.የሰነድ ፍተሸው የትኩረት ነጥቦች (ቼክ ሊስት)....................................................................................43

3.5.2.የጽሁፍ መጠይቅ አዘገጃጀት....................................................................................43

3.6 መረጃ አተናተን ዘዴ....................................................................................43

*ምዕራፍ አራት*

የመረጃ ትንተናና ማብራሪያ ....................................................................................45

4.1 የመረጃ ትንተና....................................................................................45

4.1.1 የ8ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ አጠቃላይ ይዘቶች ዳሰሳ ..............45

4.1.2 በ8ኛ ክፍል አዲሱ የ8ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ

ለአፍልቆት ክሂሎች የሰጠው ትኩረት ....................................................................................49

4.1.2.1 የመናገር ክሂል መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት ......................49

4.1.2.2. አዲሱ 8ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ለጽህፈት

ክሂል የሰጠው ትኩረት ....................................................................................51

4.1.3 ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና ..............................53

4.2 የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ ....................................................................................58

*ምዕራፍ አምስት*


ማጠቃለያና አስተያየት ....................................................................................................61

5.1 ማጠቃለያ ....................................................................................................61

5.2. አስተያየት ....................................................................................................63

ዋቤ መፃህፍት ....................................................................................................65

አባሪ 1 ....................................................................................................68

አባሪ 2 ሠንጠረዥ 4፡- የንግግር ትምህርት መልመጃዎች አደረጃጀትና አቀራረብ ..........74

አባሪ 3 ሠንጠረዥ 6፡- የጽህፈት መልመጃዎች ሥርጭት ....................................................77

አባሪ 4 ሠንጠረዥ 8፡- የክፍል ሁለት ጥያቄ መልሶች ትንተና ..........................................79

## <u>የሠንጠረዥ ማውጫ</u> <u>ገጽ</u>


ሠንጠረዥ 1፡- *አጠቃላይ የአዲሱ 8ኛ ክፍል ይዘቶች ዝርዝር* ..........46

ሠንጠረዥ 2:- በ8ኛ ክፍል *መማሪያ መጽሀፍ* ያሉ ይዘቶች የስርጭት ሽፋን ..........49

ሠንጠረዥ 3:- የ*መናገር* ክሂል *መልመጃዎች* የስርጭት ሽፋን ..........50

ሠንጠረዥ 5፡- *በአዲሱ የ8ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ*
*ያለው የጽህፈት መልመጃ የሥርጭት ሽፋን* ..........52

ሠንጠረዥ 7፡- *የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን አጠቃላይ መረጃ* ..........54

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ትምህርት በተለይም የቋንቋ ትምህርት ሲታሰብ የክሂል ዘርፎችን በተገቢው መንገድ አደራጅቶና አቅዶ መጠቀም አጠቃላይ ትምህርቱ የታለመለትን ግብ እንዲመታ የማድረግ ዕድሉ ከፍተኛ መሆኑ የታወቀ ነው፡፡ የቋንቋ ክሂሎች የሚባሉት የመረጃ መቀበያ (ማንበብና ማዳመጥ) ና የማስተላለፊያ (መፃፍና መናገር) ናቸው፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረት በአፍልቆት ክሂሎች ማለትም የመፃፍና የመናገር ክሂሎች በአዲሱ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ እንዲዳብሩ ለማድረግ የቀረቡት መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀትን መተንተን ነው፡፡

Bygate (1987) እንደሚገልጹት አንድ ሰው መናገር ይችላል የሚባለው ከአንደበቱ ቅላፄና ምት ያላቸውን ቃላትና ሀረጎች ማውጣት በመቻሉ ብቻ ሳይሆን ተናጋሪው ለፈለገው ጉዳይ ተገቢ የሆኑና ሀሳቡን በትክክል ሊያስተላልፉለት የሚችሉ ቃላት መምረጥ ሲችል ነው፡፡ ቃላትን ሲመርጥ ይህን ቃል ከጊዜ፣ ከቦታና ከሁኔታ አንፃር ብናገር የአድማጭን ስሜት ሊይዝልኝ ይችላል ወይ? የተነሳሁበትን ዓላማ ሳያፈርስ አጥርቶ ሊያስተላልፍልኝ የሚችል ቃል ነው ወይ? የሚሉትን ማሰብ ይኖርበታል፡፡ Harmar (2007:123)፣ የመናገር ክሂል ትምህርት ሲተገበር ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እንዲናገሩ የምንፈልግባቸው ሦስት ምክንያቶች በሚል እንደሚከተለው ጠቅሰዋል፡፡

- ❖ የመናገር ክሂል ተግባራት የልምምድ ዕድሎችን ማለትም በዕውኑ አለም ንግግር የሚያገለግል የልምምድ ዕድል በክፍል ውስጥ ስለሚሰጡ፣
- ❖ ተማሪዎች የሚገለገሉባቸው የንግግር ክሂል ተግባራት ለመምህራንም ሆነ ለተማሪዎች ምጋቤ ምላሽ ያህል ስኬታማ እንደሆኑና ምን አይነት የቋንቋ ችግር እንዳጋጠማቸው ስለሚለዩበት፣
- ❖ ተማሪዎች በአዕምሮኣቸው ያከማቿቸውን የቋንቋ ቅርጾች የመጠቀም ችሎታቸው ስለሚጨምር ይህም ቃላትና ሀረጋትን ያለ ምንም ጭንቀት በጥሩ ሁኔታ መገልገል ስለሚያስችላቸው ነው፡፡

በድሉ (2007፡67) የተማሪዎችን የመናገር ችሎታ በተመለከተ እንደገለጹት፣ በሀገራችን አብዛኞቹ ተማሪዎች የከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርታቸውን የሚጨርሱት ጥሩ የንግግር ችሎታ ሳያዳብሩ እንደሆነ ነው፡፡ ከላይ በተማሪዎቹ የታየው ጉዳይ የሚያመለክተው በትምህርት ቤት ደረጃ በመናገር ስሜታቸውን መግለፅ ሳይችሉ ያለፉ ተማሪዎች በቀሪው የህይወት ጉዞኣቸው ያለ ምንም ችግር ሀሳባቸውን በንግግር ለመግለፅ ይቸገራሉ፡፡ የመበለጥና የተሸናፊነት ስሜት ይሰማቸዋል፡፡ በራሳቸው ንግግር ይሸማቀቃሉ፡፡ አይናፋርነት ያጠቃቸዋል፡፡ ሀሳብን በምክንያትና ውጤት አቀናጅተው የማቅረብ፣ ሰዋስዋዊ ሥርዓት የመጠበቅ ችግር ይገጥማቸዋል፡፡

ሌላው በዚህ ጥናት የሚታየው የአፍልቆት ክሂል ጽህፈት ነው፡፡ ጽህፈት ሀሳብ ከመግለጫ ክሂሎች ልዩ ጥንቃቄና ሥልጠና የሚፈልግ ክሂል ነው፡፡ ጽህፈት የተማሪዎችን የአፍልቆት አቅም ከማደበር አንፃር ከፍተኛ ሚና አለው፡፡

እንደ Widdowson (1983:35) አገላለጽ መፃፍ ተግባቦታዊ ተግባር ስለሆነ የተግባቦትን አጠቃላይ ይከተላል፡፡ የፀሐፊንና የአንባቢን ግንኙነት ይፈልጋል፤ በሀሳብ ማስተላለፊያነቱ የሦስት መረጣ፣ የአረፍተ ነገር አወቃቀር፣ የመልዕክት ግልፅነት፣ የመሳሳሉት በዚህ መርህ ይከታተሉ በማለት ያስረዳሉ፡፡ White እና Amdt (1991:3) እንደሚሉት መፃፍ ንግግርን በምልክት ከመመዝገብ በላይ የሚሄድ፣ ሁሉን የቻለ የማሰብ ሂደት ነው በማለት ይገልፃሉ፡፡

ማረው (1987፡164) እንደሚሉት ደግሞ የመፃፍ ክሂል በባህርዩ ክሂል ብዙ ነው፡፡ የሀሳብ አደረጃጀት፣ የአረፍተ ነገር አወቃቀር፣ የአንቀጽ አመሠራረት፣ የቃላት አመራረጥና አጠቃቀም፣ የሥርኣተ ነጥብ አጠቃቀም ወዘተ… የመፃፍ ክሂል ትምህርት ከሚፈለጉ መሠረታዊ ነገሮች መካከል ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ የመፃፍ ክሂል መማርንም ያጠቃልላል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በቀጥታ ወደ መፃፍ ከመግባታቸው በፊት በሂደቱ ላይ ብዙ መስራት ይጠበቅባቸዋል በማለት ይገልፃሉ፡፡

የምሁራኑ ሀሳብ የሚያስረዳው ተማሪዎች ቋንቋ ሲማሩ አራቱንም የቋንቋ ክሂሎች አጣምረው ቢማሩ ውጤታማ እንደሚሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት ሂደት ተግባቦታዊ ብቃታቸውን እንዲያዳብሩ ጽህፈትና ንግግር አሁን በተዘጋጀው በአዲሱ መማሪያ መጽሐፍ ያሉበት ደረጃ በንጽጽር ይፈተሻል፡፡

የቋንቋ ትምህርት ይዘት የክሂልንና የዕውቀት ዘርፎችን እንደየክፍሉ ደረጃ የሚያካትት ሲሆን የዚህ ጥናት አጥኚ ትኩረት ደግሞ ከክሂል ዘርፎች መካከል ሁለቱን ማለትም ጽህፈትና

ንግግርን (የአፍልቆት ክሂሎችን) በተመለከተ በ2014 ዓ.ም በሙከራ ዳብሮ በ2015 ዓ.ም ስራ በጀመረው መጽሀፍ ውስጥ የመናገርና መፃፍ ክሂሎችን ለማዳበር የቀረቡት መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት ምን ያህል የአማርኛ ቋንቋ ይዘቶች አደረጃጀት መርህ መከተል አላመከተሉንና ባህርያቱን መያዝ አለመያዙን ለመፈተሽ አቅዶ ተነስቷል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

በአሁኑ ወቅት የተማሪዎች የትምህርት ፍላጎት ባጠቃላይ የቋንቋ ትምህርት ፍላጎት ደግሞ በተለይ በተለያዩ በሚታወቁና በማይታወቁ ምክንያቶች ዝቅተኛ ደረጃ ደርሶ ይገኛል፡፡ በማስተማር ስራ ላይ ሆነን እያየን ያለነው ተማሪዎች በስምንተኛ ክፍል ደረጃ ሆነው አብዛኞቹ በአማርኛ ቋንቋ የመናገር፣ የማንበብ፣ የማዳመጥና የመጻፍ አቅማቸው በጣም ዝቅተኛ እየሆነ መሆኑን የሚያስመዘግቡት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክልላዊ ፈተና ውጤትና የክፍል ውስጥ ተሳትፎ እያሳየ ነው፡፡ ጽህፈትን በተላይ በሚመለከት ከ8ኛ ክፍል በላይ ያሉት ሳይቀሩ አጠገባቸው ካለ ተማሪ ደብተር ላይ ስህተትን ስህተት ይሁን ትክክል ሳያረጋግጡ ስህተቱን እንዳለ ሲያባዙ (ሲያራቡ) ይውላሉ፡፡

ይህን አጥኚ ይህን ጥናት ለማድረግ ያነሳሰው መሠረታዊ ጉዳይ ከላይ ያየነው አሳዛኝ እውነት ነው፡፡ ህኛው ዝግጅት በመፃህፍት ዝግጅት ወቅት በመፈጠር ለክሂሎች መውደቅ ምክንያት የሆኑ የመልመጃዎች አደረጃጀት በምን ደረጃ ላይ እንዳሉ ማየት አጥኚውን የቀሰቀሰ ምክንያት ነው፡፡ በተለይ መጽሐፉ ለአፍልቆት ክሂሎች ምን ያህል ሽፋን እንደሰጣቸው ለመፈተሽ ይዘቱ፣ የመልመጃዎቹ አቀራረብና አደረጃጀት የተማሪዎችን የትምህርት ዳራ፣ ዕድሜ፣ ፍላጎትና ችሎታ … ያገናዘበ መሆን አለመሆኑን መፈተሽና መገምገም መሠረታዊ ምክንያት ነው፡፡ በመሆኑም አዲስ የተዘጋጀው መጽሐፍ ከላይ የቀረቡትን የተማሪን ሁኔታ የሚገልጹ ነገሮችን ከግምት ውስጥ ያስገባ ዝግጅት ከሆነ ጥንካሬውን ለማሳየት፣ ካልሆነ ወይም ዝግጅቱ ከተማሪዎች ፍላጎትና የቋንቋ ችሎታ ጋር የማይጣጣም ከሆነ፣ አደረጃጀቱና አቀራረቡም የተዛባ ከሆነ ደካማ ጎኑን በመጠቆም ክፍተቱን ለመሙላት ከሚያስችል የመፍትሄ ሀሳብ ጋር ለሚመለከታቸው አካላት ለማቅረብና ችግሩን ለማስወገድ ነው፡፡

በተጨማሪም 7ኛ ክፍልን አጠናቀው ወደ 8ኛ ክፍል የተዛወሩ ተማሪዎች በመናገር ራሳቸውን ለመግለፅ ያለመቻልና የቤት ሥራ ወቀረታቸውን በተማሪ ፊት ለማቅረብ ሲቸገሩ፣ ከጀመሩም በላብ ሲጠመቁ ይስተዋላል፡፡ ስለዚህ የዚህ ጥናት አጥኚ መምህር እንደመሆኑ መጠን በአዲሱ

የስምንተኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሃፍ ለአፍልቆት ክሂሎችና ክሂሎቹን ለማጠናከር ለቀረቡት የተለያዩ መልመጃዎች የተሰጠውን ትኩረት ከሌሎቹ ክሂሎች አንጻር አይቶ በመተንተን ክፍተት ካለ ለማሳየትና የማስተካከያ አስተያየት ለማቅረብ ጥናቱን ጀምሯል፡፡

## 1.3 የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በ2015 ዓ.ም አዲስ ወደ ትግበራ በገባው የ8ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የአፍልቆት ክሂሎችን (መፃፍና መናገር) ለማዳበር የቀረቡ መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት መተንተን ወይም መፈተሽ ነው፡፡ ይህን አላማ ከግብ ለማድረስ ሲባል የሚተኮርባቸው ዝርዝር አላማዎች፡-

- በመጽሐፉ ውስጥ ለአፍልቆት ክሂሎች የተሰጠው ሽፋን መፈተሽ፣
- የየምዕራፉ የንግግርና የጽህፈት መልመጃዎች አቀራረብ ደረጃውን የጠበቀ አደረጃጀት መከተል አለመከተሉን ማረጋገጥ፣
- በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የታዩ ክፍተቶችን በመቀመር ለአዘጋጆች የማስተካከያ አስተያየት ለመስጠት ነው፡፡

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት በአዲስ መጽሐፍ ላይ የሚደረግ ጥናት ነው፡፡ ባለፈው ዝግጅት ወቅት የነበረው የተማሪዎች የንግግርና የጽህፈት ክሂል አመርቂ አልነበረም፡፡ ይኸው ምክንያት ነው የትምህርት ዝግጅቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ እንዲለወጥ ያደረገው፡፡ አጥኚው ይህን ጥናት ካጠናቀቀ በኋላ ከሚገኘው ውጤት የተነሳ የመጀመሪያዎቹ ተጠቃሚዎች ተማሪዎች ይሆናሉ፡፡ ተማሪዎች በጽህፈት ወይም በንግግር ራሳቸውን እንዳይገልጡ ያደረገው ማነቆ ከመወገዱ በፊት ማነቆው መታወቅ ነበረበት፡፡ ሁለተኛ ተጠቀሚዎች መምህራን ናቸው፡፡ መምህራን የተፈጠረውን የጽህፈትና የንግግር ክሂል ውድቀት ክፍተት ለመሙላት በዝግጅት ሲባዝኑ ይታያል፡፡ ሆኖም በጥናት ያልተደገፈ በመሆኑ የተበታተነና የተቆራረጠ ይሆንባቸዋል፡፡ በጥናት የተረጋገጠ ክፍተት ከተሰጣቸው ግን ወጥ በሆነ መንገድ ዝግጅት ያደርጋሉ ተብሎ ስለሚጠበቅ ለመምህራን ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው፡፡ በሦስተኛ ደረጃ ለትምህርት ስርዓቱ እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡ ማንኛውም ዝግጅት ከህፀፅ የፀዳ አይደለም፡፡ ስለዚህ የተገኘውን ክፍተት ለሚመለከተው በማገለፅ አፋጣኝ መፍትሄ ለመፈለግ ጠቃሚ ነው፡፡ በመጨረሻም በክሂሎች ዙሪያ ጥናት

ለሚያደርጉ ተመራማሪዎች ግብዓት ሆኖ ሊያገለግል ይችላል። በተመሳሳይ ርዕስ ወይም በተዛማጅ ርዕሶች ጥናት የሚያደርጉ ለቀጣይ ጥልቅ ጥናት ይህን ጥናት ሊጠቀሙ ይችላሉ።

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

የዚህ ጥናት ወሰን የሚያካልለው አዲሱ የ8ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መፅሀፍ ካሉት ይዘቶች መካከል የንግግርና የጽህፈት ክሂልን ነው። የትኩረት ነጥቡም የንግግርና የጽህፈት ክሂሎችን ለማዳበር የቀረቡ መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀትን መተንተን ነው። በዚህ መሠረት የተካተቱ የዕውቀት ዘርፎችና የቀሩትን የክሂል ዘርፎች አይመለከትም። ተጽፈው የሚገኙበትን ሁኔታ ባሉበት አቀራረብ መፈተሽ እንጂ አቀራረብን፣ ከውጤት ጋር ያለውን ቁርኝት ወዘተ አይመለከትም። ስለዚህ ዋና ትኩረቱ የሆነው አዲሱ የ8ኛ ክፍል አማርኛ መጽሐፍ ለንግግርና ለጽህፈት (የአፍልቆት) ክሂሎችን ለማጎልበት የቀረቡት መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀትን መፈተሽ ብቻ ነው።

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

## 2.1 የመናገር ክሂል ምንነት

ንግግር በአንደበት ክፍሎች የተቀናጀ የድምፅ አፈጣጠር ስርኣት አማካኝነት የሚፈጠር ነው፡፡ ንግግር የሰው ልጅ ስሜቱን አጠቃላይ ሀሳቡን ወይም አመለካከቱን ለሌላ ወገን ለመግለፅ የሚጠቀምበት ሂደት ነው፡፡ በመሆኑም በንግግር የተማረውም ያልተማረውም ሰው ይግባባል፡፡

ንግግር በተፈጥሮ ከማዳመጥ ቀጥሎ የሚገኝ ክሂል ነው፡፡ ንግግር ለተማሪዎች አስቸጋሪ ከሆኑት ክሂሎች መካከል አንዱ ነው፡፡ ውዳዲስ ምህረቱ (2006) Bueno, Madird, Mclaren (2001:321)ን ጠቅሰው ንግግር ከአራቱ መሠረታዊ ክሂሎች አንዱና ዋነኛው ሲሆን በዚህ ረገድ በተማሪዎች ዘንድ ብዙ ጥረት ቢኖርም አሁንም ድረስ ሰፊ የንግግር ክፍተት እንዳለባቸው ይናገራሉ፡፡

እንደ Scoot (2005:79) አገላለጽ "ንግግር በአንደበት ክፍሎች በተቀናጀ የድምፅ አፈጣጠር ስርኣት አማካኝነት የሚፈጠር አፍላቂ ክሂል ነው፤ ንግግር አዕምሮኣዊ ችሎታን የሚጠይቅ፣ የአስተሳሰብ ዕውቀት በጨመረ ቁጥር እያደገ የሚሄድና በበቂ ልምምድ ውስጥ የሚዳብር ነው፡፡" በማለት ይገልጻል፡፡ እንደገናም ንግግር የሰው ልጅ ፍላጎቱን፣ ስሜቱን፣ አጠቃላይ ሀሳቡን ወይም አመለካከቱን ለሌላ ሁለተኛ ወገን ለመግለፅ የሚጠቀምበት ሂደት ነው በማለት Venkantes Warn.S.(1997:83) ያብራራሉ፡፡ በማያያዝም Warn.S. እንደሚሉት ቋንቋ የሚባል ነገር ሲነሳ ንግግር ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል፡፡ እንዲሁም ሰው ሀሳቡን፣ አስተያየቱን፣ ፍላጎቱን በመግለፅና ማህበራዊ ትስስሮችንና ወዳጅነትን ለመፍጠር ንግግር እንደመሣሪያ ይጠቅማል በማለት ይገልጻሉ፡፡

Ur (1991:120) ከአራቱ የክሂል ዘርፎች ንግግር ግንባር ቀደምትነት አለው ይላሉ፡፡ አንድ ሰው አንድን ቋንቋ ያውቃል ሲባል ቋንቋውን መናገር ይችላል ማለት ነው፡፡ አንድን ቋንቋ በልምድ ወይም በመማር የሚናገር ሰው የቋንቋውን የድምፅ፣ የቃላትና የሰዋስው ስርኣት ጠብቆ መናገር ይጠበቅበታል፡፡ በንግግር ትምህርት ውስጥ ተማሪዎች ከነዚህ የቋንቋ ንጥረ ነገሮች በተጨማሪ የተናጋሪው የህብረተሰብ ባህል፣ ስነልቦና፣ አመለካከትና ማህበራዊ እሴቶች በመግባባቱ ሂደት

ከፍተኛ ፋይዳ እንዳላቸው መገንዘብ ይቻላል፡፡ የመናገር ትምህርት ከነዚህ ተጨባጭ ጉዳዮች ጋር በተገናዘበ መልኩ የመናገር ክሂል ኖሮአቸው መጠቀም እንዲችል መርዳት ነው፡፡

ከቋንቋ ክሂሎች ውስጥ አንዱ የሆነው የመናገር ክሂል በጣም አስፈላጊ እና ተማሪዎች እርስ በርሳቸው ጥሩ ግንኙነት ሊያደርጉ የሚችሉበት እንዲሁም ከሌሎች ጋር የምንገናኝበት ቃላዊ የቋንቋ መሣሪያ ነው በማለት Fulcher (2003:28) ያብራራሉ፡፡

በአጠቃላይ ንግግር አንድን ነገር ተረድተን የምንቀበለው እንዲሁም ምላሽ በመስጠት በማህበራዊ ሂደት ውስጥ  የምንግባባበት መሣሪያ ነው፡፡ ንግግር አንድን ነገር ለመግለፅ ድምፅንና ቃላትን በማውጣት ቋንቋን በገሃዱ አለም ውስጥ መጠቀም የሚያስችለን ነው፡፡ በአጭሩ ንግግር ስሜትን ቃላት፣ ሀረጋትና አረፍተ ነገሮች በመጠቀም የምንገልጽበትና ከሌሎች ጋር የሚንግባባበት ትርጉም ያለው የእርስ በርስ ግንኙነት ማድረግያ ነው፡፡

## 2.1.1 የመናገር ክሂልን የማስተማር አላማ

የንግግር ክሂልን ማስተማር ዋነኛው አላማ ተማሪዎችን ጥሩ ተናጋሪ ማድረግ ነው፡፡ Byren (1987:8) እንደገለጹት መምህራን ውስን ንግግርን ልቅ ወይም ነፃ ንግግርን ጎን ለጎን በማካሄድ የተማሪዎችን ችሎታ ማዳበር ይቻላል፡፡ በተጨማሪም የመናገር ክሂል የሚከተሉት የማስተማር ንዑስ አላማዎች አሉት፡፡

- የቋንቋውን ድምፀ ልሳናዊ ባህሪያት አድማጭ ሊረዳ በሚችልበት መንገድ መጠቀም እንዲችል፣
- በንግግር ሂደት ሀሳብን በቅደም ተከተል አዋቅረው ማፍለቅ እንዲችሉ፣
- መስተጋብራዊ በሆኑ የተግባቦት ሂደቶች መሳተፍ እንዲችሉ፣
- በውይይት ሂደት የተደረሰባቸውን ስምምነቶችና መደምደሚያዎች በቃል መዝግበው ማቅረብ እንዲችሉ ወዘተ…

በተጨማሪም እና Brown (1983:27) ንግግርን የማስተማር አላማ ያሏቸውን ነጥቦች እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡

- የተማሪዎችን ስነልሳናዊ ብቃት ለማሻሻል፣
- ተመሪዎች የንግግር ቋንቋ በመጠቀም በራስ የመተማመን ችሎታ እንዲያዳብሩ፣

- ❖ ችሎታን ለማሳደግ በሚደረግ ሂደት የንግግር ብቃትን ለመተንተንና ለመገምገም፣
- ❖ የፊት ለፊት መስተጋብር ብቃት ዕውቀት ለማስጨበጥ ናቸው፡፡

ከላይ የተገለጹት የመናገር ክሂልን የማስተማር አላማዎች በአቀራረብ የተለያዩ ቢመስሉም አጠቃላይ ይዘታቸው ተመሳሳይ ነው፡፡ ይህ ተግባቦታዊ ተግባር በየጊዜው እየተፈተሸና ማስተካከያ እየተደረገበት ግቡን እንዲመታ የሚደረግበትን ሂደት የሚያመለክት ነው፡፡

## 2.1.2 የመናገር ክሂል የመማር አስፈላጊነት

እንደ Harmar (1991:15) አገላለጽ የንግግር ክሂል ከጽሑፍ በበለጠ ሀሳባችንን ለመግለጽና ለማስተላለፍ የምንጠቀምበት ክሂል ሲሆን ከማዳመጥ ቀጥሎ አብዛኛውን ጊዜያችንን የምናጠፋበት መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ ሰዎች በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ጊዜ ይበልጥ መገልገል የሚፈልጉት በንግግር ነው፡፡ በመሆኑም በአብዛኛው እንቅስቃሴያችን ውስጥ ሰፊ ቦታ የሚይዝ በመሆኑ ተገቢ በሆነ መንገድና ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ ማስተማርና መማር ተገቢ ነው፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች በቋንቋ ተጠቅመው ሀሳባቸውን መግለፅ እንዲችሉ ዘመናዊ በሆነ የማስተማሪያ ዘዴ ትምህርቱ ሊሰጣቸው እንደሚገባና ሊያስገኝላቸው የሚችላቸውን ጠቀሜታዎችም እንደሚከተለው ይዘረዝራሉ፡፡

- ❖ ተገቢ ቃላትን በተገቢ ቦታ መጠቀም እንዲችሉ፣
- ❖ ተግባቦታዊ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ፣
- ❖ ሀሳብን በተጠየቃዊ ቅደምተከተል ማቅረብን እንዲለማመዱ፣
- ❖ የንግግራቸውን ፍሰት ፈር አስይዘው ሀሳባቸው እንዲገልጹ፣
- ❖ አስተያየቶችን በማስረጃ አስደግፈው ማቅረብ እንዲችሉ፣
- ❖ ኢ-መደበኛ የአነጋገር ልምድን አስወግደው መደበኛ የአነጋገር ስልትን እንዲጠቀሙ ወዘተ…

### 2.1.3 የመናገር ክሂል ደረጃዎች

የመናገር ክሂል በክፍል ውስጥ በ3 ደረጃዎች ይቀርባል። ውዳዲስ (2001) Dale, R.ad Wolf.J. (1988)ን ጠቅሶ ደረጃዎቹን እንደሚከተለው አስቀምጧል።

1. **ቅድመ ንግግር፡-** በዚህ ደረጃ ንግግር የሚደረግበትን ርዕስ ጉዳይ ወስኖ መምረጥ፣ ንግግር የሚደረግበትን አላማ ማወቅ፣ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ አድማጭን መወሰንና ዋና ዋና ሀሳባችን ማስፈር ናቸው።

2. **የንግግር ተግባራት፡-** ተማሪዎች በንግግር ሂደት እያሉ የንግግሩን ርዕስ ለአድማጭ የሚያሳውቁበት፣ አላማውን ባጭሩ የሚገልጹበት፣ ንግግሩን ሳቢ አድርገው የሚያቀርቡበት፣ በአድማጭ የሚጠየቁትን ጥያቄዎች ማስታወሻ የሚይዙበትና ለተጠየቁት ጥያቄዎች መልስ የሚሰጡበት ደረጃ ነው።

3 **ድህረ-ንግግር**፡- የተላለፈውን መልዕክት አድማጮቾ ምን ያህል እንደተገነዘቡት የሚገመግምበት ሂደት ነው። እንዲሁም አድማጮች ያልተረዱት ነገር ካላቸው አንዳንድ ጥያቄዎችን የሚጠይቁበትና አስተያየት የሚሰጡበት ደረጃ ነው። በአጠቃላይ የማዳመጥና የንግግር ክሂል በዕለት ተዕለት የሀሳብ ልውውጥ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ ጠቀሜታ አላቸው። ስለዚህ የማዳመጥና የንግግር ክሂል በተግባቦት ሂደት ውስጥ ያላቸው ድርሻ በጣም ከፍተኛ እንደመሆኑ መጠን በቋንቋ ትምህርት ሂደትም ትኩረት ተሰጥቷቸው ሊቀርቡ ይገባል።

### 2.1.4 የንግግር መልመጃ አዘገጃጀት

ንግግር በተናጋሪና በአድማጭ መካከል የሚደረግ የሁለትዮሽ ሂደት ሲሆን ይህንን ክሂል ለማዳበር የሚዘጋጁ መልመጃዎች የመማር ማስተማሩን ሂደት ከመምህር መር አቀራረብ በማላቀቅ የተማሪዎችን መስተጋብራዊ ግንኙነት የሚያበረታቱ መሆን ይኖርባቸዋል። ስለሆነም ተግባራቱ ተማሪዎችን በጥንድ፣ በሶስትዮሽ፣ በቡድን ወዘተ… የሚያሳትፉና በራስ የመተማመን ስሜት በማዳበር ሀሳባቸውን እንዲገልጹ የሚያግዙ ሊሆኑ ይገባል።

ይህንንም አስመልክተው በድሉ (2007፡91) ገለፃ መናገርን ለማስተማር የሚዘጋጁ መልመጃዎች ሁለት መልክ እንዳላቸው እንደሚከተለው ያቀርባሉ።

1. **ርዕስ ተኮር** (Topic Centered)፡- ርዕስ ተኮር መልመጃዎች ከተማሪዎች ደረጃና ዳራዊ እውቀት ተስማሚ የሆነውን ርዕስ ጉዳይ በመምረጥ የክፍል ውስጥ የንግግር ተግባራት በዚያ ዙሪያ እንዲከናወኑ የሚደረግበት ሂደት ነው፡፡

2. **ተግባር ተኮር** (Task Centered)፡- ተግባር ተኮር መልመጃዎች ተማሪዎች በመምህራን በተዘጋጁ የክፍል ውስጥ ተግባራት እየተሳተፉ ንግግር የሚያደርጉበት ነው፡፡ የሚዘጋጁት የክፍል ውስጥ ተግባራት የተማሪዎችን ዳራዊ እውቀት ወይም በመማሪያ ክፍል ውስጥና ከመማሪያ ክፍል ውጪ ያደረጉትን ንባብ መሠረት አድርገው ሊዘጋጁ ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም እንደ በድሉ (2007፡92) ገለፃ ንግግርን በማስተማር የሚዘጋጁ መልመጃዎች የሚከተሉት ባህርያት ሊኖሩ እንደሚገባ በዝርዝር አቅርበዋል፡፡ እነሱም ተማሪዎች ብዙ እንዲናገሩ የሚያደርጉ፣ ተማሪዎች ሀሳባቸውን በራሳቸው መንገድ እንዲገልፁ ዕድል የሚሰጡ መሆን እንዳለባቸው ያስረዳሉ፡፡

   እንደ Grant (1987:80) ገለፃ ለየትኛውም የክፍል ደረጃ መልመጃዎች ሲዘጋጁ ተማሪዎች ቋንቋውን በገሃድ አለም እንዲጠቀሙ የሚረዱ መሆን አለባቸው፡፡ በተጨማሪም Grant (1987:34-35) መማሪያ መፃህፍት ሲዘጋጁ የመናገር ክሂል ለማስተማር ማካተት ያለባቸውን ተግባራት እንደሚከተለው ያስቀምጣሉ፡፡

   - ❖ **ድግግሞሽ** (Drills)፡- የአንድን ድምፅ ወይም ቃል አባባልና ሰዋሰውን ተማሪዎች በተደጋጋሚ ንግግር የሚያጠኑበት ሆኖ አስቸጋሪና ፈታኝ ባልሆነ መንገድ ሁሉንም ተማሪዎች ሊያሳትፍ የሚችል መሆን አለበት፡፡

   - ❖ **ተግባቦታዊ ልምምድ** (Communicative exercise)፡- የንግግር ክሂልን ለማስተማር የተዘጋጁ የቋንቋ መማሪያ መፅሐፍት ሊይዙት የሚገባው ተግባቦታዊ ተግባር ሲሆን ከተማሪዎች የሚጠበቀው ቋንቋውን ለመግባቢያነት በመጠቀም የንግግር ክሂልን ልምምድ ማምጣት እንጂ በቋንቋው ህግና ደንብ ላይ የሚያተኩር ባለመሆኑ መምህራን ተማሪዎቹ መልዕክት ማስተላለፋቸውን ብቻ በቡድን እና ጥንድ ውይይት ላይ ቁጥጥር ያደርጉበታል፡፡

   - ❖ **ተፈጥሮኣዊ የቋንቋ አጠቃቀም** (Natural language Use)፡- ተማሪዎች በመናገር ክሂል ትምህርታቸው ርዕስ ጉዳዩ የሚጠይቀውን አውድ በትክክል ተረድተው ተፈጥሮኣዊ የሆነውን ልምምድ የሚያደርጉበት እና በመምህሩ

እገዛ ተጨማሪነት ለተግባራዊነቱን ይበልጥ እውተኛ አውዶችን በመፍጠር የሚማሩበት ሂደት መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

ከላይ በቀረበው ሃሳብ መሠረት መልመጃዎች ለአንድ ለተወሰነ የክፍል ደረጃ በተወሰነ ጊዜ ገደብ በስርዓተ ትምህርት ውስጥ ተማሪዎቹን በሚመጥን መልኩ በተመረጠው መርህ ትምህርት የተወሰኑትን ዓላማዎች ግባቸውን እንዲመቱ ተደርጎ የሚዘጋጅ የአደረጃጀት ስልት መሆኑን ነው፡፡

Ur(1996:120)ለክፍል ውስጥ መናገር ክሂል ተገቢ ተግባራትን እንደሚከተለው አስቀምጠዋል፡፡

1. **ብዙውን ጊዜ ተማሪዎች እንዲናገሩ ማድረግ፡-** በተቻለ መጠን ለንግግር ተግባር ጊዜ በተማሪዎች ንግግር መሸፈን ይኖርብናል፡፡ ጉዳዩ ግልፅ ሆኖ እያለ ግን የክፍል ውስጥ ክንውን አብዛኛውን ጊዜ በመምህሩ ይሸፈናል፡፡ ስለዚህ የመምህሩን ሚና በመቀነስ የተማሪዎች መስተጋብራዊ ግንኙነት ጉልቶ እንዲወጣ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡
2. **ሁሉን ያማከለ ተሳትፎ፡-** የክፍል ውስጥ ክንውን ጥቂት ቁጥር ባላቸው ተማሪዎች ተፅዕኖ ብቻ መውደቅ የለበትም፡፡ ሁሉም የክፍሉ ተማሪዎች የመናገር ዕድል ሊሰጣቸው እና ተሳትፎኣቸው የተመጣጠነ ሊሆን ይገባል፡፡
3. **ከፍተኛ ተነሳሽነት፡-** ተማሪዎች ለመናገር የሚነሳሱት በተመረጠው ርዕስ ጉዳይ ከፍተኛ ፍላጎት ሲኖራቸው እና ስለ ርዕሱ ጉዳዩ የሚናገሩት አዲስ ሀሳብ ስለሚኖራቸው ነው፡፡ ወይም ደግሞ በሂደቱ ተሳትፎ በማድረግ ለንግግር ተግባሩ አላማ መሳካት አስተዋጽኦ ለማበርከት ነው፡፡ ስለዚህ ተግባራቱ የተማሪዎችን ተነሳሽነት የሚያሳድጉ ሊሆኑ ይገባል፡፡
4. **የቋንቋ ቅቡልነት ደረጃ፡-** ተማሪዎች ሀሳባቸውን በንግግር ማለትም ተገቢነት ባለው መንገድ እርስ በርሳቸው መግባባት መቻላቸውንና ተቀባይነቱ ከፍ ባለ የቋንቋ ብቃት የመግለፅ አቅም ያላቸው መሆኑን ያመለክታል፡፡

ባጠቃላይ መምህራን ከላይ የተጠቀሱትን የስኬታማ የንግግር ክሂል ባህሪያት እና በቋንቋ ትምህርት የክፍል ውስጥ ክንውን ወቅት መተግበር ከቻሉ ተማሪዎች የመናገር ክሂልን በቀላሉ ሊያዳብሩ ይችላሉ፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው የንግግር ተግባር ሲከናወን መምህራኑ ለተማሪዎቹ

ግልፅ የሆነ መመሪያ በመስጠት ክፍለ ጊዜውን ተማሪዎቹ እንዲጠቀሙበት ማመቻቸት ይኖርበታል፡፡

እንዲሁም (Garinger: 2002) የመናገር ክሂል መልመጃ ይዘቶች የሚከተሉትን ማሟላት እንዳለባቸው ይገልፃል፡፡

**ተገቢነት**፡- ክሂሉ ተገቢ ትኩረት ማግኘቱን፣ በመማሪያ መጽሐፉ የቀረበው የንግግር ትምህርት መልመጃ ከተማሪዎች ዕድሜ፣ ችሎታ እና አካባቢያዊ ሁኔታዎች አንፃር ተገቢ መሆኑን፣ የንግግር ትምህርቱን የማስተማር አላማ ከማሳካት አንፃር ያለውን ተገቢነት የሚገልፅ ነው፡፡

**ግልፅነት፡-** የመልመጃዎችና የተግባራት አቀራረብ፣ የቋንቋ አጠቃቀም፣ የመመሪያ አሰጣጥ፣ እና የዓላማ አነዳደፍ ግልጽ መሆን አለበት፡፡

**ተለጣጣቂነት**፡- የቀረቡት የንግግር ትምህርት መልመጃዎች አንዱ ከሌላው የሚቀጥልና በየምዕራፉ ሲመጡ ተገቢውን የዕድገት ሂደት የጠበቁ ማለትም ከተራ ወደ ውስብስብ መሸጋገራቸውን፣ ተማሪዎች እንዲፍጨረጨሩና እንዲሞክሩ የሚገፉ፣ ለተጨማሪ ሥራ የሚያነሳሱ መሆን አለባቸው፡፡

**ተተግባሪነት**፡- ለመናገር ልምምድ የቀረቡ መልመጃዎች ለትግበራ ያላቸው አመቺነት ከተማሪዎች አቅምና ችሎታ አንፃር፣ ከመማሪያ ክፍል አውድ አንፃር፣ ከመርጃ መሣሪያ አጠቃቀም አንፃር፣ ተማሪዎች በእውኑ ዓለም የሚገጥማቸውን ህይወት እንዲለማመዱ የሚያስችሉ መሆናቸውን የምንፈትሽበት ነው፡፡

**አሳታፊነት**፡- በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኙት የንግግር መልመጃዎች ሁሉንም ተማሪ እኩል ደረጃ የሚያሳትፉ መሆን ይገባቸዋል በማለት ገልፀዋል፡፡

መልመጃዎቹ ተማሪዎችን ለዘላቂ መስተጋብር የሚያነሳሱ፣ በየምዕራፉ አዳዲስና ሳቢ ስልቶችን የሚያካትቱ፣ የንግግር ብቃታቸውን ማለትም የሰዋስውና የማህበራዊ ስነልሳን ብቃት ማበልፀግ የሚያስችሉ፣ ተገቢውን የድምፅ አጠቃቀም (ቃና፣ አወራረድ እና ፍጥነት) እንዲያጎለብቱ የሚያስችሉ መሆን አለባቸው፡፡

ተማሪዎችን ለማለማመድ የተለያዩ ዘዴዎች በመኖራቸው የንግግር ችሎታቸውን መሠረት በማድረግ የክሂሉን ብቃት ለማሳደግ ተገቢውን ደረጃ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ ሀሳብ አንፃር

Roger (1995:100-102) የመናገር ክሂልን ለማስተማር ሦስት መንገዶች መኖራቸውን በመጠቆም ሲያስረዱ፦

**1ኛ ውሱን ልምምድ፦** አንድን ነገር አይተን ወይም ሰምተን ሳንለውጥ መናገር ሲሆን የሚተገበረውም ምልልስና ዝግ የሆኑ መልሶችን በመስጠት ነው።

**2ኛ መምህር መራሽ ልምምድ፦** መምህሩ ከሚሰጣቸው ፍንጭ ላይ ተመርኩዘው ተማሪዎች በርካታ ሀሳቦችን በመግለፅ የሚናገሩበት ዘዴ ነው።

**3ኛ ነፃ ተግባቦት፦** የተማሪዎችን ግንዛቤ የሚጠይቅ ሆኖ የመናገር ነፃነት በከፍተኛ ደረጃ የሚሰጥና ሁሉንም ተማሪዎች ሊያሳትፍ የሚችል ስለሆነ ተግባሩን ሊያስፈጽም የሚችል መመሪያ በመስጠት ይከናወናል።

## 2.1.5 የመናገር ክሂል አቀራረብ መልኮች

የመናገር የክሂል የማስተማሪያ ስልቶች በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደቱን ተግባር የሚመሩ ሆነው በተማሪው መጽሐፍ ውስጥ የተጠቆሙ ናቸው። የመናገር ክሂልን ለማስተማር የሚያስችሉ የተለያዩ ስልቶች በመኖራቸው የትምህርቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በሚያስችል መልኩ የተደራጁ ስለሆነ በተማሪዎችና በሚቀርቡ ተግባራት መካከል ያለውን ሁኔታ በመረዳት አመቺ የሆነውን በመምረጥ ተጠቅሞ ማስተማር አስፈላጊ ነው (Brown 2007)

በንግግር የትምህርት አቀራረብ በውጤታማነታቸው ከሚጠቀሱ ልዩ ልዩ የንግግር ማስተማሪያ ስልቶች መካከል የሚከተሉት ስልቶች በተማሪ ተኮር የትምህርት አቀራረብ ጠቀሜታ እንዳላቸው በርካታ ምሁራን ይገልፃሉ።

### ሀ. ቃለ መጠይቅ (Interview)

በድሉ (2007፡95) እንደሚገልጹት ተማሪዎች አንድን ርዕስ ጉዳይ አስመልክተው ስለ ርዕስ ጉዳዩ መረጃ ይኖራቸዋል ብለው የሚያስቧቸውን ሰዎች በቃለ መጠይቅ መረጃ የሚሰባስቡትና ያገኙትን መረጃ አቀናብረው በክፍል ውስጥ በንግግር እንዲያቀርቡ በማድረግ ንግግርን ለማስተማር የሚጠቀሙበት ስልት ነው። በዚህ የክፍል ውስጥ ተግባር ውጤታማነት በቃል መጠይቁ ውስጥ የሚካተቱት ጥያቄዎች ብዛትና ጥራት ከፍተኛ ድርሻ አለው። መምህራን በሚሰጡት ርዕስ ተማሪዎች የተለያዩ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ሰዎች ጋር ቃለ መጠይቅ በማድረግ መረጃ ከሰበሰቡ በኋላ ከሰበሰቧቸው መረጃዎች ውስጥ

ለንግግራቸው ርዕስ የሚመጥኑትን በመምረጥ፣ በሚመቻቸው ቅደም ተከተል በማደራጀትና በማቀናበር በንግግር ለኃደኞቻቸው እንዲያቀርቡ በማድረግ የሚከናውን ነው (Byme 1987)፡፡

## ለ. ሚና ጨዋታ (Role Play)

ሚና ጨዋታ የሚለው ጽንሳ ሀሳብ ማንኛውም እንቅስቃሴ የሚመለከት ሲሆን ተማሪዎች ስለ አንድ ትምህርት ርዕስ በተጨባጨ ዓለም ድርጊቶችን ወደ ክፍል ውስጥ በማቅረብ ንግግርን ማስተማሪያ መንገድ ሲሆን በአቀራረቡ ድራማዊ ይዘት ያለው ምልልስ በመሆኑ ጥልቅ የሆነ ቁጥጥር እና ተግባራቱን በሚገባ በማጥናት የሚቀርብ ስለሆነ የንግግር ክሂልን በማሳደግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል (Byme 1987, Nunan 1989)፡፡

ለምሳሌ ተማሪዎች የአንድን መምህርና ተማሪ ወዘተ… ባህሪ ተክተው የሚያከናወኑት ተግባር ሲሆን ተማሪዎች ወክለው የተወኑትን ተግባር እንዲያስታወሱና ከአዳዲስ የቋንቋ አገላለፆች ጋር እንዲተዋወቁ ዕድል ከመስጠቱም በላይ የተማሪዎችን የቋንቋ ፍሰት ብቃታቸውን ማሻሻል እንዲችሉ ዕድል ይሰጣቸዋል፡፡ መምህሩም የተማሪዎችን ጥንካሬና ድክመት በመለየት መፍትሄ እንዲፈልግ ያደርጋል በማለት Browen R, Phillips D, Walfers s(1995:105) ገልጸዋል፡፡

Richards እና Rodgers (1985:79) "የመናገርን ክሂል ለማዳበር ይረዳ ዘንድ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ተማሪዎችን ለሚና ጨዋታ የሚጋብዙ፣ ሊያነጋግሩ የሚችሉ መልመጃዎችን በማካተት ሀሳብ እንዲለዋወጡ የሚያበረታቱ ተግባራት መኖር አለባቸው" በማለት ገልፀዋል፡፡

## ሐ. ጭውውት

ጭውውት የንግግር ክሂልን ለማዳበር አንፃራዊ ተመራጭነት ያለው ዘዴ ነው፡፡ ተማሪዎች እንደየክፍል ደረጃቸው አግባብነት የተመረጡ ቅንጫቢዎች በመጠቀም የሚያካሂዱት የጭውውት ተግባር እውነተኛ የንግግር አውድን ይፈጥራል፡፡ ለጭውውት የሚመረጠው ርዕስ ጉዳይ አግባብነት የሚመዘነው ከርዕስ ጉዳዩ ቅላትና ክብደት እንዲሁም ከተማሪዎች ዳራዊ ዕውቀት አንፃር ነው፡፡ ተማሪዎች የሚናገሩት ነገር ላይ ጥርጣሬ እንዲኖራቸውና በራስ የመተማመን ደረጃቸውን ከፍ እንዲል ያደርጋል በማለት (በድሉ 2007፡94) ገልጸዋል፡፡

## መ. ውይይት Discusion

Harmar (1989:207) "ውይይትን መሠረት ያደረገ የንግግር ተግባር ተማሪዎች ሀሳባቸውን መግለፅን፣ መደበኛ የሆኑ አገላለጾችን መጠቀምንና የውይይት ስርኣት መልመድን

ይማሩበታል፡፡ በተጨማሪም ውይይት የተማሪዎችን የመናገር ዕድል በከፍተኛ ሁኔታ ስለሚፈጥር እርስ በርስ ተቃውሞ፣ አስተያየት፣ አስታረቂ ሀሳብ ወዘተ… የማቅረብ ብቃታቸውን ያሳድጋል" በማለት ገልፀዋል፡፡

የቡድን ውይይት ተማሪዎችን አንድ የጋራ የሆነ ድምዳሜ ላይ ለማድረስ የሚያስችል የፊት ለፊት የሀሳብ ልውውጥ የንግግር ዘዴ በመሆኑ የጋራ የሆነ አላማ ለማሳካት በተወሰኑ ሰዎች መካከል የሚካሄድ እንደሆነ Ryriacou (1998:77) ይገልፃሉ፡፡

Long and poter (1985:209) የቡድንን ውይይት በተመለከተ ሲያብራሩ የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ብቃት የሚያሳድግ ነው፡፡ ምክንያቱም በተመሳሳይ ወቅት ብዙዎችን የሚያሣትፍ እንደሆነ ጭምር ገልፀዋል፡፡

## ሠ. ክርክር (Debate)

በአንድ ጉዳይ ላይ የራስን አቋም ማንፀበረቂያ ይዘት በመሆኑ ገለጻው የንግግርን ክሂል አዳባሪነቱ አጠያያቂ አይሆንም፡፡ በዚህ የንግግር መለማመጃ አሁንም ለውጤታማነቱ መምህሩ የጎላ ሚና አለው፡፡ ክርክርም ሆነ ውይይት ሲካሄድ የመደማመጥ ክሂልም ይዳብራል፡፡ የመናገር ክሂልን ለማስተማር ሲታሰብ በተለያዩ የስነጽሑፍ ስራዎች ውስጥ ያሉትን ገፀ-ባህሪያት ግጭት በንባብ በማቅረብ ከግጭት ለመውጣት የሚያደርጉትን ፍጭት አንዱን ደግፈው ሀሳብ እንዲሰጡ ማድረግ ንግግርን በክርክር ማስተማሪያ ሌላው መንገድ ነው (በድሉ 2007)

ክርክሩን ሳቢና ማራኪ ለማድረግ ለመከራከሪያነት የሚመረጡ ርዕስ ጉዳዮች የክብደት ቅለት ደረጃቸው ተመጣጣኝ መሆን እንዳለበት ጌታቸው (2004) ገልፀዋል፡፡

## ረ. ቃላዊ ሪፖርት (Oral Report)

ይህ የንግግር ዘዴ ተማሪዎች ያነበቡትንና ያዳመጡትን በራሳቸው የቃላት አጠቃቀምና የአገላለጽ ችሎታ በንግግር የሚያቀርቡበት ነው፡፡ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ቃላዊ ሪፖርት በሚያቀርቡበት ጊዜ አመቺ ሁኔታን ለመፍጠር መምህራን የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከክፍለ ጊዜው አስቀድሞ ተማሪዎች በቂ ዝግጅት ማድረጋቸውን ማረጋገጥ፣ ለሪፖርቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በቃል ሪፖርት እንዲያደርጉ ማድረግ፣ ሪፖርቱ ከቀረበ በኋላ አድማጮች ያልገባቸውን ጉዳይ እንዲጠይቁ ማድረግ፣ አቅራቢው ለተጠየቁ ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጥ ማድረግ ወዘተ… ናቸው በማለት (በድሉ 2007፣ 95) ዘርዝረዋል፡፡

### ሰ. ችግር መፍታት Problem Solving

ችግር መፍታት መፍትሄ በሚያስፈልገው አንድ ችግር ዙሪያ ተማሪዎችና መምህሩ ሆን ብለውና አቅደው ከአላማ ወደ ተመሳሳይ የመፍትሄ ሀሳብ ለመድረስ የሚጠቀሙት የመናገር ክሂል ማስተማሪያ ቴክኒክ ነው፡፡ ይህ የማስተማሪያ ቴክኒክ የቋንቋ ትምህርት አላማ መሸምደድ ሳይሆን በቋንቋው መግባባትና ተወያይቶ ለችግር መፍትሄ መስጠት መቻል ነው፤ የሚለውን መነሻ ሀሳብ መሠረት ያደረገ ነው (Johnson 1981)፡፡

ከዚህ የምንረዳው ተማሪዎች በአንድ ጠንከር ብሎ በተነሳ ጉዳይ ዙሪያ ተነጋግረው ለችግሩ የመፍትሄ ሀሳብ የማመንጨት አቅም ማዳበር እንዲችሉና ለዚህም ሲባል በማህበረሰብ ውስጥ ተመሳሳይ ሁነቶች ሲከሰቱ በእውን ተናግረው፣ ሀሳብ አመንጭተውናተወያይጠው ችግር መፍተት እንደሚችሉ ነው፡፡ የምክንያታዊነትን ልምድ ያዳብራሉ፡፡ በይሆናል ከመፈረጅና ከመወሰን ይድናሉ፡፡

### ሸ. ስለ ራስ መናገር (Expressing one self)

Harmar (2007:129) ስለራሳችንና ስለሌሎች ሰዎች ታሪኮችን በመተረክ የንግግር ችሎታችንን ማጎልበት እንችላለን፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በቋንቋቸው ስለራሳቸው መናገር መለማመድ አለባቸው በማለት አቅርበዋል፡፡

Heaton (1990:60-61) በበኩላቸው ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በንግግር ክሂል ይበልጥ እንዲጋለጡ ከፈለግን ታሪኮችን ነግረን ደግመው እንዲናገሩ ማድረግ፣ ስዕል አቅርበን አነፃፅረው ተመሳሳይነትና ልዩነታቸውን በተመለከተ ከክፍል ጓደኞች ጋር ውይይት ክርክርና ሀሳብ ለሀሳብ ልውውጥ እንዲያደርጉ ማድረግ ጠቃሚ እንደሆነ ገልፃዋል፡፡

## 2.2 የመጻፍ ክሂል ምንነት

አብዛኞቹ ምሁራን ጽህፈትን ሀሳብን በድምፅ ወይም በንግግር ወኪል ምልክቶች ወይም ትዕምርቶች አማካኝነት በወረቀት ወይም በብራና ወይም በሌላ ጠፍጣፋ ገጽ ላይ በማሳረፍ ከአንባቢ ጋር ሀሳብ የመለዋወጫ መንገድ ነው በሚል ይስማማሉ፡፡

Wallace እና ሌሎች (2004) “ጽህፈት ከሰው ልጆች ተግባቦታዊ ሂደት መከወኛ መሣሪያዎች ውስጥ አንዱ ሲሆን በቋንቋ ትምህርት ስርዓተ-ትምህርት ውስጥ ተቀርጾ የሚገኝ፣ ነገር ግን በማንኛውም የትምህርት አይነት ውስጥ ጉልህ ፋይዳ ያለው የቋንቋ ክሂል አይነት ነው”

በማለት ገልፃዋል፡፡ በሌላ በኩል Byrne (1988) በበኩላቸው "ንግግር ድምፅ ከማውጣት ያለፈ ተግባር እንደሆነ ሁሉ የጽህፈት ትዕምርቶች የተወሰኑ ስምምነቶች በተደረሱባቸው ስልቶች እየተዋቀሩ ቃላትን ሲመሠርቱ፣ ቃላትም ተዋቅረው አረፍተ ነገርን ይመሠርታሉ፡፡ ይህን መዋቅራዊ ሥራም ጽህፈት ብለን እንጠራለን" በማለት አስረድተዋል፡፡ እንደዚህ ምሁር አገላለጽ ጽህፈት ስምምነት የተደረገበት መዋቅር ነው፡፡ መዋቅሩ ውስጥ የሚካተቱ ነገሮች የራሳቸው የሆነ ቅደም ተከተል ይኖራቸዋል ማለት ነው፡፡

Raimes (1983) እንደሚገልጹት መፃፍ በአንባቢ እና በፀሐፊ መካከል የሚደረግ የተግባቦት ሂደት ነው፡፡ የዚህ ምሁር ብያኔ የሚያሳየው አንድ ፀሐፊ እውስጡ የተቀመጠውን ሀሳብ፣ ፍላጐት፣ ስሜት፣ ወይም አመለካከት በጽሑፍ አጋዥነት የሚገልጽበት ወይም በሌላ መልኩ አንባቢው የቀረበለትን ጽሑፍ ለመረዳት በሚያደርገው ጥረት የንባብ ሂደት ከፀሐፊው ጋር ተግባቦት ለመፍጠር የሚሞክርበት መንገድ እንደሆነ ነው፡፡ Byrne (1988) ደግመው ጽህፈት ወረቀትን በሆሄያት ከማዥጐርጐር ያለፈ ጥልቅ ተግባር እንደሆነ ሲገልጹ "መፃፍ፣ ሆሄያትን በወረቀት ላይ ከማስፈር ከፍ ያለ እና በአዕምሮ ውስጥ የሚፈልቀውን ሀሳብ በጽሑፍ መልክ ለአንባቢ አቀነባብሮ የመግለፅ ሂደትን የሚያመለክት ነው" ብለዋል፡፡ የዚህን ምሁር ሀሳብ ስንመለከት መፃፍ የአዕምሮ ነፀብራቅ ነው ለማለት ያስደፍረናል፡፡ አዕምሮ ያሰበውን ሀሳብ በፊደላት ውክልና በማስቀመጥ ማንበብ ከሚችል ሰው ጋር ተግባቦት መፍጠሪያ ሌላው መንገድ ነው በማለት ይቻላል፡፡

ማረው (1966፡Vii) ስለመፃፍ ያላቸውን አመለካከት በሚከተለው መልኩ ለመግለፅ ሞክረዋል፡፡ "መፃፍ ክሂለ ብዙ ተግባር ነው፤ ርዕስ የመምረጥና የማጥበብ፣ የቃላት አጠቃቀም፣ ያረፍተ ነገር አወቃቀር፣ የሀሳብ አደረጃጀት፣ የአንቀጽ አደረጃጀት ብሎም ሙሉ ድርሰት የመፃፍ ችሎታዎችን ይጠይቃል፡፡ ክሂሉ እየፃፉ መማርን የሚጠይቅ በመሆኑ ወደ ጽሑፍ ሥራ ከመገባቱ በፊት እና በኋላ በርካታ ሂደቶችን ማለፍ የግድ ይላል" በማለት አስቀምጠዋል፡፡ የማረው ብያኔ የሚያሳየው መፃፍ ድንገት ባጋጣሚ እጅ ከወረቀት ጋር ወይም ቀለም ከብራና ጋር ማገናኘት ሳይሆን በጥልቀት ማሰብን፣ ራጅምና እልህ አስጨራሽ ልምምድን፣ ደጋግሞ ማቀድና መተግበርን፣ እየተገበሩ ተመልሳው ዕቅድን መከለስን፣ ማሰብን … የሚፈልግ ውስብስብ ሥራ መሆኑን ነው፡፡

ሌሎች ምሁራንም ጽህፈትን በእይታዊ ምልክቶች በመታገዝ ሰዎች ሀሳብ ከሌሎች ጋር የሚለዋወጡበትና የእርስ በርስ መስተጋብር የሚመሠረቱበት ተግባቦታዊ መሣሪያ እንደሆነ

ይናገራሉ። በመተላለፊያ ስልትነቱም ዕይታዊ፣ በትግበራዊ (ተግባቦታዊ ባህርዩ ደግሞ ርቱዕ ክሂል እንደሆነ ይገልፃሉ (Widdowson 1987:57፣ Harmar 1991:16 Raimes 1983:5)።

ጽህፈት በተግባቦታዊ መሣሪያነቱ የተገኘን ዕውቀት ማስተላለፊያ ብቻ ሳይሆን መረጃን መቀበያ፣ በእይታዊ ምልክቶች ቀርጾ ማቆያ መንገድ ነው። ስለዚህ ጽህፈት ገጠመኞችን በመመዝገብ፣ የተለያዩ ጽሑፎችን ለምሳሌ ደብዳቤ፣ ዘገባ፣ ማስታወሻ ወዘተ ለመፃፍ፣ ለማሰብና ለመማር የሚረዳ የቋንቋ ትምህርት መሠረታዊ ክሂል ነው (Trokka 1990:2 Hadre 1982:5)::

እንደ Rivers (1981:291-294) እና Nunan (1989:36) አገላለጽ ማንኛውም ሰው በቋንቋ እንዴት መፃፍ እንዳለበት ለማወቅ የግድ መማር ይኖርበታል።

Raimes (1983:14) ስለመፃፍ ሲገልጹ ቅደም ተከተላቸውን የጠበቁና እርስ በርሳቸው ቁርኝት ያላቸው አረፍተ ነገሮችን ለማመንጨት ሀሳብን በጽሑፍ መግለፅ እጅግ ጠቃሚ ክሂል እንደሆነ ያስረዳሉ። Nunana (1989:36) Bell and Bumbey (1984)ን በመጥቀስ እንደገለፁት የጽህፈት ክሂል በአንድ ጊዜ የጽሑፍን ይዘት፣ የአፃፃፍ ስልት፣ የአረፍተ ነገር አወቃቀር፣ የቃላት ምርጫ፣የስርኣተ ነጥብ አጠቃቀም፣ የቃላት ምርጫ፣ የሀሳብ አንድነት፣ ተለጣጣቂነት፣ ተከታታይነት ወዘተ… ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚከናወን ከማሰብ ጋር የተያያዘ ውስብስብ ተግባር እንደሆነ ገልጸዋል።

Burne (1988) በበኩላቸው በአንድ ቋንቋ ውስጥ ያሉት የንግግር ድምፆች የየራሳቸው የሆነ ትዕምርታዊ ውክልና ይሰጣቸዋል። ትዕምርቶቹ የቋንቋውን ስርኣት ተከትለው ይዋሃዳሉ። እነዚህ ድምፆች ትርጉም ሊሰጡ በሚችሉበት መንገድ ተቀናጅተው ይቀርባሉ። ይህም ጽህፈት ይባላል በማለት አብራርተዋል። አክለውም ጽህፈት፣ ድምፅን አቅናጅቶ ቃላት መመስረት ብቻ ሳይሆን እነዚያን ቃላት በማቀናጀት ትርጉም ያለው አረፍተ ነገር ማዋቀርን፣ አረፍተ ነገሮችም አንቀጽ መመስረትን፣ ወዘተ… የሚያካትት ነው ገልጸዋል። ይህን የByrne ሀሳብ Harmar (1991:140) ና Nunan (1988:36) ይጋራሉ።

ከላይ በምሁራኑ ብያኔዎች መረዳት እንደምቻለው ጽህፈት የንግግር ድምፆችን የሚወክሉ ትዕምርቶች በመጠቀም ሀሳብን፣ ስሜትን፣ መረጃን፣ አመለካከትን እንዲሁም መልዕክትን ማስተላለፊያና ቀርፆ ማስቀመጫ ክሂል ነው። በሚፃፍበትም ወቅት የቋንቋው ተናጋሪዎችን የቋንቋ አጠቃቀም ስርኣት ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ነው። በተጨማሪም ጽህፈት

እንደቃላዊ ክሂል በመልመድ የማይገኝና በክፍል ውስጥ ወስኖ መማርን የሚፈልግ በመሆኑ ከፍተኛ ክትትልና ውሳኔ፣ ጥረትን የሚጠይቅ የቋንቋ መሠረታዊ ክሂል ነው። በተጨማሪም መፃፍ የሀሳብ አቀነባበር፣ የሀሳብ ፍሰት፣ የቃላት አመራረጥና የአገላለፅ ስልትን የሚጠይቅ ክሂል ነው። አብዛኞቹ ምሁራን እንደሚሉት መፃፍ የተዘጋጀ አዕምሮ ውጤት ነው። ጠቃሜታው ከፍተኛ እንደመሆኑ መጠን በጣም አስቸጋሪ መሆኑንም ብዙዎች ይናገራሉ። ትልልቆቹ ፀሃፍት ቀደደው የሚወራውሯቸው ረቂቆች የመጨረሻ ጽሑፉን ብዙ እጥፍ የሚወክሉት ለዚህ ነው። በክፍለ ጊዜ በተከበበ ሰዓት ውስጥ ጽፎ ውጤታማ የማይኮንበትም ምክንያት ጽህፈት ረዥም ጊዜ መፈለጉ ነው። ይህን የጽህፈት አስቸጋሪነት በማስመልከት Burne (1988) ሲያስረዱ ለጽህፈት አስቸጋሪነት ሦስት መሠረታዊ ምክንያቶችን ይገልፃሉ። እነዚህም ስነ ልቦናዊ ምክንያት፣ ሰዋሰዋዊ ምክንያትና ግንዛቤያዊ መክንያቶች ናቸው።

## 2.2.1 የመጻፍ ክሂል ትምህርት ዓላማ

መፃፍ በትምህርትነት የሚሰጠው በተለያዩ አላማዎች እንደሆነ ምሁራን ያስረዳሉ። ከነዚህ ምሁራን ውስጥ የተወሰኑትን በመጥቀስ በአላማነት ያስቀመጧቸውን መሠረታዊ መሠረታዊ ጉዳዮች በዝርዝር እንመልከት።

Raimes (1983) ገለፃ ተማሪዎች መፃፍን የሚሞሩባቸው አላማዎች አረፍተ ነገርን ከመፃፍ በዘለለ መልኩ የሚታይ ነው። ከአንባቢ ጋር ለመግባባት፣ ዕውቀትን ለማግኘት እንዲሁም ከዕለት ተዕለት የህይወት ገጠመኞች የሚታዩ ክስተቶችን መዝግቦ ለማቆየት ሲባል የመፃፍ ትምህርት ይሰጣል። ይኸው ምሁር የመፃፍ ክሂልን በማስተማር ሂደት ውስጥ ሊተኮርባቸው ከሚገቡ መሠረታዊ ጉዳዮች መካከል ርቱዕነት እና ትክክለኛነትን ይጠቅሳሉ። ርቱዕነት በሂደት ሊዳብር የሚችል የመፃፍ ትምህርት አንዱ አቅጣጫ ሲሆን፣ ትክክለኛነት ደግሞ በታላሚው ቋንቋ መዋቅር/ሰዋሰው ላይ ትኩረት ያደረገ የትምህርት ሌላኛው አቅጣጫ ነው። በመሆኑም በመፃፍ ትምህርት ሂደት በቋንቋው ሰዋሰዋዊ ይዘት ላይ ትኩረት የሚያደርግ ከሆነ ትክክለኛነትን ሲጠቁም፣ የመፃፍ ትምህርትን በልዩ ልዩ ተግባቦታዊ ተግባራት ተማሪዎቹ እንዲማሩ የማድረግ ተግባር ደግሞ ርቱዕነትን ያመለክታል። ከዚህ በተጨማሪ Heaton (1991) የመፃፍ ክሂልን የመማር ዓላማ ከንዑሳን ክሂል አላማዎች ጋር በማያያዝ ሀሳባቸው ይገልፃሉ። ይኸውም የመፃፍ ክሂልን መማር የተለያዩ የጽህፈት ንዑሳን ክሂሎችን (ተገቢነት፣ ያላቸውን ዐረፍተ ነገሮች የመፃፍ፣ ስርኣተ ነጥቦችን በተገቢው ቦታ ላይ የመጠቀም፣ ተቀባይነት ያለው ሀሳብ የመምረጥ፣ የማመንጨት እና አስፋፍቶ የመግለፅ፣ ተፈላጊ የሆነውን

ሀሳብ ለማስተላለፍ ተገቢ የሆኑ የአፃፃፍ ስልቶችን የመምረጥ፣ የአረፍተ ነገርና የአንቀጽ አወቃቀር ሥርዓትን ጠብቆ የመፃፍ እንዲሁም መደበኛ የሆነ የቋንቋ አጠቃቀም) የመለየት ተግባርን ይጠይቃል፡፡

ከላይ ከቀረቡት የምሁራን ዕይታዎች መረዳት እንደሚቻለው መፃፍ ከአንባቢ ጋር ተግባቦት ለመፍጠር፣ አዳዲስ ዕውቀቶችን ለማግኘት፣ አንድ ግለሰብ ወይም ማህበረሰብ በውስጡ ያለውን አመለካከት ለመግለፅ እና ለመደገፍ ልዩ ልዩ አዕምሮኣዊ ተግባራትን ለመወጣትና በታላሚው ቋንቋ ውስጥ ባሉት ሰዋሰዋዊ እና ተግባቦታዊ ክንውኖች ላይ ትኩረት ለማድረግ የሚካሄድ ጥረት እንደሆነ ነው፡፡ በአጠቃላይ የጽህፈት ክሂል የሚከተሉትን ሁኔታዎች የሚያሟላ ነው፡፡

ሀ. የንግግር ችሎታን ያዳብራል፣

ለ. መማርን ይደግፋል፣ ያበረታታል፣

ሐ. ስነልቦናዊ እርካታ ይሰጣል፣

መ. ሌሎች ክሂሎችን ያዳብራል፣

ሠ. ታሪክን ለማቆየት ይጠቅማል፣

ረ. ለምርምር ሥራ አጋዥ ኃይል ነው፡፡

## 2.2.2 የጽህፈት ትምህርት አስፈላጊነት

ተመስገን (2001) Wigand (1986)ን በመጥቀስ ተማሪው መፃፍ ከመጀመሩ በፊትም ሆነ በሚጽፍበት ጊዜ የጽህፈት ተግተራትን አላማ ለይቶ ለማወቅ ክሂሉን ባግባቡ መጠቀም እንዲችል በቂ የጽህፈት ትምህርት ያስፈልገዋል፡፡ በትምህርቱም ወቅት ለምን እንደሚጽፍ፣ ለማን እንደሚጽፍ፣ እንዴት እንደሚፃፍ፣ በመጠየቅ እንደሚፃፍበት አላማ የመፃፍ ክሂሉን የሚያዳብረው ጽህፈት ሲማር ነው፤ በማለት ጽህፈትን የማስተማር አስፈላጊነት ይገልፃሉ፡፡

ራሄል (2010) የመፃፍ ትምህርት አስፈላጊነት ሲገልጹ “ማስታወሻዎችን፣ ዘገባዎችን፣ ደብዳቤዎችን፣ የቤት ሥራዎችን፣ ገጠመኞችን ወዘተ መፃፍ አብዛኛዎቻችን በዕለት ተዕለት ህይወታችን የምናከናውናቸው ተግባራት ሲሆኑ ጥቂቶቻችን ደግሞ ልቦለድ እና ግጥም እንጽፋለን፡፡ እነዚህ የጽህፈት ተግባራት በሙሉ ተግባቦታዊ አላማ አላቸው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በዚህ ክሂል ተጠቃሚ እንዲሆኑ በትምህርት ቤት ቆይታቸው ሊያዳብሩት ይገባል፡፡

ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚያከናውኗቸው ተግባራት በርካታ በመሆናቸው እነዚህን ተግባራት ለማከናወን እና ሀሳባቸውን በጽሑፍ ለማስፈር የመፃፍ ክሂል ትምህርት አስፈላጊ ነው" በማለት ያብራራሉ፡፡

ተስፋዬ (1980) ፅህፈት ሀሳብን ለሌላ ማስተላለፊያ መሣሪያ ሲሆን በርከት ላለ ሰው ለመግለፅ፣ ለመጭው ትውልድ እንዲቆይ እና ያለፈን ነገርም ለማስታወስ እንዲረዳ የፅሑፍ አገልግሎት በጣም ከፍተኛ እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ Raimes (1983) ሰዎች ብዙ ጊዜ እርስበርሳቸው በፅሑፍ ለመግባባት ከመቻላቸው በላይ ሌላ ጠቃሚ ምክንያት አለ፡፡ እሱም ፅህፈት ተማሪዎችን እንዲማሩ የሚያግዝ በመሆኑ ነው፡፡ ተማሪዎችን እንዴት ያግዛል ለሚለው የሚከተሉትን ምላሾች አስቀምጠዋል፡፡

- ተማሪዎችን ጽህፈት የምናስተምረው ሰዋሰዋዊ መዋቅር፣ ፈሊጥ እና ቃላት እንዲዳብሩ ስለሚያደርግ ነው፡፡
- ተማሪዎች ከተማሩት በላይ ኃላፊነት ወስደው በቋንቋው የታለየ ነገር እንዲሰሩ (እንዲጽፉ) ዕድል ይሰጣል፣
- ተማሪዎች ሲጽፉ ለአዲስ ቋንቋ ተጋላጭ እየሆኑ ይመጣሉ፡፡ ሀሳባቸውን የመግለፅ አቅማቸው እና ያለማቋረጥ አይናቸውን፣ እጃቸውንና አዕምሮኣቸውን መጠቀማቸው የሚማሩትን ትምህርት ያጠናክረዋል፡፡ ምኑን ከምን ጋር እንፃፍ ብለው ሲያሰላስሉም ለፅሑፍ አዲስ የሆነን ነገር ወይም አዲስ ሀሳብ የሚገልፁበትን መንገድ እንዲፈጥሩ ያግዛል፡፡
- በሌላ በኩል ከአንባቢ ጋር መልዕክት ለመለዋወጥ ገፅ ለገፅ የመገናኘት ጫና ሳይኖርባቸው ሀሳባቸውን ለመግለፅ እና ትምህርቱን ለማጥናት ብሎም ልምዳቸውን ለመመዝገብ ስለሚጠቅም እንደሆነ ጭመር ገልጿል፡፡

የጽህፈት ትምህርት ዋና አላማ ከአንባቢ ጋር ተግባቦት መፍጠር ስለሆነ በጥረትና በጥንቃቄ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡ የጽህፈትን ትምህርት አስፈላጊነት አስመልክተው Raimes (1983) "ሰዎችን በጊዜና በቦታ ሳይገደቡ በሚታዩ ትዕምርቶች አማካኝነት ከማግባባቱም በላይ ለትምህርት መማሪያ፣ ለሀሳብ መለዋወጫና ለመሳሳሉት ጉዳዮች ጽህፈት ጠቃሚ ነው" ይላሉ፡፡ ይህ ምሁሩ የገለጹት የጽህፈት ያልተገደበ አገልግሎት ደግሞ በትምህርትነት እንዲሰጥና የዕድገት ፍላጎት እንዲኖር፣ እንዲያድግም ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ በሌላ በኩል

የRaimesን ሀሳብ ባጠናከረ መልኩ Calece Murcia (1991:241) በበኩላቸው ተማሪው በጥሩ ሁኔታ በቋንቋው እንዲጠቀምና የተግባቦትን ሂደት በጥልቀት እንዲመረምር ጽህፈት አስተዋጽኦ ያደርጋል በማለት ገልጸዋል፡፡

## 2.2.3 የጽህፈት ትምህርት ባህርይ

ጽህፈት ከባህርያቱ የተነሳ በቀላሉና በአጭር ጊዜ የሚማሩት ወይም የሚዳብር ሳይሆን የዕድሜ ልክ ጉዞ ነው(Bar Barbara 1997)፡፡ ከዚህ የተነሳ ሰፊ የልምምድ ጊዜ የሚያስፈልገው ጊዜ ፈጅ ክሂል ነው ማለት ይቻላል፡፡ ሌሎቹ ጽህፈትን አስቸጋሪ የሚያደርጉት ባህርያት ደግሞ ስነልቡናዊ፣ ስነልሳናዊና አዕምሮታዊ ገፅታዎቹ ናቸው (Reid 1993, Hedge 1988, Raims 1983, Pincas 1982)፡፡

### 2.2.3.1 ሥነ ልቡናዊ ባህርይ

በጽህፈት ክንውን ወቅት አንባቢን ማሰብ የማይቀር ተግባር ነው፡፡ መልዕክቱ ለአንባቢው እንዲደርስ ለማድረግ ፀሐፊው ይጨነቃል፡፡ (Hedge 1988:5) "የጽህፈት ትምህርት ክፍለ ጊዜ የተማሪዎች ቁና ቁና መተንፈሻ፣ እግራቸውን መፈተጊያና እርሰሳቸውን ማኘኪያ የስቃይ ጊዜ ነው" በማለት ጽህፈት በቀላሉ የሚታይ ክሂል አለመሆኑን ይገልፃሉ፡፡ ይህም ጽህፈት ባለው ስነልቡናዊ ባህርይው ምን ያህል አስጨናቂ እንደሆነ ያስገነዝባል፡፡

### 2.2.3.2 ስነልሳናዊ ባህርይ

ስነልሳን ቋንቋ የሚጠናበት ሳይንስ በመሆኑ የአንድ ቋንቋ ውስጣዊና ውጫዊ ገፅታ ይመረመርበታል፡፡ በጽህፈት ክሂል ረገድም የስነልሳን ዕውቀት አስፈላጊነት ጥያቄ ውስጥ የሚገባ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ሀሳብን በጽህፈት አማካይነት አሻሚነት ሳይኖረው መግለፅ የሚቻለው የቋንቋውን መዋቅር በማጥናት በመሆኑ ነው፡፡ ተቀባይነት ያለው የሀሳብ አደራደር እንዲገኝ የቋንቋን ህግጋት ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ የቋንቋን ስርኣት ከአጠቃቀሙ ጋር አስማምቶ በማቅረብ በጹሑፍ መግባባት ሊገኝ ይችላል፡፡ በጽሑፍ ውስጥ ወጥ ተግባቦትን ለማግኘት በንግግር ውስጥ አልባሌ መስለውን የምናልፋቸውን መዋቅሮች ሳይቀሩ ማጥናት ይገባናል (Hedge 1988)

### 2.2.3.3 አእምሮታዊ ባህርይ

ጽህፈት የአእምሮን እንቅስቃሴ የሚፈልግ መሆኑ አዕምሮታዊ ባህርይው ነው፡፡ የጽሑፍ ሥራ የግንዛቤን መዳበር ይፈልጋል፡፡ Moore (1995:13) "መፃፍ ማለት ማሰብ ማለት ነው" ይላሉ፡፡ ከዚህም ለመረዳት የሚቻለው በመጠኑም ቢሆን ሳይታሰብበት የሚከናወን የጽህፈት ተግባር አለመኖሩን ነው፡፡ የጽህፈት እውቀት እጅን አይንንና አዕምሮን በማስተባበር በተገቢ የድምፅ ምልክት ወኪሎች አማካይነት የግል ወይም የጋራ ገጠመኝን የማካፈል ችሎታን የሚጠይቅ ተግባር ነው (Reid 1993)፡፡

ስለዚህ ጽህፈት ብዙ ማሰላሰልንና ከራስ ጋር መሟገትን ይጠይቃል፡፡ የመማሪያ መፃህፍት አዘገጃጀትም እነዚህ ባህርያቱ በክሂል ላይ የሚያሳድሩትን ተፅዕኖ ከግምት ውስጥ በማስገባት የቋንቋ ትምህርት ይዘቶቹን መምረጥ ይገባቸዋል የሚል እምነት አለ፡፡

### 2.2.4 የመጻፍ ክሂል ይዘቶች

የመጻፍ ክሂል ይዘቶች ለጽህፈት ክሂል አላማ ማሳኪያ የሚመረጡ የቋንቋ አካላት ናቸው፡፡ እንደሌሎች የቋንቋ ክሂል ይዘቶች ሁሉ በቋንቋ ስርኣትና አጠቃቀም ይገለፃሉ፡፡ የጽህፈትን ትምህርትና የክሂሉን ባህርይም መሠረት ያደርጋሉ፡፡

ተማሪው በጽሑፍ ሊማረው የሚገባውን ተግባቦታዊ ክሂል ከፍ እንዲያደርግ የማህበረሰቡን የቋንቋ አጠቃቀም ከቋንቋው ስርኣት ጋር አጣምሮ ማጥናት አለበት፡፡ ለምሳሌ የአረፍተ ነገር አወቃቀር በጽህፈት የቋንቋውን ስርኣት የሚያለማምድ ይዘት ሲሆን ተረትና ምሳሌ ደግሞ ቋንቋውን ያለማምዳል፡፡ በዚህም ስርዓቱና አጠቃቀሙ ተደጋግፈው የጽህፈትን ክሂል የማሳደግ ብቃት ይኖራቸዋል የሚል እምነት አለ፡፡

### 2.2.4.1 የመጻፍ ክሂል ይዘት ከአላማ ጋር ያለው ቁርኝት

የቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ አላማ ክሂሎችን ማዳበርና የእውቀት ዘርፎችን ማስቻል ነው፡፡ የመማሪያ መፃህፍት አዘጋጆችም ዓላማውን መሠረት አድርገው ለየክሂሎቹ ተስማሚነት አላቸው የሚሏቸውን ይዘቶች ይመርጣሉ፡፡ በመጻፍ ክሂል አኳያም የተጣራ የእጅ ጽህፈት፣ የሆሄያት ትክክለኛ አገባብ ስርዓተ ነጥብና ተቀባይነት ያለው ሰዋሰውና የቃላት ምርጫ ትኩረቱን ከሚሹ ይዘቶች ይመደባሉ (Ur 1996)፡፡

የጽህፈት ክሂል ግቡን ይመታ ዘንድ ተማሪዎቹ በየደረጃቸው ምን ምን የቋንቋ አካላትን ሊማሩ ይገባቸዋል? የሚለው ጥያቄ በቅድሚያ መመለስ አለበት፡፡ ለዚህም የተማሪው ማንነት፣ የሚማርበት ዓላማ፣ የሚማርበት የጊዜ መጠን፣ ያለፈው የቋንቋ ትምህርት ዳራው፣ የቋንቋው ባህርይ፣ የተማሪውና የማህበረሰቡ ፍላጐት በወጉ ሊጠኑ የሚገባቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡

የትምህርት አላማ ይዘትን መምረጫ አንድ መስፈርት ነው፡፡ ስለዚህም ይዘት ከአላማ የሚመነጭ ነው ማለት ይቻላል (Corder 1973፣ Tyler 1949):: በዚህ መሠረት ይዘትና አላማ እንደማይነጣጠሉ መገንዘብ አይከብድም፡፡ ተማሪው ለምን እንደሚማር ከታወቀ በኂላ ያለፈ ዳራውን በመመርኮዝ ምን መማር እንዳለበት ይወስናል፡፡ ስለዚህ አላማንና ይዘትን የማይነጣጠሉ በመሆናቸው ያለይዘት ዓላማ፣ ያለ ዓላማ ይዘት አይታሰብምና ነው፡፡

## 2.2.4.2 የመጻፍ ክሂል ይዘት ከዘዴ ጋር ያለው ትስስር

የማስተማሪያ ስነ-ዘዴ ለትምህርትነት በተመረጠው ይዘት (ጉዳይ) ባህርይ የሚወሰን ነው፡፡ መንገዱም ወደ ግብ የሚጓዝበት ነው፡፡ በየዘመናቱ የቋንቋን ልዩ ልዩ ባህርያት መሠረት ያደረጉ ሥነ-ዘዴዎች ተቀርጸው ግልጋሎት ሰጥተው እንደነበር ይታወቃል፡፡ በዚህ ዘመን ውጤታማ ነው ተብሎ እየተሠራበት ያለው ተግባቦታዊ ዘዴ ተማሪው በግልም ይሁን በቡድን የጽህፈትን ክሂል በሚለማመድበት ይዘት አማካይነት ክሂሉን ለማዳበር ጥረት ሊያደርግ ይገባል የሚል አስተሳሰብን መሠረት ያደርጋል፡፡

ስለ ይዘትና ሥነ-ዘዴ Corder (1973:5) ሲገልፁ "ስነ-ዘዴ ከይዘት ይፈልቃል" ይላሉ፡፡ ይህም የሚያመለክተው ለሚመረጠው የመጻፍ ክሂል ይዘት የሚመች ስነ-ዘዴ ሊመረጥ መቻሉን ነው፡፡ ስነ-ዘዴ የተባለው ሁሉ የተዋጣለት ባለመሆኑ እንደ ይዘቱና እንደሁኔታው መርጦ መጠቀም ተመራጭ አካሄድ ነው (Rivers 1988)

በሌላ መልኩ ሥነ ዘዴ በተማሪዎች የትምህርት አቀባባል ላይ በጎም ይሁን መጥፎ ሁኔታ ሊያሳድር ይችላል፡፡ ስለዚህ የመጻፍ ክሂል ይዘቶቹ ቋንቋውን እንዲጠቀሙበት በሚያስችላቸው መንገድ ሊቀርብላቸው ይገባል ማለት ነው፡፡

### 2.2.4.3 የመጻፍ ክሂል ይዘት ተነሳሽነት (Motivation) ጋር ያላቸው ተዛምዶ

ቋንቋን በመማርና ማስተማር ሂደት የተማሪው መነቃቃት ከፍተኛ የሆነ አስተዋጽኦ አለው፡፡ የተነቃቃ ተማሪ ትምህርቱን በመቀበል ረገድ ካልተነቃቃው ተማሪ ይልቃል (Cunniqs Worth 1993, Harmar 1991):: ከዚህም መነቃቃት በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ቁልፍ ጉዳይ ሆኖ ሊጠቀስ ይገባል፡፡

የተማሪውን መነቃቃት ለመጠበቅ በትምህርት ይዘት ምርጫው ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ለመጻፍ ክሂል የሚመረጡትን ይዘቶች ተማሪው በደረጃው ሊተገብራቸው የሚችላቸው ከሆኑ መነቃቃትን ይጨምሩበታል፡፡ የይዘቶች ተማሪን አለመመጠን መነቃቃትን እንደሚቀንስ መገመት አይከብድም፡፡

ከላይ በዝርዝር ለማየት የተሞከረው ይዘቶች ከአላማ ከስነ-ዘዴና ከመነቃቃት ግር ጥብቅ ቁርኝት ያላቸው መሆኑን ነው፡፡ እያንዳንዳቸውም የሚደጋገፉ ሆነው ይታያሉ፡፡ የመነቃቃትና የስነ-ዘዴ መንደል ዓላማን ሊያደናቅፍ ይችላልና፡፡ ስለዚህ የመማሪያ መፃህፍት አዘጋጆች የጽህፈት ክሂል ይዘቶችን በመምረጥና በማደራጀት ወቅት ልብ ሊሏቸው ያስፈልጋል፡፡

### 2.2.5 የመጻፍ ክሂል ይዘቶች አደረጃጀት

የይዘት አደረጃጀት ካሉት ይዘቶች መካከል የይዘት መምረጫ መስፈቶችን ማለትም ተገቢነት፣ አስፈላጊነት፣ ዘላቂነት፣ አስደሳችነትና ለመማር ያላቸውን አመቺነት መሠረት አድርገው የተመረጡ ይዘቶች በውል የሚያያዙበት ስልት የይዘት አደረጃጀት ነው፡፡ Ponser እና Rudensky (1986:90) “ይዘቶችን ማደራጀት ማለት እንደ ባዶ አጥንት የሚቆጠረውን የትምህርት አላማ ሥጋ ማልበስ ነው” ይላሉ፡፡ ይዘቶችን ማደራጀት በይዘቶቹ መካከል መተጋገዝና ህብረት መፍጠር መሆን መረደት ይቻላል፡፡

የመጻፍ ክሂል ይዘቶች የቋንቋውን ስርኣትና አጠቃቀም ድርና ማግ አድርገው አንዱ ለሌላው ድጋፍ እየሆኑ ይደራጃሉ፡፡ የቋንቋ ትምህርት ይዘት ምርጫና ቅንብርን አጣምሮ ይይዛል፡፡ ምርጫው ምን ይቅረብ ሲል ቅንብር ደግሞ በምን ቅደም ተከተል ይቅረብ ለዚህስ መመዘኛው ምንድነው ይላል፡፡ በዚህ መሠረት እያንዳንዱ ይዘት የቀደመውን መሠረት በማድረግ መደራጀቱ ዋና ጉዳይ መሆኑን ማጤን ይቻላል፡፡ የትምህርት ይዘቶችን ማደራጀት ከሰው ልጅ የማወቅ

ባህርያት አኳያ ተጠየቃዊና ስነልቦናዊ በሆነ ቅደም ተከተል በደረጃ ማስቀመጥ ነው (Taba 1962 Bloom 1956. Tyler 1949)::

ይዘቶቹን ለማደራጀት መርሆች ሆነው የሚያገለግሉ አደረጃጀቶች ተዋረዳዊና ጎናዊ በመባል ይጣራሉ (Cunnings Worth 1995, Reid 1993, Nunan 1992, Yalden 1987, Corder 1973, Tyler 1949)::

## 2.2.5.1 ተዋረዳዊ አደረጃጀት (Vertical Organization)

ይህ የአደረጃጀት መርህ የጽህፈት ክሂል ይዘቶች በጊዜ ሂደት ውስጥ የሚኖራቸው ዕድገት ተዛምዶ የሚገለፅበት ነው፡፡ ስለዚህ አዳዲስ የቋንቋውን አካላት የአቀራረብ አድማስ በመወሰን ከተማሪው አንፃር ስነ-ትምህርታዊና ስነልሳናዊ ግምት መጨበጥ አስፈላጊ ነው፡፡ በተጨማሪም ሰዎች መማር የሚችሉት እንዴት እንደሆነ ማወቅም ለአደረጃጀት የሚጠቅም ጥበብ ነው፡፡ ሰዎች ሊማሩ የሚችሉት ከቀደመው ዕውቀታቸው ጋር ሊዛመድ በሚችል የዘት አማካኝነት ነው (Brown 1982, Bloom 1956):: በተዋረዳዊ አደረጃጀት ስር የሚመደቡት መስፈርቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

**ሀ. ተከታታይነት (Continuity)**

ይህ መስፈርት አንድን ክሂል የሚያጎለብቱ ጠቃሚ ነጥቦች ተደጋግሞ መምጣትን ይመለከታል፡፡ ተማሪው ከአንድ የቋንቋ ትምህርት ይዘት ጋር አንድ ጊዜ በመተዋወቁ ብቻ የተፈለገውን የባህርይ ለውጥ አያመጣም፡፡ ስለዚህ ይዘቱ መደጋገም አለበት፡፡ ይህም መደጋገም ተማሪው ትምህርቱን እንዳይረሳ ያደርጋል፡፡

**ለ. ተለጣጣቂነት (Sequence)**

የመጻፍ ክሂል ይዘቶች ከአላማው ጋር እንዲሰምሩ ተደርገው ተጠየቃዊ በሆነ መልክ በቅደም ተከተል የሚቀርቡበት ስልት ነው፡፡ በየክፍል ደረጃው ሊኖራቸው የሚገባውን የመነሻና የመድረሻ ነጥብ በመያዝ የሚገጣጠሙበት ነው፡፡ በዚህም ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከተራ ወደ ውስብስብ፣ ከቅርብ ወደ ሩቅ ተጠየቃዊ አካሄድን ተከትለው የሚደራጁበት መስፈርት ነው፡፡ ተማሪው የትኛውን መቼ መማር እንዳለበት ካወቅን ይህም ለምን እንደሚሆን ቀድመን ከተረዳን የተለጣጣቂነትን ጥያቄ መመለስ መቻላችን ነው፡፡ Reid (1993:86) "በመጻፍ ክሂል ረገድ ከቃላት ወደ ሀረጋት ከዚያም ወደ አረፍተ ነገሮችና አንቀጾች ምስረታ ደረጃ በደረጃ መሸጋገር

የተለጣጣቂነትን መሰፈርት የሚያሳይ አደረጃጀት ነው" ይላሉ፡፡ ስለዚህ መለጣጣቅ ውጤታማ እንዲሆን ይዘቶቹ ከተማሪው የአስተሳሳብና የግንዛቤ ደረጃ ጋር ተጣጥመው መቅረብ ይገባቸዋል ማለት ነው፡፡

ተዋረዳዊ የይዘት አደረጃጀት በተለይ ተለጣጣቂነት ባህርዩ የሚከተሉት ይዘቶች ከቀላል ወደ ከባድ ይቀርባሉ፡፡

**ዕውቀት** (Knowladge) ማስታወስንና መገንዘብን የሚጠይቅ የአንድ ክሂል ዝቅተኛው የትምህርት ደረጃ ነው፡፡

**ሽግግር** (Transfer) ዕውቀትን ተርጉሞ ሥራ ላይ የማዋልን ሁኔታ የሚይዝ የትምህርት ክፍል ነው፡፡ ምሳሌ የተዘበራረቁ ቃላትን አቀናጅቶ ዐ/ነገር መመስረት

**ተግባቦት** (Communication) ተረድቶ የመግለፅንና የትግበራን ችሎታ የሚያሳይ የትምህርት ክፍል ነው፡፡

**ትችት** (Criticism) ሒሳዊ አመለካከትና አስተያየት አዘል የሐሳብ አቀራረብን የሚጠይቅ የክሂል ከፍተኛው የትምህርት ደረጃ ነው፡፡ በዚህም እውነታን ከመላምት፣ ልዩነትን ከአንድነት፣ ተገቢን ከኢ-ተገቢ በመለየት የመፍረድን ሁኔታ ያካትታል፡፡ ምሳሌ፡- አንቀፅን ማሳጠር

እነዚህ የትምህርት ክፍሎች ለተለጣጣቂነት አደረጃጀት በእጅጉ ጠቃሚ ናቸው፡፡ በተጨማሪም በተዋረዳዊ አደረጃጀት ውስጥ ምጣኔንና ደረጃን መመልከት ተገቢ ይመስላል፡፡ ምጣኔ የትምህርት ይዘቶቹን ከተማሪው ችሎታ አኳያ የመመጠን ሁኔታ የሚጠይቅ ሲሆን ይህም ለትምህርቱ የተመደበውን ጊዜ ከግምት ውስጥ ማስገባትን የሚፈልግ ተግባር ነው፡፡ ደረጃ ደግሞ በየክፍለ ትምህርቱ ምን ያህል ይዘቶች ይካተቱ ለሚለው ጥያቄ መልስ የሚያስገኝ አደረጃጀት ነው፡፡ የትምህርት ይዘቶቹን ሚዛናዊነት በተማሪው ደረጃ መጠበቂያ ስልት ነው፡፡

### 2.2.5.2 ጎናዊ አደረጃጀት (Horizontal Organization)

በትምህርት ይዘቶች መካከል ሊኖር የሚችለው ዝምድና የሚመለከት የአደረጃጀት መርህ ነው፡፡ የመጻፍ ክሂል ይዘቶች ከሌሎች ክሂሎች ጋር ያለው ጥምረት የሚታይበትም ነው፡፡ Cunnings Worth (1995:15) "የክሂሎች ጥምረት ለአጠቃላይ የቋንቋ ችሎታ ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው፡፡ እንደዚያውም እንደ አምስተኛው ክሂል ሊቆጠር ይገባል" ይላሉ፡፡ የማስታወሻ አያያዝ፣ የቃለ መጠይቅ ዝግጅትና የቃል ጽህፈት ሁሉንም ክሂሎች አጣምረው የሚይዙ የጽህፈት ክሂል ይዘቶች መሆናቸውን መጠቆም ይቻላል፡፡

ጎናዊ ቅንብር በአንድ የክፍል ደረጃ የሚገኙ የተለያዩ የትምህርት ዘርፎች አንዱ ሌላውን ለማጎልበት የሚጫወተው ሚና የሚሳይ የአደረጃጀት መስፈርት መሆኑን ማጤን ይቻላል፡፡ የህግ ዕውቀት ያለው ሰው የማመልከቻ አፃፃፍ ህግጋትን ሊጠና ይገባል እንደማለት ነው፡፡

ከላይ በዝርዝር ለማመልከት እንደተሞከረው በሁለት አባይነት የአደረጃጀት መርሆች ሥር ተከታታይነት (Continuty)፣ ተለጣጣቂነት (Sequnce)፣ ምጣኔ (Grading)፣ ድረጃ (Staging) ውህደት (Integration) እንደሚገኙ ነው፡፡

## 2.3 የመልመጃ ምንነት

የመልመጃን ምንነት በሚመለከት በየክፍሉ የሚዘጋጁ የመምህር መምሪያዎች በፅንሳ ሀሳብ ደረጃ የቀረበን መረጃ ወይም ትምህርት ለተማሪው ግልፅ ማድረጊያና ተማሪው የተማሪውን ትምህርት የዕውቀቱ አካል የሚያደርግ የተለያየ ቅርጽና አቀራረብ ያለው ትምህርታዊ ሥራ ነው ማለት ይቻላል፡፡

Richards መልመጃን እንደሚከተለው ይገልፃሉ፡፡ "መልመጃ የማስተማር ሂደት አካል ነው፡፡ መልመጃ በዋናነት ሦስት ዓይነት ነው፡፡ በምንም መልኩና በየትኛውም የክፍል ደረጃ የሚቀርቡ መልመጃዎች ውስን (Controlled) መልመጃ፣ ጠቋሚ (guided) መልመጃና ልቅ (free) መልመጃ ናቸው፡፡"

በሌላ በኩል Longman Dictionary መልመጃን እንደሚከተለው ይገልፃል፡፡ "መልመጃ አንድን ክሂል ለመለማመድ ሲባል ታቅዶ የሚተገበር ሂደት ወይም የትምህርት ሥራ ነው፡፡ መልመጃ የተማሪዎችን የዕውቀት ደረጃ ለመፈተሽ ወይም የክሂል ብቃት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ጥያቄዎች ስብስብ ነው" በማለት አስቀምጧል፡፡

ስለዚህ መልመጃ የትምህርት ዋናው አካል ነው። ተማሪዎች በትውውቅ ደረጃ የቀረበላቸውን ክሂል ወይም ዕውቀት የራሳቸው የሚያደርጉትና የሚለማመዱት በመልመጃዎች አማካኝነት ነው። መልመጃዎች ተማሪውን ከመምህር በተጨማሪ ከተለያዩ አካላት ጋር ተገናኝቶ ዕውቀት እንዲቀስም ያደርጉታል።

## 2.3.1 የመጻፍ ክሂል መልመጃ አይነቶችና አቀራረቦች

ጽህፈትን በማስተማር ሂደት የመጻፍ ክሂል መልመጃ ተማሪዎችን የሚያግባባ ወይም መልዕክት ያዘለ ጽሑፍ እንዲያዘጋጁ የሚያበረታታ ቢሆን ይመረጣል። የጽህፈት ክሂል መልመጃዎች ሲዘጋጁ በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ቢተኮር የተሻለ እንደሚሆን pincas (1982) ያስረዳሉ።

1. የመጻፍ ክሂል መልመጃዎች ተግባራዊ ጠቃሚ በሆኑ የጽህፈት አይነቶች ላይ ማተኮር ይኖርባቸዋል።
2. የመጻፍ ክሂል መልመጃዎች የሚያተኩሩበት ልምምድ ተግባቦታዊ ወይም አገልግሎታዊ መሆን አለበት።
3. የመጻፍ ክሂል መልመጃዎች ሰዋሰውና ቃላትን ለማስተማር ከመርዳታቸው ጐን ለጐን ሌሎች ክሂሎችንም ለማሳደግ የሚረዱ መሆን አለባቸው።

ከላይ እንደተጠቀሰው የመጻፍ ክሂል መልመጃዎች ተማሪው ክሂሉን በመጠቀም መልዕክት ማስተላለፍና መግባባት እንዲችል በተግባር ሊተረጎሙ የማይችሉና በደረጃው ተማሪው ባለበት ማህበረሰብ ውስጥ ሊጠቀምባቸው የሚችሉ ሀሳቦችን ያልያዙ ሆን ብለው የተዘጋጁ መሆን የለባቸውም። የመጻፍ ክሂል መልመጃዎች ሰዋሰውና ቃላት ከማስተማር በላይ ተማሪው እንዴት መፃፍና ምን አይነት የአፃፃፍ ዘዴዎችን መከተል እንደለበት የሚያስረዱ መሆን አለባቸው። በመሆኑም የጽህፈት ክሂል መልመጃ አይነቶች ውስን የጽህፈት ክሂል መልመጃ፣ ጠቃሚ የጽህፈት ክሂል መልመጃና፣ ልቅ የጽህፈት ክሂል መልመጃ በማለት በሦስት እንደሚከፈሉ Pincas (1982) እና Raimes (1983) ይገልፃሉ።

### 2.3.1.1 ውስን የመጻፍ ክሂል መልመጃ

ይህ የመጻፍ ክሂል መልመጃ ትኩረት የሚሰጠው ለትክክለኛነት ነው፡፡ ተማሪው እንዲሠራ የሚደረገው እጅግ ውስን ነገር ነው፡፡ ከራሱ አፍልቆ የሚጨምረውና በራሱ ፍላጐት የሚከተለው የአሠራር መንገድ አይኖርም፡፡ በመሆኑም Raines (1983:95) “ውስን የጽህፈት ክሂል መልመጃ በአብዛኛው የጽሑፍ ቅርጹና ይዘት ለተማሪው ተሰጥቶት የሚሠራው መልመጃ ነው” በማለት ከላይ የቀረበውን ሀሳብ ያጠናክሩታል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ Pincas (1982) ተማሪዎች ትክክለኛ የሆነ የጽህፈት ሥራ ውጤት ለማቅረብ መመሪያ ጠብቀው የሚጽፉበት፣ ባዶ ቦታ በመሙላት የሚጽፉበት የመጻፍ ክሂል መልመጃ ነው በማለት ያስረዳሉ፡፡ ተማሪዎች ይህን የመጻፍ ክሂል መልመጃ የሚሠሩት ባዶ ቦታ በመሙላት፣ ውስን ዝርዝሮችን በመፃፍ፣ አረፍተ ነገሮችን በማያያዝ ወዘተ ሊሆን ይችላል፡፡ ከዚህ የምንረዳው ተማሪዎች ውስን ተግባር እንዲያከናውኑ የሚከተሉት ናሙና የሆነ ሥራ በመኖሩ ስህተት የመፈጸም ዕድላቸው በጣም ውስን ነው፡፡ ውስን የመጻፍ ክሂል መልመጃ በየትኛውም ደረጃ ጽህፈትን የሚማሩ ተማሪዎች ከመጀመሪያ ወደ ሌላ የመጻፍ ክሂል መልመጃ ከመሄዳቸው በፊት ልምምድ ሊያደርጉበት የሚገባ የመልመጃ አይነት ነው፡፡

### 2.3.1.2 ጠቋሚ የጽህፈት ክሂል መልመጃ

በዚህ መልመጃ ተማሪዎች እንዲለማመዱና እንዲጽፉ የሚፈለገው ጽሑፍ ፍንጭ ሊሰጣቸው የሚችልና እንደመመሪያ ሊገለገሉባቸው የሚችሉ የናሙና ጽሑፈ ይቀርብላቸዋል፡፡ ተማሪዎች ጠቋሚ የመጻፍ ክሂል መልመጃዎች በሚሠሩበት ጊዜ ከውስን የጽህፈት ክሂል መልመጃ በተሻለ መልኩ የራሳቸውን ሀሳብ የመጨመር ነፃነት አላቸው በማለት Pincas (1982) ያስረዳሉ፡፡

በተጨማሪም Raimes (1983) ጠቋሚ የጽህፈት ክሂል መልመጃ በውስንና በልቅ የጽህፈት ክሂል መልመጃዎች መካከል ያለ ድልድይ ነው፡፡ መልመጃውን ተማሪዎች በሚለማመዱበት ጊዜ የሚከተሉትን ናሙና አስፋፍተው ሊጽፉ የሚችሉት አስተዋጽኦ የተፃፈና ግማሹን እንዴት እንደሚጨርሱት ፍንጭ የሚሰጥ ጽሑፍ ወይም ልክ እንደሚነበብ ጽሑፍ አዲስ ሀሳብ የያዘ ስዕል በማቅረብ ድጋፍ በመስጠት እንዲጽፉ የሚያደርግ የጽህፈት ክሂል መልመጃ አየነት ነው፡፡ ተማሪዎች የተጀመረ ጽሑፍ ተሰጥቷቸው እንዲጨርሱ በተጠየቁ ጊዜ ጽሑፉን መጨረስ ሲለማመዱ ከራሳቸው ያፈለቁትን ሀሳብ ከተሰጠው ጽሑፍ ጋር እንዲስማማ አድርገው

መጨረስ አለባቸው፡፡ የጽሑፉን ሀሳብ ሳያዛቡ በቅደም ተከተል በራሳቸው ሀሳብ አፍልቀው ለመፃፍ ዝግጅት የሚያደርጉበት የጽህፈት ክሂል እንደሆነ ምሁሩ ያብራራሉ፡፡

### 2.3.1.3 ልቅ የመጻፍ ክሂል መልመጃ

ለቅ የጽህፈት ክሂል መልመጃ ከሌሎች የጽህፈት መልመጃዎች የሚለይበት ተማሪዎች እራሳቸው ሀሳብ አፍልቀው እንዲጽፉ ነፃነት የሚሰጥ መሆኑ ነው፡፡ ይህ የመልመጃ አይነት ባዶ ቦታዎች እንዲሞሉ፣ የተጀመሩ ዐረፍተ ነገሮችን እንዲጨርሱ፣ የአንድን ጽሑፍ የተወሰነ ክፍል እንዲጨርሱ ሳይሆን በታዛዙት መሠረት ከራሳቸው አፍልቀው በራሳቸው መንገድ ስርኣት በማስያዝ የጽሑፍ ሥራ እንዲያቀርቡ የሚያደርግ የመልመጃ አይነት ነው በማለት Pincas (1982) ያስረዳሉ፡፡

### 2.3.2 ለመፃፍ የሚያነሳሱ መልመጃዎች (ተግባራት)

ተማሪዎች የመጻፍ ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ ለማገዝ የተለያዩ መልመጃዎች ተሰጥተው ተከታታይ ልምምድ እንዲተገብሩ ማድረግ ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡ በዚህ ልምምድ ሂደትም ተማሪዎች አዳዲስ ልምዶችን ያዳብራሉ፡፡ የጽህፈት ችሎታቸውንም ቀስ በቀስ ከፍ ወዳለ ደረጃ ያሸጋግራሉ፡፡ ተማሪዎች እንደክፍል ደረጃቸው የጽህፈት ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ የሚረዱ ሦስት የጽህፈት መልመጃ ተግባራት እንዳሉ Celce Murcia (2001) ያስረዳሉ፡፡ ተግባራቱም የሚከተሉት ናቸው፡፡

#### 2.3.2.1 ተግባራዊ የጽህፈት መልመጃዎች

ተግባራዊ የጽህፈት ክሂል መለማመጃዎች ቅደም ተከተላዊ ይዘት ያላቸው ናቸው፡፡ በዚህ ልምምድና ሂደትም በማለማመጃነት ሊያገለግሉ የሚችሉት አጭር መልዕክቶች፣ ቀላል ትዕዛዞች፣ የክፍል ሥራዎች ሲሆኑ ዕድገት እያገኙ ሲሄዱ የማስታወሻ፣ የግብዣ፣ የመልዕክት፣ የሠላምታና የምስጋና ጽሑፎችን እንዲጽፉ ይደረጋል፡፡ እነዚህንና የመሳሰሉትን የመልመጃ ስልቶች በመጠቀም ተማሪዎች የተለያዩ ጽሑፎችን በክፍል ውስጥ ወይም ከክፍል ወጭ እንዲጽፉ በማድረግ የተማሪዎችን ፍላጎት ማነሳሳት ይቻላል በማለት ምሁሩ ያብራራሉ፡፡

### 2.3.2.2 የስሜት መግለጫ መልመጃዎች

ስሜት መግለጫ መልመጃዎች (ጽሑፎች) በመባል ከሚጠቀሱት ውስጥ ለንዳኛ ደብዳቤ መፃፍ፣ ስለዕለት ውሎ መመዝገብ፣ ስለሌሎች ያለንን አመለካከት መፃፍ ወዘተ መፃፍን ያካትታል። ይሁን እንጂ እነዚህን የሚመስሉ ጽሑፎች የተማሪዎችን ውስጣዊ ስሜት የሚነኩ በመሆናቸው በከፍተኛ የክፍል ደረጃዎች ለሚገኙ ተማሪዎች እንጂ ለዝቅተኛ ደረጃ ተማሪዎች እንደማይሆኑ Celce- Murcia (2001) ይጠቅሳሉ።

### 2.3.2.3 ትምህርት ቤት ተኮር የጽህፈት ክሂል መልመጃዎች

ጽህፈትን ህይወታዊ እንዲሆን የሚያደርገው ተማሪዎች በትምህርት ቤታቸው ላይ ተመስርተው ሲጽፉ ነው። ትምህርት ቤታቸው በተማሪዎች አቅራቢያ ስለሚገኝ በትምህርት ቤት ያለውን አጠቃላይ ሁኔታ ለመገንዘብ ቅርበቱ አስተዋጽኦ ስላለው የሚሰማቸውንና የሚሰጣቸውን ሀሳብ ለማደራጀት ሁኔታው ምቹ ይሆንላቸዋል በማለት ትምህርት ቤት ተኮር ጽሑፎች የተማሪዎችን የጽህፈት ክሂል ለማስለመድ ያለውን ፋይዳ Celce- Murcia (2001) ያስገነዝባሉ። ከላይ የተዘረዘሩትን ለጽህፈት የሚያነሳሱ መልመጃዎች (ተግባራት) Raimes (1983) እና Ur (1996) በሚከተለው መለኩ በዝርዝር አቅርበዋል። ተማሪዎችን እንዲጽፉ የሚያነሳሳቸው ጉዳዮች፡-

- ተማሪዎች መጽሐፍ እንዲያነቡና ስላነበቡት መጽሐፍ እንዲጽፉ ማድረግ፣
- አንድ ጽሑፍ ካነበቡ በኋላ ያነበቡትን በራሳቸው አባባል ጨምቀውና አሳጥረው እንዲጽፉ ማድረግ፣
- አንድ ስዕል በማሳየት ከስዕሉ የተገነዘቡትንና የተሰማቸውን እንዲጽፉ ማድረግ፣
- ግላዊ የህይወት ተሞክሮአቸውን በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ እንዲጽፉ ማድረግ፣
- ስለጓደኞቻቸው ወይም ስለሚያውቁት ሌላ ሰው እንዲጽፉ ማድረግ፣
- የተለያዩ ደብዳቤዎችን እንዲጽፉ ማድረግ፣ ለምሳሌ፡- የሰላምታ ደብዳቤ፣ የሥራ ደብዳቤ፣ ልዩ ልዩ የጥሪ ደብዳቤዎች፣ ወይም የመስሪያ ቤት ደብዳቤዎች እንዲጽፉ ማድረግ፣

- ተማሪዎች በሬድዮና በቴሌቭዥን ያዳመጡትን ጤና በራሳቸው የዜና ዘገባ እንዲያዘጋጁ ማድረግ፣
- ትምህርት ቤታቸውን በተመለከተ ጽሑፍ እንዲያዘጋጁ ማድረግ፣
- የመስክ ጉብኝት እንዲያደርጉ በመጋበዝ ስለተመለከተቱትና ስለተገነዘቡት ነገር እንዲጽፉ ማድረግ፣
- የተጀመሩ የተለያዩ ጽሑፎችን በመስጠት ጅምሩን አሟልተው እንዲጽፉ ማድረግ ወዘተ በማለት የዘረዘሩት ሲሆን ትልቅ ትኩረት ለደረግበት የሚገባ ጉዳይ ቢኖር ፍላጐት ለጽህፈት ወሳኝ ጉዳይ መሆኑንም ያስገነዝባሉ፡፡

## 2.3.3 የመናገር ክሂል መልመጃዎች አቀራረብ

የመናገር ክሂል ለማሳደግ ተማሪዎችን በክፍል ውስጥ ሊያሳትፉ የሚችሉ መልመጃዎችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ Harmar (2007:55) እንደሚሉት ጥሩ የመናገር ክሂል መልመጃዎች (ተግባራት) ሲዘጋጁ ተማሪዎች ሙሉ በሙሉ በትምህርቱ እንዲሳተፉ ዕድል የሚሰጡና ከልምምዱ በኋላ የመምህሩ ምጋቤ ምላሽ ግምት ውስጥ የሚያስገቡ ከሆኑ ተማሪዎች በትምህርቱ ዕርካታ ያገኛሉ፡፡ የመናገር ክሂልን እንደክሂል ተማሪዎች እንዲያዳብሩት የሚረዱ መልመጃዎች በተለያዩ ምሁራን ሥራዎች ውስጥ የተጠቀሱ ሲሆን Harmar (2007:129) ይህንኑ ሲገልጹ የመረጃ ክፍተት ተግባራት አቀጣጫን ማሳየት፣ የነገሮችን ልዩነት መናገር፣ በሠንጠረዥ መልክ የቀረቡ መልመጃዎችን ማሟላት ላይ ስለሚመሠረቱ መልመጃዎቹ የውስብስብነት ባህሪ አይታይባቸውም፡፡ ይህም ባህሪያቸው ተማሪዎች ሀሳባቸውን በቀላሉ እንዲገልጹ ይረዳቸዋል፡፡ ተረቶች (ታሪኮች) የተማሪዎችን ባህሪ ከመቅረፅ ባሻገር ስሜት የማነሳሳት አቅማቸው ከፍተኛ ነው፡፡ በድሉ ዋቅጅራ (2007፡92-93) ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የንግግር መልመጃ (ተግባር) ላይ ከመሳተፋቸው አስቀድሞ ሊያከናውኗቸው የሚገቡ ቅድመ ንግግር ተግባራት አሉ ይላሉ፡፡ እነዚህ ቅድመ ንግግር ተግባራት የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ንግግር የሚደረግበትን ርዕስ መምረጥና መወሰን፣
- ለርዕሱ ተስማሚ መረጃ መሰብሰብ፣
- ንግግር የሚደረግበትን ዓላማ መወሰን፣

አድማጭን መወሰን (ማወቅ)፣

- ዋና ዋና ነጥቦችን በማስታወሻ ማስፈር፣

እንዲሁም ቅድመ ተግባራትን ካጠናቀቁ በኋላ ወደ ንግግር ተግባር ይገባሉ፡፡

የሚከተሉት ተግባራት ተማሪዎች በንግግር ሂደት ላይ እያሉ ትኩረት ሊያደርጉባቸው የሚገቡ ናቸው፡፡

- በንግግሩ መጀመሪያ ርዕሱን ለአድማጭ በሚገባ ማስተዋወቅ፣
- የንግግሩን ዓላማ ባጭሩ ማስተዋወቅ፣
- የአድማጭን ስሜትና ፍላጐት መጠበቅ፣
- አድማጭን በአይን መቃኘት፣
- የአድማጮችን አስተያየትና ምላሽ መቀበል፣
- አስፈላጊ ከሆነ መረጃ መሣሪያ መጠቀም፣
- ንግግርን ሳቢና ማራኪ ማድረግ፣
- የአድማጮችን ጥያቄዎች በቅደም ተከተል መመዝገብ፣
- ለጥያቄዎች ምላሽ በመስጠት ማጠቃለል፣
- አድማጮችን በማመስገን መጨረስ፣

የድህረ ንግግር ተግባር ተናጋሪዎች አድማጮቻቸውን ምን ያህል መልዕክቱን እንደተረዱ የሚገመግሙበት ነው፡፡ ይህ የተወሰኑትን አድማጮች በዘፈቀደ በመምረጥ የንግግሩን ፍሬ ሀሳብ አስመልክቶ አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ለማድረግ ሊካሄድ ይችላል በድሉ (2007፡93)፡፡

ንግግር በተናጋሪና በአድማጭ መካከል የሚደረግ የሁለትዮሽ ሂደት ሲሆን ይህንን ክሂል ለማዳበር የሚዘጋጁ መልመጃዎች የመማር ማስተማሩን ሂደት ከመምህር መር አቀራረብ ለማላቀቅ የተማሪዎችን መስተጋብራዊ ግንኙነት የሚያበረታቱ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ስለሆነም መልመጃዎቹ ተማሪዎችን በጥንድ፣ በሦስትዮሽና በቡድን የሚያሳትፉና በራስ የመተማመን ስሜት በማዳበር ሀሳባቸውን እንዲገልጹ የሚያግዙ ሊሆኑ ይገባል፡፡

የንግግር መልመጃዎች ሲተገበሩ መምህራን ለተማሪዎቹ ግልፅ መመሪያ በመስጠት ክፍለ ጊዜውን ተማሪዎች በአግባቡ እንዲጠቀሙበት በማድረግ ማመቻቸት ይኖርባቸዋል፡፡ የሚከተሉት የንግግር መልመጃዎች ንግግርን ለማስተማር ተገቢ እንደሆኑ በርካታ ምሁራን ይስማማሉ፡፡

### 2.3.3.1 ጨዋታዎች

Sesnan (1997:116)"ጨዋታዎች ደስታ እየፈጠሩ የልጆችን የቋንቋ ችሎታ ለማሻሻል ይረዳሉ" ይላሉ፡፡ ጨዋታዎች በባህሪያቸው የየራሳቸው ህግና ደንብ የሚኖራቸው ውድድርን እና ትብብርን የሚጠይቁ ሁለቱንም አካተው የሚይዙ ናቸው፡፡ ስለዚህ ተማሪዎችን በቡድን ማደራጀት፣ ለጨዋታው ግልፅ ህግ ማዘጋጀት፣ የጨዋታው አሸናፊዎች የሚታውቁበት የመጨረሻዎቹ ደቂቃዎች ድረስ ሂደቱ ሁሉንም የቡድኑን አባላት የሚያሳትፍ መሆኑን ማወቅ፣ ተሸናፊዎች ከጨዋታ ውጭ ከሆኑ በኋላ እንደገና ወደ ጨዋታው የሚመለሱበት ህግ መኖሩን ማረጋገጥ፣ ወይም ጨዋታውን አሳጥሮ ቶሎ እንዲያልቅ ማድረግ ከጨዋታው በፊት የሚታሰብባቸው ጉዳዮች እንደሆኑ አስገንዝበዋል፡፡ ስለዚህ ልጆች ጨዋታ እየተጫወቱ እግረ-መንገዳቸውን የቋንቋ ችሎታቸውን ማሳደግ ይችሉ ዘንድ የመለማመጃ ተግባራቱ እንዴት እንደሚከናወኑ ዝርዝር መመሪያዎችን መምህራን በቅድሚያ ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡

### 2.3.3.2 ችግሮችን አፍለቆ መፍትሄ መሻት

ተማሪዎች ችግሮችን በሀሳባቸው አፍለቀው የችግሮቹን አስገዳጅ ሁኔታዎች በቡድን የሚመረምሩበት ነው፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች የተወሰኑ ችግሮችን በማንሳት ለችግሮቹ መፍትሄ ወይም ውሳኔ ለመስጠት የሚሞክሩበት ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ተማሪዎች እራሳቸው ማህበራዊ ሚና እንዳላቸው በመቁጠር በህብረተሰቡ ዘንድ ያሉ ችግሮችን በማንሳት የወደፊቱን እንዲተነብዩ፣ የሚያመጣውን ችግር እንዲያስቀምጡ፣ እርስ በርስ እንዲወያዩ፣ አንድ ሀሳብ ላይ እንዲደርሱ ያደርጋቸዋል፡፡ በተጨማሪም አንድን ችግር ለመፍታት የሚደረግ ህዝባዊ ውይይት ማካሄድ ለዚህ መልመጃ ጥሩ ምሳሌዎች ሊሆኑ እንደሚችሉ Sesnan (1997) ገልፀዋል፡፡

የዚህ መልመጃ ዋና ዓላማ ተማሪዎች የቀረቡላቸውን ችግሮች ከመፍታት ባለፈ ሳይታወቃቸው እርስ በርስ በሚያደርጉት የንግግር ተረክቦ የመናገር ችሎታቸውን እንዲያደብሩ ማድረግ ነው፡፡ ስለዚህ ለመለማመጃነት የሚቀርቡ ተግባራት የተማሪዎችን ችሎታ ከግንዛቤ ያስገቡ ሊሆኑ ይገባል፡፡ Beygate (1981:81) ከላይ የቀረቡ ተግባራትን ለማከናወን ሦስት ደረጃዎችን

መከተል ግዴታ እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ እነዚህም የመጀመሪያው አስፈላጊውን መረጃ የመስጫ ጊዜ፣ ሁለተኛው ችግሩን ለመፍታት የሚከናወን ውይይትና ሦስተኛ የመምህሩ ክትትል ናቸው፡፡

### 2.3.3.3 ታሪክ መናገር

Harmar (2007:129) ስለራሳችንና ስለሌሎች ሰዎች ታሪኮችን በመተረክ አብዛኛውን ጊዜያችንን እናጠፋለን፡፡ ስለሆነም ተማሪዎች በቋንቋቸው ታሪክ መናገር መለማመድ አለባቸው በማለት ሂደቱን እንደሚከተለው አቅርበዋል፡፡

ተማሪዎች በቡድን ተከፋፍለው ይቀመጣሉ፡፡ ለያንዳንዱ ቡድን ተከታታይነት ያላቸው መልዕክት አዘል ስዕሎች ይሰጣሉ፡፡ እያንዳንዱ ቡድን አባላት የየራሳቸውን ስዕል ከተመለከቱ በኋላ ይሰበሰባሉ፤ ከዚያም የመጀመሪያዎቹ ቡድኖች ተበታትነው አባላቱን የተለያዩ ቡድኖች ሆነው ይዋቀራሉ፡፡ በቀደመው ቡድን የሚቀር አንድ ተማሪ ብቻ ይሆናል፡፡ የአዲሱ ቡድን አባላት ሁሉም ከተለያዩ ቡድኖች የመጡ መሆን አለባቸው፡፡ የአዲሱ ቡድን አባላት በቀደመው ቡድን ያዩት ስዕል ምን መልዕክት እንዳለው ይተርካሉ፡፡ በመጨረሻም ቡድኖቹ የቀረበውን ታሪክ ለክፍል ያቀርባሉ፡፡ ተማሪዎች ታሪክ እንዲናገሩ ለማለማመድ የሚቀርቡ መልመጃዎች ለተማሪዎች ህይወት ቅርበት ያላቸው መሆን እንደሚገባቸው Harmar (1997:130) እንዲህ ሲሉ ይገልፃሉ፡፡ “የተማሪዎችን የመተረክ ችሎታ ለማሳደግ የየራሳቸውን ለምሳሌ፡- በሰውነታቸው ላይ ስላለ ጠባሳ፣ ስለፀጉራቸው፣ ስለጌጦቻቸው፣ ስለትምህርት መሣሪያዎቻቸው፣ ስላሰላፈት በጎ ወይም መጥፎ ገጠመኝ ወዘተ እንዲተርኩ የሚያነሳሱ ጥያቄዎችን መምህሩ እንደመነሻ ቢጠቀም ውጤቱ በጣም የተሻለ ይሆናል” ይላሉ፡፡

### 2.3.3.4 ሚና ጨዋታ

ተማሪዎች የአንድን ግለሰብ ሚና ለምሳሌ፡- የሱቅ ሻጭና ገዥ፣ መምህርና ተማሪ ባህሪ ወዘተ ተክተው የሚያከናውኑት ተግባር ሲሆን ሚና ጨዋታ ተማሪዎች ወክለው የሚተውኑትን ተግባር እንዲያስታወሱና ከአዳዲስ የቋንቋ አገላለጾች ጋር እንዲተዋወቁ ከመርዳቱም በላይ ተማሪዎች የቋንቋ ፍሰት ብቃታቸውን ማሻሻል እንዲችሉ ዕድል ይሰጣቸዋል፡፡ መምህሩም የተማሪዎቹን ጥንካሬና ድክመት በመለየት መፍትሄ እንዲፈልግ ይረዳዋል፡፡ Gower,R. Phillips,D. and Walters,S. (1995:105) የሚና ጨዋታን ፋይዳ ጠቅሰዋል፡፡ ቀላል ያሉ ሚና ጨዋታዎች ለምሳሌ ሸቀጥ ከሱቅ መግዛት አቅጣጫን ማሳየት፣ ወዘተ የመሳሳሉት በዝቅተኛ

ደረጃ ላሉት ተማሪዎች በጣም ጠቀሚ ተግባራት ሲሆኑ ውስብስብ የሆኑ ሚና ጨዋታዎች ለምሳሌ፡- በአንድ ታሪክ ውስጥ የተካተቱ ገፀ-ባህሪያትን ወክሎ መጫወት ወዘተ የክፍል ደረጃቸው ከፍ ላሉ ተማሪዎች ተገቢና ተስማሚ እንደሆኑ ምሁራኑ አክለው ገልፀዋል፡፡ ስለዚህ ለተማሪዎች የክፍል ደረጃ ተገቢነት ያላቸውን መልመጃዎች መርጦ በክፍል ውስጥ ማቅረብ የመምህራን ግዴታ ነው፡፡

### 2.3.3.5 ጭውውት

ጭውውት የመናገር ክሂልን ለማዳበር አንፃራዊ ተመራጭነት ያለው ዘዴ ነው፡፡ ተማሪዎች እንደየክፍል ደረጃቸው አግባብነት የተመረጡ ቅንጫቢዎችን በመጠቀም የሚያካሂዱት የጭውውት ተግባር እውነተኛ የንግግር አውድን ይፈጥራል፡፡ ለጭውውት የሚመረጠው ርዕስ ጉዳይ አግባብነት የሚመዘነው ከርዕስ ጉዳዩ ቅለትና ክብደት እንዲሁም ከተማሪዎቹ ዳራዊ ዕውቀት አንፃር ነው፡፡ ከተማሪዎቹ የዕውቀት ዳራ ከፍ ያለም ሆነ ዝቅ ያለ ጉዳይ ሲመረጥ ተሳትፎው መምህሩ ስለሚከተላቸው ብቻ እንጂ ጉዳዩን ጉዳዬ ስላሉት አይሆንም፡፡ የዕውቀት ዳራቸውን የሚመጠን ከሆነ መልመጃው ተስማምቷቸው ይሠራሉ፡፡

### 2.3.3.6 ቃላዊ ሪፖርት

ይህ ዘዴ ተማሪዎች ካነበቡት ወይም ደግሞ ከተመለከቱት ነገር ተነስተው በክፍል ውስጥ በመናገር ሪፖርት የሚያቀርቡበት ነው፡፡ ቃላዊ ሪፖርት ሲቀርብ መምህራን የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ይጠበቅባቸዋል፡፡

- ከክፍለ ጊዜ በፊት ለተማሪዎች የዝግጅት ጊዜ መስጠት፣
- ሪፖርቱን በቃል እንዲያቀርቡ ማድረግ (ከሰው፣ ከቦታ ስምና ሰዓት ውጭ)፣
- ከሪፖርቱ በኋላ ለአድማጮች የጥያቄ ጊዜ ማመቻቸት፣
- አቅራቢው ለተጠየቁት ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጥ ማድረግ በድሉ (2007፡95)

### 2.3.3.7 ውይይት

ውይይት ከፍተኛ ዝግጅት የሚጠይቅ ሲሆን በክፍል ውስጥ ከተማሪዎች ጋር የሚደረግ ውይይት ውጤታማ የሚሆነው የሚከተሉትን ነጥቦች ከግምት ውስጥ ያስገባ እንደሆነ፡፡ Gower,R. Phillips,D. and Walters,S. (1995:107-108) አስረድተዋል፡፡

- ተማሪዎች በሚወያዩት ርዕስ ጉዳይ ሲቀሰቀሱና የሚናገሩት ሀሳብ ሲኖራቸው፣
- ተግባሩ በአደረጃጀቱ የመናገር ፍላጐት ለመፍጠር በቂ የሆነ የማነሳሳት አቅም ሲኖረው፣
- ተማሪዎች ለውይይት የቀረበውን ጉዳይ መግለፅ የሚችል የቋንቋ ችሎታ ሲኖራቸው፣
- ተማሪዎቹ ለውይይቱ ዝግጁነትና ሀሳባቸውን ለማደራጀት የሚሰጠው ጊዜ ታሳቢነት፣
- ተግባሩ በሚፈለገው አግባብ መሄድ ማለትም ውይይቱ በውስን ተማሪዎች ተፅዕኖ አለመዋል፡፡

በክፍል ውስጥ የሚቀርቡ ውይይቶች ተማሪዎችን በማነሳሳት ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ ከዕድሜያቸውና ከችሎታቸው ጋር የሚጣጣሙ የመወያያ ይዘቶችን ማዘጋጀት ተገቢ ነው፡፡

## 2.4 ቀደምት ጥናቶች ቅኝት

ይህ በአዲሱ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የአፍልቆት ክሂሎችን (መናገርና መፃፍ) ለማዳበር የቀረቡ መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት ትንተና በሚል ርዕስ የቀረበው ጥናት በአይነቱ አዲስ ነው፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት መጽሐፉ በቀጥታ ሥራ ላይ በዋለበት በመጀመሪያው አመት የተከናወነ ጥናት በመሆኑ ነው፡፡ ይህን ጥናት ከግብ ለማድረስ ሲባል ሌሎች በርካታ የድህረ ምረቃ ተማሪዎች ጥናቶች ታይተዋል፡፡ ሆኖም በቀጥታ በዚህ ርዕስ የተሠራ ጥናት አልተገኘም፡፡ በዚህ መሠረት ጥናቱ አዲስ ነው ለማለት ያስደፍራል፡፡

ሆኖም አንዳንድ ቃላዊ ክሂሎች (ማዳመጥና መናገር) ጽሑፋዊ ክሂሎችን (መፃፍና ማንባብ) አንድ ላይ አጣምራው ወይም በየግል እያንዳንዱ ክሂል ለያይተው ከተለያዩ የአቀራረብ ዘዴዎች አንፃር ያቀረቡትን ከዚህ አጥኚ ጥናት ጋር ካላቸው ግንኙነት አንፃር ለማየት ተሞክሯል፡፡ ጥቂቶቹን ቀጥለን እንመለከት፡፡

በሰለሞን ገብሩ (2010) ዓ.ም የተሠራው "በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ በአራት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባባር ግምገማ" በሚል የቀረበው ጥናት ሞዴል የመናገር አማራጮችን በመያዝ የቀረበ ቢሆንም ትኩረቱ በአንድ ክሂል ላይ ብቻ በማድረጉ ከዚህ ጥናት ውጤቱ የተለየ እንዲሆን ሆኗል፡፡ ሌላው ልዩነት ያተኮረበት የክፍል ደረጃ ነው፡፡ ያተኮረበት የክፍል ደረጃ 10 ክፍል

ሲሆን የዚህኛው አጥኚ ጥናት ግን በ8ኛ ክፍል ላይ ትኩረቱን አድርጓል፡፡ ሰለሞን ለጥናቱ ግኝት ሲያስቀምጥ ተማሪዎች በሦስት ምክንያቶች በመናገር ክሂል ረገድ ዝቅተኛ ሆነዋል ይላል፡፡ እነዚህም መታቀብ፣ ለንግግር የሚሆን ሀሳብ ማጣትና ዝቅተኛ ወይም ሁሉን ያላማከለ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ናቸው፡፡

ሌላው የሚዛመድ ጽሑፍ እጅጉ ይማም በደብረብርሃን ከተማ በተመረጡ ሦስት ትምህርት ቤቶች "የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል አቀራረብ ግምገማ" በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ በ2003 ዓ.ም የተደረገ ጥናት ነው፡፡ ይህም እንደ ሰለሞን ገብሩ ጥናት ሁሉ በአንድ ክሂል ዙሪያ ብቻ የሚያነጣጥር ስለሆነ ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰል የተሟላ ነገር የለውም፡፡

በአያልሰው ይታየው "ከ9ኛ-12ኛ ክፍል ባሉ በአማርኛ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ በሚገኙ የልቦለድ ምንባቦች ስር የሚገኙ የመናገር ክሂል ይዘቶች አቀራረብ ትንተናና ግምገማ" በሚል ርዕስ የተጠናው ጥናት ዋና ትኩረቱ አሁንም በነዚህ አራት ክፍሎች ባሉት መፃህፍት ውስጥ ያለውን አንድ ይዘት ከምንባቦች መካከል የልቦለድ ድርሰት ቁርጭኞችን ለይቶ በማውጣት በነዚህ ስር የቀረቡ የመናገር ክሂል ይዘቶችን መፈተሻ ነው፡፡ ትኩረቱ አንድ ክሂል ብቻ ላይ በመሆኑና የክፍል ደረጃዎቹን ከሚጠናው ነገር ውስን መሆን አንፃር ከ9ኛ-12ኛ በማድረጉ የተለየ ነው፡፡

ሌላው በአዘነ ደምሴ በደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ በ2013 ዓ.ም "የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመናገር ክሂል መልመጃዎች የክፍል ውስጥ አተገባባር ፍተሻ፣ በአማራ ክልል በሰሜን ሸዋ ዞን በምረትና ጅሩ ወረዳ በተመረጡ ሦስት የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ማሳያነት" የቀረበው ጥናትም እንደቀደሙት ሁሉ መናገርን ብቻ ትኩረት አድርጎ የቀረበ ስለሆነ ውጤቱ ከዚህ ጥናት ውጤት የጠበበ ሊሆን ችሏል፡፡

ባጠቃላይ ይህን ጥናት ከላይ ከየናቸው አራት ጥናቶች ልዩ የሚያደርጉ ሦስት ዋና ዋና ጉዳዮች አሉ፡፡ እነዚህም አንደኛው ያተኮረበት ክፍል ስምንተኛ መሆኑ ነው፡፡ ከላይ የቀረቡት 7ኛ ክፍል ላይ ሁለቱ ሲያተኩሩ አንደኛው በ9ኛ ክፍል ሌላው ከ9ኛ-12ኛ ክፍሎች ላይ አትኩሯል፡፡ የትኩረት ክፍል ልዩነት አለ፡፡

ሁለተኛው ነጥብ እነዚህ ጥናቶች ትኩረታቸው በአንዱ ክሂል ላይ ብቻ ማለትም በመናገር ላይ ብቻ ሲሆን ይህኛው ጥናት በሁለቱም የአፍልቆት ክሂሎች ላይ ያነጣጥራል፡፡ ሦስተኛው ልዩነት

እነዚህ ጥናቶች በሥራ ላይ በቆዩ መፃህፍት ላይ ትኩረት ሲያደርጉ ይህኛው አጥኚ ደግሞ አዲስ በአዲሱ ስርዓተ ትምህርት መሠረት በ2015 ወደ ትግበራ በገባ አዲስ መጽሐፍ ላይ ትኩረት ማድረጉ ጥናቱን ወጥ ያደርገዋል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

# የአጠናን ዘዴ

## 3.1 የጥናቱ ንድፍ

እንደሚታወቀው አይነታዊና መጠናዊ የጥናት ንድፍ አለ፡፡ ይህ አጥኚ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎቹ ሠነድ ፍተሻና የጽሑፍ መጠይቅ በመሆናቸው ለአተናተኑ ቅይጥ የምርምር ዘዴን በመጠቀም በዋናነት አይነታዊውን በደጋፊነት ደግሞ መጠናዊውን የምርምር ዘዴ ተጠቅሟል፡፡

አይነታዊው የምርምር ዘዴ በዋናነት የተመረጠበት ምክንያት የአጥኚው ዋና የመረጃ ምንጭ የሰነድ ፍተሻ ስለሆነ ነው፡፡ የሰነድ ፍተሻው ደግሞ በአብዛኛው በገለጻ የቀረበ ነው፡፡ ስለዚህ አይነታዊው ዘዴ ዋና ሆኖ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ መጠናዊው ደግሞ በደጋፊ ዘዴነት ቀርቧል፡፡ ምክንያቱም የጽሁፍ መጠይቅ በመረጃ ምንጭነት ለመምህራን ሲቀርብ የሰነድ ፍተሻውን ሃሳብ ለመደገፍና ለማጠናከር በመሆኑ ደጋፊ የመረጃ ምንጭ ነው፡፡ ከጽሁፍ መጠይቁ የሚገኘው መረጃም በስፋት የሚተነተነው በቁጥር ስለሆነ መጠናዊውን በደጋፊ የምርምር ዘዴነት ተጠቅሟል፡፡ የጥናቱ አቀራረብ ገላጭ ንድፍ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በመሆኑም አጥኚው ቅይጥ የምርምር ዘዴ የሚጠቀሙትን የCresswell እና የያለው(2001) የምርምር መጻህፍት ለጥናቱ ተጠቅሟል፡፡

## 3.2 የክፍል ናሙና አመራረጥ

ለዚህ ጥናት ትኩረት ሆኖ የተመረጠው ክፍል 8ኛ ክፍል ነው፡፡ ምክንያቱም የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን በማጠናቀቅ ላይ የሚገኙ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ያሉበት የተግባቦት ደረጃ መታወቅ ስላለበት ክፍሉ ተተኩሮበታል፡፡ በሌላም በኩል አጥኚው ከ9ኛ ክፍል በላይ ያሉትን ተማሪዎች አማርኛ በማስተማር ከሃያ አመት በላይ ልምድ ያለው በመሆኑ ችግሩን በቅርበት ያውቀዋል፡፡ በተጨማሪም ማረው(1996) ለአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያነት በተዘጋጁ መጻህፍት ውስጥ የመጻፍ ክሂል ተገቢው ተኩረት እንዳልተሰጠውና በዚህም ምክንያት የተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ ዝቅተኛ ደካማ እንደሆነ ያስረዳል፡፡ ሰለሞን ገብሩ (2010) በበኩሉ በንግግር ክሂል ላይ ጥናት ለማድረግ ያነሳሳውን ምክንያት ሲገልጽ “የጥናቱ አቅራቢ ለዚህ ጥናት መነሻ የሆነው በስራው አለም ካካበተው ልምድ ለመገንዘብ እንደቻለው ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት በንግግር ክሂል ወቅት ከሚያሳዩት ደካማ ግብረ መልስ በመነሳት ነው፡፡

ስለዚህ የዚህ ጥናት አቅራቢም የዚህ ችግር መነሻ የነበረው በለፈው ጊዜ በነበሩት መማሪያ መጻህፍት ውስጥ ለአፍልቆት ክሂሎች የተሰጠው አነስተኛ ትኩረት በአዲሱ የስምንተኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሃፍ እንዳይደገም በጥናት አረጋግጦ ለዝግጅት ክፍሉም ሆነ ለመምህራን ሀሳብ ለመስጠት በማሰብ አዲሱን የስምንተኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሃፍ መርጦ ጥናት አካሂዷል፡፡

## 3.3 የት/ቤቶች ናሙና አመራረጥ

ይህ ጥናት በሥራ ላይ ባለ መጽሐፍ ላይ የሚከናወን እንደመሆኑ መጠን ለጥናቱ ዱራሜ ከተማ ውስጥ ካሉት የመጀመሪያ ደረጃ የመንግሥት ት/ቤቶች መካከል አራቱን መርጧል፡፡ እነዚህም ሆምቦ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ዱራሜ ቁጥር አንድ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ቀርጭቾ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤትና ዱራሜ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ናቸው፡፡ እነዚህ ትምህርት ቤቶች ሲመረጡ በምክንያት ነው፡፡ የመጀመሪያውና ዋናው ጉዳይ ለአጥኚው ካለው የቦታ ቅርበትና የመንገድ አመቺነት አንፃር ታይተው ነው፡፡ አጥኚው ማየት የተሳነው በመሆኑ እነዚህ ምርጫዎች ከዚህ አንፃር የተቃኙ ናቸው፡፡

## 3.4 የመምህራን ናሙና አመራረጥ

በነዚህ ትምህርት ቤቶች በድምሩ ሃያ ስድስት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚገኙ ሲሆን በቀጥታ ስምንተኛ ክፍል በ2015 ዓ.ም አዲሱን ዝግጅት ማስተማር የጀመሩ አስራ ሁለቱ ናቸው፡፡ የቀረበው መረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ የጽሑፍ መጠይቅ እንደመሆኑ መጠን እነዚህን አስራ ሁለት መምህራን እንዳሉ መጠቀም አስፈላጊ ሆኗል፡፡ ስለዚህ ለዚህ የተመረጠው የንሞና ዘዴ እንደ ያለው (2009፡135) መሠረት ጠቅላይ የንምና ዘዴ ነው፡፡

## 3.5 መረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች

ለዚህ ጥናት ሁለት የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ከሁለት ምንጮች መረጃ እንዲሰበሰቡ ተደርጓል፡፡ የመረጃ ምንጮቹ አዲሱ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ እና አሁን በ8ኛ ክፍል በማስተማር (የአማርኛ ቋንቋ ትምህርቶች) ላይ የሚገኙ መምህራን ናቸው፡፡ የመረጃ

መሰብሰቢያ መሣሪያዎቹም ሰነድ ፍተሻና የጽሑፍ መጠይቅ ናቸው፡፡ የሰነድ ፍተሻው ዋናው የመረጃ ምንጭ ሲሆን የጽሑፍ መጠይቅ ደግሞ ደጋፊ እንዲሆን የታሰበ ነው፡፡ የጽሑፍ መጠይቁ ለመምህራን ዝግ (አማራጭ መልስ የያዙ) እና ክፍት ጥያቄዎች እንዲቀርቡላቸው

### 3.5.1.የሰነድ ፍተሸው የትኩረት ነጥቦች (ቼክ ሊስት)

ለዚህ ጥናት ሰነድ ሆኖ የቀረበው አዲሱ የ8ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ሲሆን የሚከተሉት ጉዳዮች በፍተሻ ወቅት ይተኮርባቸዋል፡፡

- በየምዕራፉ ያሉት የክሂል አይነቶች፣
- በየምዕራፉ ያሉት ክሂሎች የያዙት አቀማመጥ ተፈጥሯዊ መሆን አለመሆኑ፣
- በምዕራፍ ውስጥ ያሉት ይዘቶች በምዕራፉ የያዙት ሽፋን ፣
- እያንዳንዱ ክሂል ከሌሎች አንጻር በየምዕራፉ የያዘው ሽፋን ፣
- በየምዕራፉ ብሎም በመጽሀፉ ባጠቃላይ ያለው የሁሉም ክሂሎች ስርጭት ፍትሃዊነት፣
- የጽህፈትና የንግግር ክሂሎች ሽፋን ፍትሃዊነት በተላይና ባጠቃላይ፣
- ንግግርና ጽህፈት ከይዘት አደረጃጀትና አቀራረብ መርህ አንጻር የሚሉ ናቸው፡፡

### 3.5.2.የጽሁፍ መጠይቅ አዘገጃጀት

ለዚህ ጥናት በጽሁፍ መጠይቅ አማካኝነት መረጃ የሚሰበሰበው ከመምህራን ነው፡፡ለጽሁፍ መጠይቁ የሚሆኑ ጥያቄዎችን ለማዘጋጀት የያለው እንዳወቀ``የምርምር መሰረታዊ መርሆዎች አተገባበር`` እና የአለም እሼቱ``መሰረታዊ የምርምርና ዘገባ አጻጻፍ``መጻህፍት ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ ጥያቄዎቹም አብዛኞቹ ዝግ ሲሆኑ ሁለት ጥያቄዎች ብቻ ክፍት ሆነው ቀርበዋል፡፡የጥያቄዎቹ አይነት መለያየት ለመረጃ አጠነቃቀር ካለው አመቺነት አንጻር ታይቶ የተደረገ ነው፡፡የጥያቄዎቹ አስተማማኝነትም የጥናት ልምድ ባላቸው መምህራንና በጥናቱ አማካሪ ተጣርቷል፡፡

### 3.6 መረጃ አተናተን ዘዴ

ከሁለቱም የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች የተገኙ መረጃዎች በተለያዩ ሠንጠረዥች በመዘጋጀት በአይነታዊና በመጠናዊ የአተናተን ዘዴ በመተንተን ቀርበዋል፡፡ የመረጃ አተናተን ሂደቱ ክሂሎች የቀረቡበትን መጠን አንዱን ከሌላው በንጽጽር የሚያቀርብ በመሆኑ መጠናዊነት ሊጐላበት ችሏል፡፡ ባጠቃላይ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት የመፃፍና የመናገር ክሂል ይዘቶች የቀረቡበት ሁኔታ በሰነድ ፍተሻ ከተሰበሰበው መረጃ ጋር ከመምህራን የጽሑፍ

መጠይቅ የተገኙት መረጃዎች ተደምረው የአቀራረብና የአደረጃጀት ሂደቱን በሚያሳይ መልኩ በአይነታዊ በዋናነት በመጠናዊ በደጋፊነት የመረጃ መተንተኛ ስልት ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## 4. የመረጃ ትንተናና ማብራሪያ

## 4.1 የመረጃ ትንተና

ለዚህ ጥናት ሰነድ ሆኖ የሚፈተሸው አዲስ ወደ ትግበራ የገባው የ8ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ነው፡፡ መጽሀፉ በደቡብ ክልል ትምህርት ቢሮ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጀ ነው፡፡ የቋንቋ ክሂሎችን በሚጠቁሙ፣ሀገራዊና ክልላዊ ባንዲራዎች በሚያሳዩ ስዕሎችም የተዋበ መጽሀፍ ነው፡፡ የትምህርት ሚኒስቴር ንብረት መሆኑን የሚጠቁም የትምህርት ሚኒስቴር አርማም አለበት፡፡ በውስጠኛው የሽፋን ገጽ የመጽሐፉ ዝግጅት ክፍል አባላት የሚጠቁም ዝርዝር ያለ ሲሆን የመግቢያና የማውጫ ገጾች ተከታይ ሆነው ቀርበዋል፡፡

በአጠቃላይ ለአንድ ዓመት ለክፍሉ የተወሰነው ይዘት በአሥር ምዕራፎች፣ እያንዳንዱ ምዕራፍም የተለያየ መጠን ባላቸው ትምህርቶች ተከፋፍሎ ተቀምጧል፡፡ ከፍ ባሉት ክፍሎች ክፍል አንድ፣ ክፍል ሁለት ወዘተ በሚል የቀረበው ይዘት በዚህ በ8ኛ ክፍሉ መጽሐፍ ትምህርት አንድ ትምህርት ሁለት ወዘተ በሚል ቀርቧል፡፡ የትምህርቶቹ ብዛት በምዕራፎች መካከል ተመሳሳይ መጠን ያለው የስርጭት ሽፋን የለውም፡፡ መጽሐፉ በጠቅላላው 135 ገጾች አሉት፡፡

በዚህ በአራተኛው ምዕራፍ የ8ኛ ክፍል መጽሐፍ ካካተታቸው ይዘቶች መካከል የአፍልቆት ክሂሎች (መናገርና መፃፍ) ይዘት መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

### 4.1.1 የ8ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ አጠቃላይ ይዘቶች ዳሰሳ

ለዚህ ጥናት አጥኚው የመረጠው አዲስ በ2015 ዓ.ም ወደ ሙሉ ትግበራ የገባው የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ነው፡፡

የጥናቱ ዋና ትኩረት በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት የንግግርና የጽህፈት ክሂል መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት መፈተሻ ነው፡፡ በዚህ ንዑስ ክፍል በአጠቃላይ በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት አጠቃላይ ይዘቶች ተዘርዝረው ቀርበዋል፡፡

ሠንጠረዥ 1፦ አጠቃላይ የአዲሱ 8ኛ ክፍል ይዘቶች ዝርዝር

| ምዕራፍ | የምዕራፉ ርዕስ ጉዳይ | ትምህርት | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 |
| 1 | የህይወት ቅመም | ማዳመጥ | መናገር | ማንበብ | መፃፍ | መፃፍ | | | | | | | |
| 2 | የህይወት መመሪያ | ማዳመጥ | መናገር | ማንበብ | መፃፍ | ቃላት | ቃላት | መፃፍ | መናገር | መናገር | | | |
| 3 | የሰው ልጆች አቅም | ማዳመጥ | መናገር | መናገር | መናገር | መናገር | ማንበብ | መናገር | መፃፍ | መፃፍ | ቃላት | ሰዋሰው | ሰዋሰው |
| 4 | አካቶ ትምህርት | ማዳመጥ | መናገር | ማንበብ | መፃፍ | ቃላት | ቃላት | ቃላት | ቃላት | ቃላት | | | |
| 5 | የተሰደዱ ስሞች | ማዳመጥ | መናገር | ማንበብ | መፃፍ | መፃፍ | ሰዋሰው | ሰዋሰው | ሰዋሰው | ሰዋሰው | | | |
| 6 | ወዳጅ ሲከዳ | ማዳመጥ | መናገር | ማንበብ | መፃፍ | መፃፍ | መናገር | ቃላት | ሰዋሰው | ሰዋሰው | | | |
| 7 | ኮተት | ማንበብ | ማዳመጥ መናገር | መናገር | መናገር | መናገር | መፃፍ | መናገር | ማንበብ | ስነ-ጽሑፍ | መናገር | ሰዋሰው | ሰዋሰው |
| 8 | ወራሾቹ | ማዳመጥ | መናገር | ማንበብ | ማንበብ | ማንበብ | መፃፍ | | | | | | |
| 9 | አባይ | ማዳመጥ | መናገር | መፃፍ | መፃፍ | ማንበብ | ማንበብ | መናገር | ማንበብ | | | | |
| 10 | ሀብታሙ ሰው | ማዳመጥ | መናገር | መናገር | መናገር | መናገር | መናገር | መናገር | መናገር | መናገር | | | |

ከላይ ሠንጠረዥ 1 የሚያመለክተው በአስሩ ምዕራፎች የተሠራጩትን የትምህርት ይዘቶች ነው፡፡ ይዘቶቹ ትምህርት በሚል የምዕራፉ ንዑስ ክፍል ተወክለዋል፡፡ እያንዳንዱ ምዕራፍም በትምህርቶች ተከፋፍሏል፡፡ የየምዕራፉ ትምህርቶች እንደሚከተለው ተተንትነዋል፡፡

በምዕራፍ አንድ አምስት ትምህርቶች አሉ፡፡ እነዚህም መፃፍ በሁለት ትምህርቶች ቀርቧል፡፡ የቀሩት ማዳመጥ፣ ማንበብና መናገር በአንዳንድ ትምህርቶች ቀርበዋል፡፡

ምዕራፍ ሁለት ዘጠኝ ትምህርቶች ያሉት ሲሆን መናገር በሦስት ትምህርቶች የተወከለ ሲሆን፣ ቃላትና መፃፍ እያንዳንዳቸው በሁለት በሁለት ትምህርቶች ቀርበዋል፡፡ ማዳመጥና ማንበብ ደግሞ በአንዳንድ ትምህርቶች በየግል ተወክለዋል፡፡

ምዕራፍ ሦስት አስራ ሁለት ትምህርቶችን ያካተተ ሰፊ ምዕራፍ ነው፡፡ በዚህ ምዕራፍ መናገር በአምስት ትምህርቶች በመቅረብ ከፍተኛ ሽፋን አለው፡፡ ሰዋሰውና መፃፍ እያንዳንዳቸው በሁለት በሁለት ትምህርቶች የቀረቡ ሲሆን ማዳመጥና ቃላት እያንዳንዳቸው በአንድ በአንድ ትምህርት አማካኝነት ቀርበዋል፡፡

ምዕራፍ አራት ዘጠኝ ትምህርቶችን የያዘ ምዕራፍ ነው፡፡ በዚህ ምዕራፍ ሰፊ ሽፋን የተሰጠው የቃላት ትምህርት ሲሆን በአምስት ትምህርቶች ቀርቧል፡፡ የቀሩት ማዳመጥ፣ መናገር፣ መፃፍና ማንበብ እያንዳንዳቸው በአንዳንድ ትምህርቶች ቀርበዋል፡፡

ምዕራፍ አምስት ዘጠኝ ትምህርቶች ያሉት ምዕራፍ ነው፡፡ በዚህ ምዕራፍ ሰዋሰውና ጽህፈት ቀዳሚውን ቦታ ይዘዋል፡፡ ሰዋሰው፣ በአራት ትምህርቶች የቀረበ ሲሆን መፃፍ በሁለት ትምህርቶች ቀርበዋል፡፡ የቀሩት ማዳመጥ፣ ማንበብና መናገር እያንዳንዳቸው በአንድ በአንድ ትምህርቶች አማካኝነት ቀርበዋል፡፡

ምዕራፍ ስድስት በዘጠኝ ትምህርቶች ተሸንሽኖ ለትምህርትነት ቀርቧል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ሰዋሰው፣ መናገርና መፃፍ በተመሳሳይ በሁለት በሁለት ትምህርቶች የተወከሉ ማዳመጥ፣ ቃላትና ማንበብ በአንዳንድ ትምህርቶች አማካኝነት ቀርቧል፡፡

ምዕራፍ ሰባት ከምዕራፍ ሦስት ጋር ተመሳሳይ ቁጥር ባላቸው በአስራ ሁለት ትምህርቶች የተከፋፈለ ነው፡፡ በዚህ ምዕራፍ የማንበብና ሰዋሰው መልመጃዎች በሁለት በሁለት ትምህርቶች ቀርበዋል፡፡ መፃፍ፣ ማዳመጥና ሥነ-ጽሑፍ በአንዳንድ ትምህርቶች ተካተዋል፡፡ አብዛኛው

የምዕራፉ ክፍል ስድስት ትምህርቶች የመናገር ክሂል የቀረበባቸው ናቸው፡፡ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ማዳመጥና መናገር በጋራ የቀረቡበት ትምህርት አለ፡፡

ምዕራፍ ስምንት ከአጫጭር ምዕራፎች መካከል ይመደባል፡፡ ማዳመጥ፣ መናገርና መፃፍ በአንዳንድ ትምህርቶች ሲቀርቡ የቀሩት ሦስት ትምህርቶች ማንበብን የያዙ ናቸው፡፡

ምዕራፍ ዘጠኝ በስምንት ትምህርቶች የተደራጀ ነው፡፡ ከእነዚህ ትምህርቶች ማንበብ በሦስት፣ መናገርና መፃፍ በሁለት በሁለት እና ማዳመጥ በአንድ ትምህርት ተወክሏል፡፡

ምዕራፍ አስር በዘጠኝ ትምህርቶች ተቀናጅቶ ቀርቧል፡፡ ይህ ምዕራፍ በስፋት መናገርን የያዘ ነው፡፡ ስምንቱ ትምህርቶች ስለ መናገር የቀረቡ ናቸው፡፡ የቀሩት ማዳመጥን የያዘ ነው፡፡

ከላይ በስፋት እንዳብራራው በአስሩም ምዕራፎች 90 ትምህርቶች ተደራጅተው የቀረቡ ሲሆን በአዲሱ የ8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ እንደአጠቃላይ ሰፊ ሽፋን የተሰጠው ለመናገር ክሂል መልመጃዎች ነው፡፡ ከዘጠና ትምህርቶች በ30ዎቹ የቀረቡት የመናገር ክሂል መልመጃዎች ናቸው፡፡ የመጽሐፉ አንድ ሦስተኛው እጅ በንግግር መልመጃዎች የተሸፈነ ነው፡፡ ከንግግር ቀጥሎ በስፋት የቀረበው የመፃፍ መልመጃ ነው፡፡ አስራ ስድስቱ ትምህርቶች በጽህፈት መልመጃዎች የተሸፈኑ ናቸው፡፡ በአዲሱ የ8ኛ ክፍል መጽሐፍ ለተለያዩ ይዘቶች የተሰጠውን ሽፋንና ትኩረት ከሚከተለው ሠንጠረዥ እንመልከት፡፡

ሠንጠረዥ፡ 2 በ8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ያሉ ይዘቶች የስርጭት ሽፋን

| የየክሂሉ ይዘቶችና መልመጃዎች ዝርዝር | ይዘትና መልመጃው የቀረበባቸው ትምህርቶች ብዛት | መልመጃው (ይዘቱ) ከጠቅላላው የተሰጠው ሽፋን |
|---|---|---|
| ማዳመጥ | 10 ትምህርቶች | 11.1% |
| መናገር | 30 ትምህርቶች | 33.3% |
| ማንበብ | 14 ትምህርቶች | 15.5% |
| መፃፍ | 15 ትምህርቶች | 16.6% |
| ቃላት | 9 ትምህርቶች | 10% |
| ሰዋሰው | 10 ትምህርቶች | 11.1% |
| ሥነ ጽሑፍ | 1 ትምህርቶች | 1.1% |
| ድምር | 90 ትምህርቶች | 100% |

ከላይ በሠንጠረዡ በግልጽ እንደተጠቆመው መጽሐፉ በስፋት ያተኮረው በንግግር ክሂል ዙሪያ ባሉት መልመጃዎች ላይ ሲሆን ሥነ-ጽሑፍ የመጨረሻው ትኩረት ተሰጥቶታል፡፡ የዚህ ጥናት አቅራቢ ትኩረት በአፍልቆት ክሂሎች ማለትም መናገርና መፃፍ ላይ ስለሆነ ትንታኔው ከላይ ከቀረቡት ዝርዝሮች በስፋት በመቅረብ ቀዳሚ ትኩረት በተሰጣቸው በመናገርና በመፃፍ ላይ በማድረግ ትንታኔው ቀርቧል፡፡

### 4.1.2 በ8ኛ ክፍል አዲሱ የ8ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ለአፍልቆት ክሂሎች የሰጠው ትኩረት

#### 4.1.2.1 የመናገር ክሂል መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት

ከላይ በሠንጠረዥ ሁለት እንደታየው የመናገር ክሂል ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው ነው፡፡ በመጽሐፉ ውስጥ በሁሉም ምዕራፎች ተሰራጭቷል፡፡ የንግግር ክሂል በአስሩም ምዕራፎች ውስጥ የሚገኝ ሲሆን በአብዛኞቹ ከአንድ ትምህርት በላይ ተደጋግሞ ቀርቧል፡፡ ከአስር

ትምህርቶች በስምንቱ የመናገር ክሂል መልመጃ የቀረበበት ምዕራፍም አለ፡፡ ለአብነት የሚከተለውን ሠንጠረዥ እንመልከት፡፡

ሠንጠረዥ፡ 3 የመናገር ክሂል መልመጃዎች የስርጭት ሽፋን

| ምዕራፍ | ከምዕራፉ ትምህርቶች መካከል የንግግር መልመጃ የቀረበባቸው መልመጃዎች | በየምዕራፉ ውስጥ የሚገኙ መልመጃዎች | | ከምዕራፉ ውስጥ የንግግር ክሂል የያዘው ሽፋን |
|---|---|---|---|---|
| | | ጠቅላላ መልመጃዎች ብዛት | የንግግር ክሂል መልመጃዎች | |
| 1 | ትምህርት 2 | 5 | 1 | 20% |
| 2 | ትምህርት 2፣ 8፣9 | 9 | 3 | 33.3% |
| 3 | ትምህርት 2፣ 3፣ 4፣ 5፣ 7 | 12 | 5 | 41.6% |
| 4 | ትምህርት 2 | 9 | 1 | 11.1% |
| 5 | ትምህርት 2 | 9 | 1 | 11.1% |
| 6 | ትምህርት 2፣ 6 | 10 | 2 | 20% |
| 7 | ትምህርት 2፣ 3፣ 4፣ 5፣ 7፣ 10 | 12 | 6 | 50% |
| 8 | ትምህርት 2 | 6 | 1 | 16.6% |
| 9 | ትምህርት 2፣ 7 | 8 | 2 | 25% |
| 10 | ትምህርት 1፣ 2፣ 3፣ 4፣ 5፣ 7፣ 8፣ 9 | 10 | 8 | 80% |
| ድምር | 30 ትምህርቶች | 90 | 30 | |

ሠንጠረዥ ሦስት በግልጽ የሚያሳየው በአስሩም ምዕራፎች ያለው የመናገር ክሂል ሽፋን ወጥ ሆኖ ያልቀረበ መሆኑን ነው፡፡ ለምሳሌ ምዕራፍ አስር 90 በመቶው በንግግር መልመጃዎች የተሸፈነ ሲሆን ምዕራፍ አራትና ምዕራፍ አምስት ከዘጠኝ ትምህርቶች መካከል አንዱ ትምህርት ብቻ የንግግር መልመጃ የቀረበበት ሆኗል፡፡ ይህ ልዩነት የሚያሳየው የንግግር ክሂል በምዕራፎች መካከል የያዘውን የሥርጭት ፍትሃዊ ያለመሆንን ነው፡፡ ከአጠቃላይ በመማሪያ መጽሐፉ ሊተኮርባቸው ከሚገቡ ሰባት የይዘት አይነቶች መካከል ንግግር በአጠቃላይ በመማሪያ መጽሐፉ ከቀረቡት ዘጠና ትምህርቶች ሰላሳ ትምህርቶችን መልመጃዎች ሸፍኗል፡፡ ይህም መጽሐፉ ለክሂል የሰጠውን ከፍተኛ ትኩረት ያመለክታል፡፡ 33.3% የመጽሐፉ መልመጃዎች

የንግግር ክሂሉን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ይህን ጉዳይ ግልፅ ለማድረግ የሚከተለው ሠንጠረዥ የያዘውን ትንታኔ እንመልከት፡

**ሰንጠረዥ4፡- የንግግር ትምህርት መልመጃዎች አደረጃጀትና አቀራረብ**

ይህ በሠንጠረዥ (አባሪ 2 ይመልከቱ) በግልፅ የሚያሳየው የንግግር መልመጃዎች ከሌሎች ክሂሎች መልመጃዎች አንፃር ሲታይ በራቀ ልዩነት ሰፋ ያለ የሥርጭት ሽፋን ያላቸው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የመናገር ክሂል መልመጃዎችም ቢሆኑ በመጽሐፉ ውስጥ ባሉት ምዕራፎች የያዙት የሥርጭት ሽፋን ይለያል፡፡ ለምሳሌ ምዕራፍ አስር ሰማኒያ በመቶው ንግግር ነው፡፡ ከአስር ትምህርቶች ስምንቱ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ንግግርን የሚያበረታቱ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ እንዲሁም ምዕራፍ ሦስት ወደ 42% ገደመ በንግግር የተሸፈነ ይዘት ያለው ነው፡፡ ምዕራፍ ሰባትም በበኩሉ የመልመጃዎቹ ግማሽ (50%) በንግግር ተሸፍኗል፡፡ ይዘቱ በውስን ምዕራፎች ተከማችቶ በሌሎቹ ደግሞ በተመጣጣኝ ደረጃ ቀርቧል፡፡ የንግግር ይዘት ትኩረት አልሰጣም ሊባል የሚችል ምዕራፍ የለም፡፡ በሁሉም ምዕራፎች መገኘቱ እንደ ጥንካሬ ቢቆጣርም ተማሪዎችን ሊያስለች በሚችል መልኩ ተከታታይ ክፍለ ጊዜያትን ምናልባትም ሳምንታትን በሚሸፍን መልኩ መሆኑ ግን አሰልቺነትን ያመጣል፡፡ ለምሳሌ በሣምንት ሁለት ትምህርት የሚሰጥ ቢሆን በምዕራፍ አስር ለንግግር ብቻ አራት ሣምንት በተከታታይ ያስፈልጋል ማለት ነው፡፡ አንድ ወር በንግግር ሊሸፈን መሆኑ ነው፡፡

## 4.1.2.2. አዲሱ 8ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ለመጻፍ ክሂል የሰጠው ትኩረት

ቀደም ሲል ሠንጠረዥ 2 አጠቃላይ የ8ኛ ክፍል አማርኛ አዲሱ መጽሐፍ የያዛቸው መልመጃዎች የሥርጭት ሽፋን አሳይቷል፡፡ በሠንጠረዡ ንግግርን በመከተል ሰፊ ሽፋን ተሰጥቶት የቀረበው የመፃፍ ክሂል ይዘት ነው፡፡ ይዘቱን ለማስረጽ በትንሹ ከዘጠና አጠቃላይ የመጽሐፉ መልመጃዎች መካከል አስራ አምስቱ የመፃፍ መልመጃዎች እንደሆኑ በሠንጠረዡ ተመላክቷል፡፡

እነዚህ አስራ አምስት የመፃፍ መልመጃዎች ዘጠኙ ምዕራፎች የያዙትን የሥርጭት ሽፋን ከሚከተለው ሠንጠረዥ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ምዕራፍ አስር የመፃፍ መልመጃ የለውም፡፡

*<u>ሠንጠረዥ 5</u>፡- በአዲሱ የ8ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ያለው የጽህፈት መልመጃ የሥርጭት ሽፋን*

| ምዕራፍ | ከምዕራፉ ትምህርቶች መካከል የመፃፍ ክሂል የቀረበባቸው | የምዕራፉ ጠቅላላ መልመጃዎች ብዛት | የምዕራፉ የመፃፍ ክሂል ብዛት | መፃፍ የያዘው ሽፋን በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ትምህርት 4፣ 5 | 5 | 2 | 40% |
| 2 | ትምህርት 4፣ 7 | 9 | 2 | 22.2% |
| 3 | ትምህርት 8፣ 9 | 12 | 2 | 16.6% |
| 4 | ትምህርት 4 | 9 | 1 | 11.1% |
| 5 | ትምህርት 4፣ 5 | 9 | 2 | 22.2% |
| 6 | ትምህርት 4፣ 5 | 10 | 2 | 20% |
| 7 | ትምህርት 6 | 12 | 1 | 8.3% |
| 8 | ትምህርት 6 | 6 | 1 | 16.6% |
| 9 | ትምህርት 3፣ 4 | 8 | 2 | 25% |
| 10 | መፃፍ የለም | 10 | | 0% |
| ድምር | | 90 | 15 | |

ሠንጠረዥ 5 የሚጠቁመው በአዲሱ የ8ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በየምዕራፉ ያለውን የመጻፍ ክሂል ሥርጭታዊ አደረጃጀት ነው፡፡ የመፃፍ ክሂል ሥርጭት ከንግግር በተለየ መልኩ ከሞላ ጎደለ ተመጣጣኝነት ያለው ይመስላል፡፡ ከሁለት መልመጃዎች ወይም ትምህርቶች በላይ የያዘ ምዕራፍ የለም፡፡ በመጽሐፉ ውስጥ ካሉት አስር ምዕራፎች መካከል የመፃፍ ክሂል በአንድ ትምህርት የተወከለባቸው ሦስት ምዕራፎች ናቸው፡፡ ምዕራፍ አራት፣ ምዕራፍ 7፣ ምዕራፍ ስምንት ናቸው፡፡ የቀሩት ምዕራፎች በሁለት በሁለት ትምህርቶቻቸው የመፃፍ ክሂል መልመጃዎችን ይዘዋል፡፡ ምዕራፍ 10 ጽህፈትን አልያዘም፡፡

ከንግግር ክሂል በጣም ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ ጽህፈት በሙሉ መጽሐፉ በ15 ትምህርቶች ተወክሏል፡፡ ይህም በመቶኛ 16.6% ይሆናል፡፡ 33.3% ሽፋን ካለው የንግግር ክሂል አንፃር ሲታይ ተመሳሳይ ሥርጭት እንዳለው ያሳያል፡፡ ይህን ጉዳይ ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ የመፃፍ ክሂል ያተኮረባቸውን የመልመጃ አይነቶች ከሚከተለው ሠንጠረዥ እንመልከት፡፡

ሰንጠረዥ 6፡- የጽህፈት መልመጃዎች ስርጭት

በሰንጠረዥ (አባሪ 3 ይመልከቱ) ለመግለፅ እንደተሞከረው ከጽህፈት አቀራረብ አንፃር ሲታይ የ8ኛ ክፍል አማርኛ መጽሐፍ በ10ኛ ምዕራፉ ጽህፈትን አልነካም፡፡ ከዚህ ውጭ ያሉት ግን ተመጣጣኝ ሥርጭት ያላቸው ናቸው፡፡ በጽህፈት ዝግጅቱም ከአነስተኛው ዐረፍተ ነገር ጀምሮ እስከ ትልቁ መዋቅር ድርሰት ድረስ ለመፃፍ የሚቀሳቅሱ መልመጃዎች በየደረጃው ጽህፈትን በመለማመድ ከልምምድ በኋላ በመፃፍና የፃፉትን በጥንድና በቡድን በመገምገም የእርስ በርስ መማማርን በሚያበረታታ መልኩ ቀርቧል፡፡ አንድ ምዕራፍ ሙሉ በሙሉ የጽህፈትን መልመጃ አለመያዝ ከስርጭት ፍትሃዊነት አንፃር ተቀባይነቱ የወረደ ነው ማለት ይቻላል፡፡

## 4.1.3 ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና

ከጽሑፍ መረጃዎችን ለመግኘት በሦስት ክፍሎች ተከፍለው የተዘጋጀ ጥያቄዎች ቀርበው የሚከተለው መረጃ ተሰብስቧል፡፡

**ክፍል 1፡- በመጠይቁ የተሳተፉ የመምህራን አጠቃላይ መረጃ**

በዚህ ጥናት 12 በ2015 ዓ.ም የ8ኛ ክፍል አማርኛ በማስተማር ላይ የሚገኙ መምህራን ቢመረጡም ሦስቱ በተለያዩ ምክንያቶች በጽሁፍ መጠይቁ አልተሳተፉም፡፡ ስለዚህ የሚቀጥለው ሠንጠረዥ የአራት ሴትና የአምስት ወንድ መምህራንን የጽሑፍ መጠይቅ ውጤት የሆነውን መረጃ የያዘ ነው፡፡

ሠንጠረዥ 7፦ የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን አጠቃላይ መረጃ

| ተቁ | መጠይቁ ዓይነት | | የመ/ራን መረጃ | | | ሌሎች በምክንያት አልተሳተፉም |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ወንድ | ሴት | ድምር | |
| 1 | የመ/ራን ብዛት | | 5 | 4 | 9 | |
| 2 | የመ/ራን ዕድሜ ከ25-30 | | 1 | 2 | 3 | |
| | ከ30 ዓመት በላይ | | 4 | 2 | 6 | |
| 3 | የመ/ሩ የትምህርት ደረጃ | 12+3 | 3 | 3 | 6 | |
| | | ቢኤ ዲግሪ | 2 | 1 | 3 | |
| 4 | የመ/ሩ አገልግሎት | ከ6–10 ዓመት | | 1 | 1 | |
| | | ከ11–20 ዓመት | 1 | 1 | 2 | |
| | | ከ21-30 | 3 | 2 | 5 | |
| | | ከ30 በላይ | 1 | | 1 | |
| 5 | በአማርኛ ቋንቋ መ/ርነት ያገለገሉበት ዘመን | ከ0–10 | 1 | 1 | 2 | |
| | | ከ11–20 | 1 | 1 | 2 | |
| | | ከ21–30 | 3 | 2 | 5 | |
| | | ከ30 በላይ | | | | |
| 6 | በ2015 የሚያስተምሩበት ክፍል ደረጃ | 7ኛ--8ኛ | 1 | 1 | 2 | |
| | | 8ኛ | 3 | 3 | 6 | |
| | | 8ኛና በላይ | 1 | | 1 | |
| 7 | ሌላ የትምህርት ዓይነት ሰልጥነው አማርኛ የሚያስተምሩ መ/ራን | | | | | |

ከላይ በክፍል 4.1.3 ለማብራራት እንደተሞከረው በዕቅድ ለመጠይቅ ከተያዘው የ8ኛ ክፍል መ/ራን መካከል በመጠይቁ ወቅት ዝግጁና ፈቃደኛ ሆነው የተገኙት ዘጠኝ መምህራን የቀረበላቸውን የጽሑፍ መጠይቅ ሞልተው መልሰዋል፡፡ ከጠቅላላ መምህራን የመላሾች ብዛት ከአራት እጅ ሶስቱ ወይም 75% በመሆኑ ምላሾቹ ተቀባይነት አግኝተዋል፡፡ በመጠይቅ ከተሳተፉት መምህራን መካከል ስድስት መምህራን (66.6%) ዕድሜያቸው ከ30 ዓመት በላይ ነው፡፡ የቀሩት ሦስቱ (33.4%) ከ25–30 ዓመት መካከል ናቸው፡፡ ይህ የሚያሳየው መ/ራኑ የቀረቡላቸውን ጥያቄዎች አመዛዝነው ለመመለስ የሚያስችል የዕድሜ ደረጃ ላይ መሆናቸውን ነው፡፡ በስሜት በመሆን የግብር ይውጣ ሥራ ላይሠሩ ይችላሉ፡፡ ስለሆነ ከመ/ራኑ የሚገኘው መረጃ ተኣማኒ ነው ማለት ነው፡፡

የመምህራኑ የትምህርት ደረጃ የሚያሳየው ደግሞ ሁሉም የመጀመሪያ ዲግሪ ከበቂ ልምድ ጋር አጣምረው የያዙ ናቸው፡፡ በ12+3 እና በ12+4 ዲግሪ የተመረቁ መሆናቸውን መልሳቸው

ያሳያል። የሥራ ልምዳቸው በአጠቃላይና በአማርኛ ቋንቋ መምህርነት በተለይ ሲታይ አንዲት መ/ርት ከ10 ዓመት በታች፣ ሁለት መ/ራን ከ11-20 ዓመትና የቀሩት ስድስት መ/ራን ከ21 ዓመት በላይ አጠቃላይ አገልግሎት ይዘዋል። በአማርኛ ቋንቋ መ/ርነት በተለይ ደግሞ ሁለቱ መምህራን ከ10 ዓመት በታች አገልግሎት አላቸው። አምስቱ መ/ራን ከ20 ዓመት በላይ የአማርኛ መ/ርነት አገልግሎት ያላቸው ሲሆን አንድ አንጋፋ መ/ር ከ30 ዓመት በላይ አገልግሎት አላቸው።

የጥናቱ ተሳታፊ መምህራን በ2015 ዓ.ም አማርኛን ከ7ኛ ክፍል ጀምሮ እያስተማሩ ያሉ ናቸው። ሁለት መ/ራን 7ኛና 8ኛ ክፍሎችን የሚያስተምሩ፣ አምስቱ መ/ራን 8ኛ ክፍልን ብቻ ያስተምራሉ። አንድ መምህር በመንግሥስት ት/ቤት 8ኛ ክፍልን በትርፍ ጊዜው ደግሞ በግል ድርጅት ት/ቤት 9ኛና 10ኛ ያስተምራል።

በዚህ መሠረት ሁሉም መ/ራን ከዕድሜ፣ ካላቸው ልምድና ከተማሪ መጽሐፉ ጋር ካላቸው ቅርበት የተነሳ የሰጡት ምላሽ ከስሜታዊነትና ከግዴለሽነት ነፃ እንደሚሆን ሊታመን ይችላል።

## ሠንጠረዥ 8፡-የክፍል ሁለት ጥያቄ መልሶች ትንተና

ሠንጠረዥ 8 (አባሪ 4 ይመልከቱ) የያዘው መረጃ የሚያመለክተው በክፍል ሁለት ለመ/ራን ቀርበው የነበሩ ጥያቄዎች ምላሽ የተተነተነበት መረጃ ነው። የመጀመሪያው ጥያቄ የጥናቱ አካል ባይሆንም ተገቢ ጥያቄ ስለሆነ ተካቷል። ሁሉም መላሾች ከመምህሩ መምሪያ ቀጥሎ ባለው የ8ኛ ክፍል አዲሱ መርሀ ትምህርት ውስጥ በአላማነት የተጠቆሙ ሀሳቦች ከግብ እንዲደርሱ የሚያስችሉ መልመጃዎች ቀርበዋል በሚል የጽሑፍ መጠይቁን የሞሉ ዘጠኙም መምህራን (100%) ያስችላሉ በሚል ተስማምተዋል። ስለሆነም ሁለተኛውን ጥያቄ የሚመልስ መላሽ አልተገኘም።

ጥያቄ ቁጥር ሦስት የያዘው የንግግርና የጽህፈት መልመጃዎች ሲመረጡ መምረጫ መስፈርቶችን መከተል ግዴታ ነው። ለመ/ራኑ ስድስት የይዘት መምረጫ መስፈርቶች ቀርበው ለስድስቱም የየራሳቸውን ግንዛቤ በሚያሳይ መልኩ የሰጡት መልስ እንደሚከተለው ተተንትኖ ቀርቧል።

ከቀረቡት ስድስት የይዘት መምረጫ መስፈርቶች መካከል ተገቢነት፣ አስፈላጊነትና ወቅታዊነት በሚሉ መስፈርቶች አንፃር ተመርጠው ለትምህርትነት የቀረቡት ይዘቶች ተገቢ፣ ወቅታዊና

አስፈላጊ መሆናቸውን ሁሉም መላሾች፣ ዘጠኙም "ከፍተኛ ነው" በማለት መልሰዋል። ይህም 100% መሆኑ ነው።

ሌላው የይዘት መምረጫ መስፈርት ዘላቂነት ነው። በዚህ ዙሪያ አንዱ መ/ር ብቻ ዘላቂነትን መካከለኛ ነው በሚል መልስ ሰጥቷል። ይህም በመቶኛ 11.2% መሆኑ ነው። የቀሩት 8 መምህራን "ከፍተኛ ነው" የሚል መርጠዋል። ይህም በመቶኛ 88.8% ነው። አጥኚው ከዘላቂነት መስፈርት አንፃር መላሾቹን ከመረጃው ግኝት በኋላ በአካል አግኝቶ ሁለት መምህራንን ለምን ከፍተኛ ነው ብለው እንደመለሱ ሲጠየቁ "መልመጃዎቹ ፓለቲካ፣ ሃይማኖት፣ ብሄር፣ …" ያልደሰሱ ነፃ ስለሆኑ በጊዜ የማይወሰኑና የመዝለቅ አቅማቸው ከፍተኛ እንደሆነ ተናግረዋል።

ሌላው ትንተና "አስደሳችነትን" የሚመለከት ነው። መልመጃዎቹ አስደሳች ከመሆን አንፃር መጠይቅ ከቀረበላቸው ዘጠኝ መላሶች መካከል 5 መ/ራን ማለትም 55.5% "አስደሳችነቱ ከፍተኛ ነው" ብለው ሲመልሱ የቀሩት አራት መምህራን ማለትም 44.5% አስደሳችነቱን መካከለኛ ነው ብለው መልሰዋል። ይህ የሚያሳየው የተመረጡት መልመጃዎች ከአስደሳችነት አንፃር የሚቀራቸው ነገር እንዳለ ነው።

ለመማር ካላቸው አመቺነት መስፈርት 7 መምህራን መልመጃዎቹ ለመማር አመቺ ናቸው ብለዋል። ይህም ከመቶ 77.7% ሲሆን የቀሩት ሁለት መምህራን ደግሞ አመቺነቱ መካከለኛ ነው። የሚቀረው ነገር አለ በሚል መልሰዋል። መካከለኛ የሚለው ሀሳብ 22.3% ከመቶውን የሸፈነ ነው። በአማዛኙ አመቺ ናቸው የሚለው በሰፊ ርቀት የሚበልጥ ስለሆነ አመቺነቱ የጎላ ነው ማለት ይቻላል።

ለመምህራኑ ከቀረቡት ጥያቄዎች አራተኛው የይዘትና መልመጃዎች አደረጃጀት መስፈርቶችን የሚመለከት ነው። ለመምህራኑ ተከታታይነት፣ ተለጣጣቂነትና ውህደት/ቅንጂት የተሰኙ የአደረጃጀቶች መስፈርቶች የቀረቡ ሲሆን መ/ራኑ ውህደትን ከምርጫቸው ውጭ አድርገዋል። ምክንያታቸው ከሌሎች የትምህርት አይነቶችና የክፍል ደረጃዎች ጋር ያለውን ግንኙነት የሚፈልግ ስለሆነ ይህን ለማድረግ ካለው የጊዜ ማነስ የተነሳ መሆኑን ገልፀዋል።

መምህራኑ "ተከታታይነትን" በሚመለከት ባልተለያየ ምላሽ ሁሉም መምህራን 100% ተከታታይነት አለው ብለው መልሰዋል። "ከፍተኛ ነው" የሚለውን ምላሽ በመምረጥም አረጋግጠዋል። የተለጣጣቂነት የአደረጃጀት መስፈርት በሚመለከት ግን 5 መ/ራን በመቶኛ

ሲሰላ 55.6% ተለጣጣቂነቱ ከፍተኛ ነው ብለው መልሰዋል፡፡ የቀሩት አራት መምህራን ደግሞ ተለጣጣቂነቱ የሚጎድለውን ነገር አለ ስለዚህ “መካከለኛ ነው” የሚለውን መርጠዋል፡፡ ይህም በመቶኛ ሲሰላ 44.4% መሆኑ ነው፡፡ በዚህ መሠረት የ8ኛ ክፍል አዲሱ መጽሐፍ ከያዛቸው ከንግግርና ከጽህፈት መልመጃዎች ተለጣጣቂነት አንፃር መሻሻል ያለበት ነገር መኖሩን ያሳያል፡፡

ጥያቄ አምስት የነበረው ዝግጅቶቹ የተማሪውን የቋንቋ ዕውቀት ዳራ የሚጠይቅ ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ ዘጠኙ መምህራን 100% ተመሳሳይ መልስ “የጽህፈትና የንግግር ክሂሎች የተማሪውን የቀደመ ዕውቀት፣ የዕውቀት ዳራ ታሳቢ ያደረጉ በመሆን ተማሪውን ይመጥናሉ” የሚለውን ሀሳብ መርጠዋል፡፡ ይህም ማለት የክብደት ደረጃው ከመጨመሩና ከመስፈርቱ ውጪ በቀደመው ክፍል በትንሹ ያገኙትን በዚህኛ ክፍል በስፋት ያገኛሉ ስለዚህም ጥሩ ዝግጅት ነው ማለት ነው፡፡

6ኛ ጥያቄ፣ ጥያቄ አምስት “ከፍተኛ ነው” የሚል ምላሽ ባያገኝ የሚመለስ ነው፡፡ ጥያቄ አምስት “ከፍተኛ ነው” የሚል ምላሽ ስላገኘ አልተመለሰም፡፡

7ኛው ጥያቄ ለክሂሎች የተሰጠው ትኩረት ተመጣጣኝ መሆን አለመሆኑን ለማወቅ የቀረበ ጥያቄ ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ከሰጡ ዘጠኝ መምህራን መካከል ሰባቱ ማለትም 77.8% “መካከለኛ ነው” የሚለውን መርጠዋል፡፡ ሁለቱ መምህራን ብቻ “ከፍተኛ ነው” የሚለውን መርጠዋል፡፡ በርካታ መምህራን “መካከለኛ ነው” የሚለውን የመረጡበት ምክንያት ሲፈተሽ በጥናቱ ውስጥ በሰነድ ምርመራ ላይ ከ90 ትምህርቶች መካከል 30 የሚሆኑት ማለትም 33.3% በንግግር ክሂል ተሸፍነዋል፡፡ ሌሎቹ ስድስት የይዘት ወይም የመልመጃ አይነቶች 66.7% ብቻ ይዘዋል፡፡ ተመጣጣኝ እንዳይሆኑ ያደረገው ይህ ነው፡፡ ይህ ትንታኔ የሚጠቁመው ለይዘቶችና የመልመጃ አይነቶች በአንፃራዊነት ተመጣጣኝ ትኩረት ተሰጥቶ መሰራጨት ስለነበረባቸው የሚሻሻሉ ጉዳዮች መኖራቸውን ያሳያል፡፡ እዚህ ላይ አዲሱ በደቡብ ክልል ትምህርት ቢሮ የተዘጋጀው መጽሐፍ አማርኛ በ2ኛ ቋንቋቸው ለሆኑ ተማሪዎች የተዘጋጀ እንደመሆኑ መጠን ሁሉም ይዘቶች ለተማሪዎቹ አዲስ ናቸው፤ ከክፍል ውጭ ያለው ለይዘቶቹ የሚያቀርበው ተጋልጦ በጣም አነስተኛ ስለሆኑ ሁሉም በክፍል ውስጥ መጠናከር አለባቸው፡፡

የክፍል ሦስት ጥያቄዎች ክፍት ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ በመምህራኑ የተመለሱት ምላሾች የዝግ ያህል ተቀራራቢ ሆነዋል፡፡ ለምሳሌ ለመጀመሪያ የመ/ራንን አመለካከት የሚጠይቅ ጥያቄ “አዲሱ የ8ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ የአፍልቆት ክሂሎችን በተመለከተ የተዘጋጁ

መልመጃዎች አደረጃጀትና አቀራረብ ከቀደመው የክፍሉ መጽሐፍ አሻሽሎታል የሚሉት ነገር ካለ ቢገልጹልኝ፡፡" የሚል ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ የተሰጠው ምላሽ ተሰብስቦ አማካዩ ሲታይ የሚከተለው አይነት ነው፡፡

"የቀደመው መጽሐፍ የይዘት መዘበራረቅ ይታይበት ነበር፡፡ ይዘቶች በስፋት ቅደምተከተል ቃላት፣ ሀረጋት፣ ዐረፍተ ነገሮች… ቅደምተከተል ይዘው አልነበረም የተደራጁት፡፡ በአዲሱ ይህ ችግር ከሞላ ጎደል መቀረፉን የሚያሳይ መረጃ ተገኝቷል፡፡ ሌላው የይዘት መታጨቅ ችግር ነበረበት፤ ለመምከር ምንም ጊዜ የማይሰጥ ዝግጅት ነበር፡፡ አሁን ያለው ይዘቱ ክፍተት የሰጠ፣ አንዱን ይዘት ለመምህር ከማሳየት በፊት የመምከሪያ ጊዜ ያዘጋጀ ዝግጅት ነው፡፡" የሚል ነው፡፡ ስለዚህ ለጥያቄ 1 የተሰጠው ምላሽ አበረታች ነው፡፡ ጥያቄ ሁለት "ስለአፍልቆት ክሂሎች መልመጃዎች አመራረጥም ሆነ አደረጃጀት ያለዎትን ተጨማሪ አስተያየት ቢገልጹልኝ፡፡" ለሚል ጥያቄ ከአመራረጥ ይልቅ አደረጃጀት ላይ ትኩረት በማድረግ ከላይ በክፍል ሁለት አራተኛ ጥያቄ ላይ የመለሱትን ምላሽ እንደሚከተለው አብዛኞቹ ደግመው አስቀምጠዋል፡፡

"መጽሐፉ ለአፍልቆት ክሂሎች ልዩ ትኩረት ሰጥቷል፡፡ ከ90 ትምህርቶች ከግማሽ በላይ በአፍልቆት ክሂሎች ተሸፍኗል፡፡ 30 የንግግር ትምህርቶችና 16 የጽህፈት ትምህርቶች በድምሩ 46 ትምህርቶችን አፍልቆት ሸፍኗል፡፡ ይህም ተመጣጣኝ ስፋት ከመያዝ አንፃር የጎደለው ነገር እንዳለ ያሳያል፡፡ ሁሉም ክሂሎችና የዕውቀት ዘርፎች ቃላትና ሰዋሰውን ጨምሮ ተመጣጣኝ ትኩረት መስጠት ነበረበት" ብለው መልሰዋል፡፡ ስለዚህ ከዚህ አንፃር በዝግጅቱ መሻሻል የሚፈልግ ነገር አለ ማለት ነው፡፡

## 4.2 የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ዋነኛ አላማ በ2015 ዓ.ም አዲስ ወደ ትግበራ የገባው የ8ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ለትምህርትነት የተካተቱት የአፍልቆት ክሂሎችን ለማዳበር የቀረቡ መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት መፈተሽ ነው፡፡ ዝርዝር አላማዎቹም በመጽሐፉ ውስጥ ለአፍልቆት ክሂሎች የተሰጠውን ሽፋን መፈተሽ፣ የየምዕራፉ የንግግርና የጽህፈት መልመጃዎች አቀራረብ ደረጃውን የጠበቀ አደረጃጀት መከተል አለመከተሉን ማረጋገጥ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የታዩ ክፍተቶችን በመቀመር ለአዘጋጆች የማስተካከያ አስተያየት ለመስጠት ነው፡፡ ለጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያነት የተማሪው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያለውን የአፍልቆት ክሂሎችን አደረጃጀት በመመርመር መፈተሽና ለዘጠኝ መምህራን የጽሑፍ መጠይቅ በማቅረብ

ነው፡፡ ይህም መረጃው በዋናነት ከሰነድ ፍተሻ የተገኘ ነው፡፡ በደጋፊነት ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች በቅይጥ የመረጃ አተናተን (በዋናነት ለአይነታዊ በደጋፊነት ደግሞ በመጠነዊ) ስልት ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

በመጀመሪያ ከተተነተነው መረዳት እንደተቻለው የቋንቋ ትምህርት ተፈጥሮኣዊውን የቋንቋ ለመዳ ወይም ተጋልጦ ሂደትን መከተል እንዳለበት ይታመናል፡፡ የሰው ልጅ ቋንቋን የሚጀምራው በማዳመጥ፣ በመናገር፣ በማንበብ፣ በመፃፍ እያለ ይቀጥላል፡፡ ይህ አካሄድ በአብዛኞቹ ምዕራፎች ትክክለኛውን ሂደት ይዞ ቀጥሏል፡፡ ይህ ተፈጥሮኣዊው ቅደም ተከተል የተፋለሰው በአንድ ምዕራፍ ብቻ ነው፡፡ ምዕራፍ ሰባት በንባብ በመጀመር አካሄዱን አፋልሷል፡፡

ሌላውና በዋናነት የተተኮረበት ጥናቱ ውጤቱን በደንብ የሚፈልገው ለመልመጃዎቹ አቀራረብ የተሰጠውን ትኩረት መፈተሽ ነው፡፡ ጥናቱ ይህን ዓላማ በትክክል መልሷል፡፡ ለሁለቱም ክሂል መልመጃዎች የተሰጠው ትኩረት ከሰነድ ፍተሻውና ለመምህራን ከቀረባቸው የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች እንደሚያሳዩት በንግግር ክሂል ከተገቢው በላይ ትኩረት ተሰጥቶታል፡፡ ከ90 ትምህርቶች መካከል 30 ትምህርቶች የንግግር ክሂል መልመጃዎችን ይዘዋል፡፡ ይህ ከአጠቃላይ 33.3% መሆኑ ነው፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን የንግግርና የጽህፈት ክሂሎች በየምዕራፉ ያላቸው ሥርጭት ተመጣጣኝ አይደለም፡፡ ለምሳሌ የጽህፈት ክሂል መልመጃዎች ከአስር ምዕራፎች መካከል በአስረኛው ምዕራፍ ውስጥ ግን ጽህፈት አልቀረበም፡፡ በስድስት ምዕራፎች ሁለት ሁለት ትምህርቶች የቀረቡ ሲሆን በሶስቱ ምዕራፎች በአንድ አንድ ትምህርቶች ተወክሏል፡፡ አንድም ትምህርት ጽህፈትን ያለማቅረብ በራሱ ችግር ነው፡፡ የንግግር ክሂል መልመጃዎች አደረጃጀት ደግሞ ከፍተኛ ችግር ያለበት ነው፡፡ ለምሳሌ ጽህፈት ባልቀረበበት ምዕራፍ አሥር ከአስር ትምህርቶች ስምንቱ ንግግርን ይመለከታል፡፡ በምዕራፍ ሰባት በስድስት ትምህርቶች፣ በምዕራፍ ሦስት በአምስት ትምህርቶች ተወክሏል፡፡ በዚህ መሠረት ከሰላሳ የንግግር መልመጃዎች መካከል አስራ ዘጠኝ መልመጃዎች በሦስት ምዕራፎች ውስጥ ብቻ ታጭቀዋል፡፡

የንግግር መልመጃዎች ሥርጭት በጠቅላላው ፍትሃዊ አይደለም፡፡ ፍትሃዊ ያለመሆኑ በሁለት መንገድ ይታያል፡፡ አንደኛ ከጠቅላላ መልመጃዎች 33.3% መሸፈንና ሁለተኛ ሰላሰዎቹ የንግግር መልመጃዎች በመጽሐፉ ውስጥ በጥቂት ምዕራፎች ውስጥ መታጨቃቸው ነው፡፡

በተለይ የአደረጃጀትና አቀራረብ መስፈርቶችን ከመጠበቅ አንፃር ከመ/ራን ከቀረቡት የጽሑፍ መጠይቆች የተሰባሰበው መረጃ የሚያሳየው የይዘቶቹ አደረጃጀት የተከታታይነትን መርህ

የተከተለ ነው። በይዘት መታጨቅን ከግምት ውስጥ ሳያስገባ በይዘቱ ደረጃ ዝግጅቱ የተማሪዎችን የቀደመ ዕውቀት ከግምት ውስጥ ያስገባ ነው። በሁለቱም ይዘቶች ሁለት ተከታታይ ትምህርቶች በአንድ መልመጃ ሲያዙ አንዱን ለመለማመጃ አንዱ ለትግበራ የሚታረም፣ ለክፍል፣ ለቡድን ወይም ለመ/ር የሚቀርብ ሥራ በመስራት ጥቅም ላይ ውሏል።

የተለጣጣቂነትን መስፈርት በተመለከተ ከመ/ራን የተገኘውና ከሰነድ ፍተሻው የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው መጽሐፉ ክፍተት ያለበት መሆኑን ማየት ይቻላል። Raid (1993፣ 86) "በጽህፈት ክሂል ረገድ ከቃላት ወደ ሀረጋት፣ ከዚያም ወደ አረፍተ ነገሮችና አንቀጾች ምስረታ ደረጃ በደረጃ መሸጋገር የተለጣጣቂነትን መስፈርት የሚያሳይ አደረጃጀት ነው" ይላሉ። በዚህ መጽሐፍ ግን ወጣ ገባ አካሄድ ታይቷል። በንግግር ክሂል መልመጃዎች አደረጃጀቶች ክፍተቶቹ በስፋት ያልታዩ ሲሆን በጽህፈት መልመጃዎች ላይ ግን ታይቷል።

በመጀመሪያው ምዕራፍ "ገጠመኛችሁን በአንድ አንቀጽ ፃፉ" የሚል መልመጃ አለ። አረፍተ ነገር መፃፍ መቅደም ነበረበት። በምዕራፍ ዘጠኝ ግን "አያያዦችን በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን መስርቱ።" የሚል መልመጃ ይገኛል። እንደ አጥኚ ምዕራፎቹ ቦታ የተቀያየሩ ይመስላል። ይህ የተለጣጣቂነት ችግር ከታዩ የመጽሐፉ የአደረጃጀት ችግሮች መካከል አንዱና መሻሻል ያለበት ነው።

ባጠቃላይ ይህ ጥናት ይዞት የተነሳውን ዓላማ የሁለቱንም ይዘቶች ማለትም የንግግርና የጽህፈት ክሂል ይዘቶችን በመፈተሽ ከተከታታይነት አንፃር ያላቸውን ጠንካራ ጎን፣ ከተለጣጣቂነት አንፃር ያላቸውን ደካማ ጎንና ከአጠቃላይ ይዘቶች ሥርጭት አንፃር የአፍልቆት ክሂሎች በክሂል ደረጃ ልዩ ትኩረት የተሰጣቸው ቢሆንም ይዘቶችን በማመጣጠን ሚዛናዊ ከማድረግ አንፃር በጣም የሰፋ ክፍተት ያለው ዝግጅት መሆኑ ታይቷል። የውጤት ማብራሪያውም በምዕራፍ ሁለት የተገለጹትን የምሁራን ንድፈ ሀሳቦች መሠረት በማድረግ የታዩትን ጥንካሬዎችና ክፍተቶች አስቀምጧል።

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያና አስተያየት

## 5.1. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት አላማ አድርጐ የተነሳው አዲስ በ2015 ዓ.ም ወደ መደበኛ ትግበራ በገባው የ8ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በትምህርትነት የተካተቱ የመናገርና የመፃፍ ክሂሎችን ለማዳበር የተዘጋጁትን መልመጃዎች አደረጃጀትና አቀራረብ መፈተሽ ነው። ይህ ዋና ዓላማ ሦስት ዝርዝር አላማዎች አሉት። እነዚህም የመጀመሪያው በመጽሐፉ ውስጥ ለአፍልቆት ክሂሎች የተሰጠውን አጠቃላይ ሽፋን መፈተሽ፣ ሁለተኛው የየምዕራፉ የንግግርና የጽህፈት መልመጃዎች አቀራረብ ደረጃውን የጠበቀ አደረጃጀት መከተል አለመከተላቸውን ማረጋገጥና የመጨረሻው በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የታዩ ክፍተቶችን በመቀመር ለአዘጋጆች የማስተካከያ አስተያየት መስጠት የሚሉ ናቸው።

ይህን ጥናት ከግብ ያደርሳሉ ተብለው ተመርጠው መረጃ የተሰበሰበባቸው መረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ሁለት ናቸው። እነዚህም በመጽሐፉ ውስጥ ተዘጋጅተው የቀረቡ ክሂሎችን መፈተሻ (ሰነድ ፍታሻ) አንደኛው ሲሆን ሁለተኛው ለመምህራን የቀረበ የጽሑፍ መጠይቅ ነው። ከሁለቱም የመረጃ ምንጮች የተሰባሰቡት መረጃዎች በዋናነት በአይነታዊ፣ በደጋፊነት በመጠናዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ (በቅይጥ ዘዴ) መረጃው ተተንትኖ ቀርቧል።

የመረጃ ትንተናው የተለያዩ ጠንካራና ደካማ ጐኖች በመጽሐፉ የአፍልቆት ክሂሎች ላይ እንዳሉ አሳይቷል። ከነዚህም መካከል በጠንካራ የተለዩ ጉዳዮች፡-

- ❖ የመልመጃዎቹ አደረጃጀት በአብዛኛው ተፈጥሮአዊውን የቋንቋ ለመዳ አካሄድ ተከትሎ ለመዘጋጀት ጥረት የተደረገ መሆኑ፣
- ❖ የመልመጃዎችን የአደረጃጀት መርህ በተለይ ከተከታታይነት መርህ አንፃር ይዘቶች ተደጋግመው መቅረባቸው፣
- ❖ ለተማሪዎች ለጽህፈትም ሆነ ለንግግር በቂ የልምምድ ጊዜ የተሰጣ መሆኑ፣
- ❖ ከጽህፈት መልመጃ በቀር የንግግር መልመጃ በሁሉም ምዕራፎች ሥርጭት ይዞ መገኘቱ፣

- የይዘትና መልመጃ አመራረጥ መስፈርቶችን የሚያሟሉ ይዘቶች ተመርጠው ለትግበራ መቅረባቸው የመሳሳሉት ይገኙበታል፡፡

ጥናቱ በክፍተትነት የያዛቸው ጉዳዮችም አሉ፡፡ የክፍተቶቹ ትኩረት አጠቃላይ ይዘት ባጠቃላይ፣ የጽህፈትና የንግግር ክሂሎችን በተለይ የያዘ ነው፡፡ በደካማነት የተያዙ ጉዳዩች፡-

- የይዘት ሥርጭት በምዕራፍ መካከል የሚያሳየው ከፍተኛ ክፍተት ኢ-ፍትሃዊ ሥርጭት እንዳለ ማሳየቱ፡- ለምሳሌ ምዕራፍ አንድ ውስጥ አምስት ትምህርቶች ብቻ ያሉ ሲሆን በምዕራፍ ሦስትና በምዕራፍ ሰባት ደግሞ አስራ ሁለት ትምህርቶች ይገኛሉ፡፡ ይህም ተመጣጣኝ ሥርጭት አለመኖርን ያሳያል፡፡

- ለንግግር ክሂል የተሰጠው ትኩረት ከሚገባው በላይ የተለጠጠ መሆን፣ በአጠቃላይ በመጽሐፉ ውስጥ ዘጠና ትምህርቶች ያሉ ሲሆን የንግግር ክሂል ብቻውን 30 ትምህርቶችን ሸፍኗል፡፡ ከአጠቃላይ መጽሐፉ $^{1}/_{3}$ኛው ንግግር ነው፡፡ በመቶኛ ሲሰላ 33.3% መሆኑ ነው፡፡ ዝግጅቱ በሁለተኛ ቋንቋነት የተዘጋጀ እንደመሆኑ መጠን ለሁሉም ክሂሎች ተመጣጣኝ ትኩረት መሰጠት ነበረበት፡፡ ይህ የዝግጅቱ ሰፊው ክፍተት ነው፡፡

- በተለይ የጽህፈት መልመጃዎች የተለጣጣቂነትን መርህ በስፋት ያለመከተል ችግር ታይቷል፡፡ በምዕራፍ አንድ አንቀጽ ፃፉ ይልና በምዕራፍ ዘጠኝ አረፍተ ነገር መስርቱ የሚል ቀርቧል፡፡ መሃል ላይ ያለውም ተመሳሳይ ወደኂላና ወደፊት መመላለስ አለ፡፡ ይህም ከክፍተቶች መካከል የሚቆጠር ነው፡፡

- አንዳንድ ምዕራፎች በውስን ክሂል መልመጃዎች መታጨቅ ታይቷል፡፡ ለምሳሌ በምዕራፍ አስር ካሉት 9 ትምህርቶች ስምንቱ የንግግር መልመጃዎችን ብቻ የያዙ ሲሆን አንድ ትምህርት ብቻ በማዳመጥ ተሸፍኗል፡፡

- የጽህፈት መልመጃ ሥርጭት ከሌሎቹ በተለየ የተሻለ ፍትሃዊ ሥርጭት ያለው ቢሆንም በምዕራፍ አስር አንድም የፅህፈት መልመጃ አለመኖር የሚሉ ይገኙበታል፡፡

## 5.2. አስተያየት

ይህ የንግግርና የጽህፈት ክሂል መልመጃዎችን ትኩረት አድርጐ የተነሳው ጥናት የተነሰበትን አላማ አሳክቷል፡፡ ዓላማው የሁለቱንም ክሂሎች መልመጃዎች አደረጃጀትና አቀራረብ መፈተሽ እንደመሆኑ መጠን በሰፊ ዝርዝር ትንተናዎች አደረጃጀትና አቀራረቦችን በመፈተሽ ደካማ እና ጠንካራ ጎኖቹን አሳይቷል፡፡ በዚህ መሠረት የክፍሉ መምህራንና የትምህርት ባለሙያዎች ጠንካራ ጎኖቹን ይበልጥ በማጐልበት፣ ደካማ ጎኖቹን በማሻሻል እንዲጠቀሙ የሚያሳዩ አስተያየቶችን አጥኚው ሰንዝሯል፡፡ ወደፊት መጽሐፉ ሲሻሻልም ክፍተቶቹ ከግምት መግባት እንደሚገባቸው አጥኚው የመፍትሄ ሀሳብ ይጠቀማል፡፡

- ❖ መልመጃዎቹ ተከትለው የያዙትን ተፈጥሮአዊ የቋንቋ ለመዳ ቅደምተከተል የተከታታይነት መርህ እንደጠበቁ ለትምህርትነት ማቅረቡ ተጠናክሮ ቢቀጥል፣
- ❖ የመጽሐፉ ዝግጅት አንዱን ክፍል ለልምምድ ሌላውን ለውጤት እየሰጣ የተዘጋጀው ከይዘት ተከታታይነት መርህ አንፃር ለተማሪዎች ሌላ የጥንካሬ አቅም የሚሆን ስለሆነ መ/ራን ሳያሸራርፉ አጠናክረው ቢቀጥሉ፣
- ❖ ይዘቶችና መልመጃዎቹ ከይዘት ምርጫ መስፈርቶች አንፃር በጣም ጥሩ በሆነ መንገድ ለክፍሉ በሚመጥን ሁኔታ የተዘጋጁ ስለሆኑ የሚመለከታቸው አካላት በተለይ መምህራኑ የጐደሉትን ወቅታዊ መልመጃዎች በመጨመር ቢጠቀሙ የሚሉ አስተያየቶች ይገኙበታል፡፡

የታዩ ክፍተትና ደካማ ጐኖችን ከማስተካከል አንፃር መጽሐፉ አዲስ በ2015 ዓ.ም ወደ ትግበራ የገባ ስለሆነ በተለይ መ/ራን ክፍተቶቹን በማየት የማስተካከያ እርምጃ ትምህርቱን ለማስተማር ሲዘጋጁም ሆነ ሲተገብሩ እንዲወስዱ በመጠየቅ በክፍተትነት ተይዘው መሻሻል የሚገባቸውን ነጥቦች በሚከተለው መልኩ አቅርቧል፡፡

- ❖ የአጠቃላይ ይዘቶች ሥርጭት በምዕራፎች መካከል ከፍተኛ ልዩነት የሚያሳዩ ስለሆነ ቢስተካከል፣
- ❖ የንግግር ክሂል ከሚገባው በላይ በመልመጃዎች የታጨቀ፣ ለሌሎች ይዘት መልመጃዎች ውስን መሆን ለምሳሌ ሥነ-ጽሑፍ በአንድ ትምህርት ብቻ መወሰን

ወዘተ… ምክንያቱ የንግግር መልመጃዎች የሌሎቹን ቦታ መሸፈን ስለሆነ የማሻሻያ እርምጃ ቢወሰድ፣

- ❖ ከተለጣጣቂነት አንፃር የጽህፈት ክሂል በቀደመ ዕውቀት ላይ ያለመመስረትና አንቀጽን አስቀድሞ በማቅረብ ዐረፍተ ነገርን ማስቀጠል የተለጣጣቂነትን መርህ የሚያፋልስ ስለሆነ ቢሻሻል፣
- ❖ በውስን ክሂል መልመጃዎች የታጨቁ ምዕራፎች ተማሪዎችን የሚያሰለቹ እንዳይሆኑ በመምህራኑ ሌሎች ክሂሎች የሚተኩበት ሁኔታ ቢመቻች፣
- ❖ የጽህፈት ክሂል በሌለበት አስረኛው ምዕራፍ መምህራን የራሳቸውን ፈጠራ በመጠቀም የጽህፈት መልመጃ ቢያዘጋጁ የሚሉ ናቸው፡፡

ባጠቃላይ በጠንካራ ጐንነት የተያዙ ጉዳዮች ተጠናክረው እንዲቀጥሉና በክፍተትነት የተያዙ ጉዳዮች ልዩ ትኩረት ተሰጥቷቸው በተለይ በክፍሉ መምህራን አማካይነት የማሻሻያና የማስተካከያ ሥራ ቢሰራ የሚል አስተያየት በመስጠት አጥኚው ጥናቱን አጠናቋል፡፡

# ዋቤ መፃህፍት


ማረው ዓለሙ፡፡ (1966)፣ በሳል ድርሰት ማስተማሪያ፡፡ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

ራሄል ቶላ (2010) ፣ ረጅም ልቦለድ የመፃፍ ክሂልን ለማዳበር ያለው ሚና፡፡ በጉለሌ ክፍለ ከተማ፣ በየካቲት 12 መሰናዶ ት/ቤት የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ሙካራዊ ጥናት ለማስተርስ ድግሪ ማሟያ የቀረበ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)፡፡

ሰለሞን ገብሩ (2010)፣ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ በአራት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባባር ግምገማ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)

በድሉ ዋቅጅራ (1996)፡፡ በስነ ጽሑፍ ቋንቋን ማስተማር፡፡ አዲስ አበባ፡፡

---------- (2007)፡፡ በስነጽሑፍ ቋንቋን ማስተማር፡፡ ፋር እሳት ትሬድንግ ሀ.የተ.የግል ማህበር

ባየ ይማም (2009፣ የአማርኛ ሰዋሰው፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ማተሚያ ቤት፡፡

ተመስገን ፈቃደ (2001)፣ የ11ኛ ክፍል መምህራን የጽሀፈት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ እና የተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ብልሃት ተዛምዶ፣ የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር ኤም.ኤ ድግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)፡፡

ተስፋዬ ሸዋዬ (1981)፣ ስነልሳንና ቋንቋን ማስተማር፣ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)፡፡

ተስፋዬ አበራ (1980) በሳል ድርሰት ማስተማሪያ ጸሑፍ፡፡ ባህር ዳር አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ባህር ዳር መምህራን ኮሌጅ (ያልታተመ)፡፡

አለም እሼቱ (1997)፣ መሠረታዊ የምርምርና ዘገባ አፃፃፍ፣ አዲስ አበባ፡፡

አዘነ ደምሴ (2013)፣ የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመናገር ክሂል መልመጃዎች የክፍል ውስጥ አተገባባር ፍተሻ፣ በአማራ ክልል በሰሜን ሸዋ ዞን በምረትና ጅሩ ወረዳ በተመረጡ ሦስት ትምህርት ቤቶች (የመንግስት) ማሳያነት፡፡ ደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)፡፡

አያልሰው ይታየው (2003)፣ ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ባሉ በአማርኛ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ በሚገኙ የልቦለድ ምንባቦች ስር የሚቀርቡ የመናገር ክሂል ይዘቶች አቀራረብ ትንተናና ግምገማ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)፡፡

እጅጉ ይማም (2003)፣ በደብረ ብርሃን ከተማ በተመረጡ ሦስት ትምህርት ቤቶች የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል አቀራረብ ግምገማ፣ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የተዘጋጀ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)፡፡

ውዳዲስ ምህረቱ (2001)፣ አማርኛ ቋንቋ በማስተማር ሂደት መ/ራን ለማዳመጥና ለንግግር ክሂሎች የሚሰጡት ትኩረት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለድህረ ምረቃ ትምህርት የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ (ያልታተመ)፡፡

ያለው እንዳወቅ (2009) የምርምር መሠረታዊ መርሆዎችና አተገባበር

ጌታቸው በለጠ (2004)፣ የጥበባት ጉባኤ፡፡ አዲስ አበባ፣ አስቴር ነጋ አሳታሚ ድርጅት

Brown G.and George Y. (1983) Teaching Spoken Language Cabridge, Cabrdge Universty.

Brown, D. (2007) Principles of Language Learning and teaching. USA, Lang Man Publishing.

Bygote M. (1987) Speaking. Oxford, Oxford Univeristy press.

Byren. (1987). Teaching for class room integration. Landon, Longman.

Byrne (1987) Teaching for classroom interaction. London, Longman. Group UK Limited.

------- (1988) Teaching writing skills. Lngman, Longman press.

Garinger, D. (2002) Text book selection for the ESL classroom ERIC Digest

Grant, N. (1987) Making the most of your text-New Yourk Langman INC.

Gower, R, Phillips, D and Walfers S. (1995) Teaching Practrce and look. Oxford, Heinemann.

Harmar (1991) the Practice of English Language Teaching. London, Longman press.

Heaton.J.(1990) Writing English Language Tests. A practice Guide for Teacher for English as 2nd Language 2nd ed. Longman.

Johnson, K. (1981). Introduction, some back ground, some key terms and some diffinitions in Kelth Johnson K Morrow (ed) Communication classroom. London Longman 1-12.

Kyriacou (1998) Essential of Teaching Skills (2nd) London Nelson Thomes Larson freeman.

Lang and Poter (1985) Group work. Inter Language talk and Second Language acqusition. TESOL quarter 1912 207-208.

Nunan (1989) Designing tasks for the communicative classroom Cambridge, Cambridge press.

Raimes (1983) Techiniques of Teaching writing Oxford, Oxford University press.

Rivers, W. (1981) Teaching foreign Language skills (2nd ed) Chicago, Chicago press.

Richards and Rodgers (1989) Interactive Language Teaching Cambridge, Cambridge Press.

Scoot (2005) How to teach speaking. Langman, England.

Trokka (1990) Hand book for writers. Engle wood Cliffs, New jersy prentrce Hall Inc.

Ur. P. (1991) A course in Language teaching practice and theory. Cambridge, Cambridge University press.

Wallace T and et. al (2004) Teaching Speaking, Listening and Writing. Belgium, Brussels. International Burea of Education (IBE).

Widdowson (1992) Skills, abilities and contexts of reality. Annual review of Applied Lingustics. Vol 18 323-333.

# አባሪ 1

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ኘሮግራም በደቡብ ክልል በዱራሜ ከተማ ውስጥ በሚገኙ አራት የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት የ8ኛ ክፍል አማርኛ ለሚያስተምሩ መምህራን የተዘጋጀ የጽሑፍ መጠይቅ ጥያቄዎች

ይህ መጠይቅ አዲስ በደቡብ ክልል ት/ቢሮ ለ8ኛ ክፍል በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የአፍልቆት ክሂሎችን ለማበልፀግ የቀረቡትን መልመጃዎች አደረጃጀትና አቀራረብ ለመረዳትና ለጥናቱ የሚያግዝ መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡

የጥናቱ ዓላማ ከግብ የሚደርሰው ዝግጅቱ የተማሪዎች አጠቃላይ ዳራና የቋንቋ ትምህርት ፍላጐት ከግምት ያስገባ እንደሆነ ነው፡፡ የቋንቋ መምህራንም ሲያስተምሩ ወይም የትምህርት ዝግጅት ሊያደርጉ ያስተዋሏቸውን ክፍተቶች በመያዝ መልመጃዎች ምን መልክ ሊኖራቸው እንደሚገባ ሀሳባቸውን በመሰንዘር ቀና ትብብር ሲያደርጉ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ስለዚህ እርስዎም ይህን መጠይቅ በትዕግሥት እንዲሞልኝ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡ ስለትብብርዎም በቅድሚያ አመሰግናለሁ፡፡

## <u>ክፍል አንድ፡-</u> የመምህራን አጠቃላይ መረጃ

ለሚከተሉት ተገቢ መልስ በመፃፍ ወይም አማራጭ ላላቸው መልሱን የያዘውን ሆሄ በመክበብ ይመልሱ፡፡

1. የመምህሩ ፆታ ________________
2. የመምህሩ ዕድሜ ሀ) ከ20 በታች ለ) ከ20–25 ሐ) ከ25–30 መ) ከ30 በላይ
3. የመምህሩ የትምህርት ደረጃ ሀ) 10+2 ለ) 12+2 ሐ) 12+3 መ) ቢ.ኤ ዲግሪ ሠ) ማስተርስና በላይ ዲግሪ
4. የመምህሩ የአገልግሎት ዘመን ሀ) 0–5 ለ) 6–10 ሐ) 11-20 መ) 21–30 ሠ) ከ30 በላይ

5. በአማርኛ ቋንቋ መምህርነት ያገለገሉበት ዘመን ሀ) 0-10 ለ) 11-20 ሐ) 20-30 መ) ከ30 በላይ

6. አሁን የሚያስተምሩበት የክፍል ደረጃ ሀ) ከ5ኛ --8ኛ ለ) 7ኛ --8ኛ ሐ) 8ኛ መ) 8ኛና በላይ

7. ከአማርኛ ሌላ ሰልጥነው አማርኛ በማስተማር ላይ ካለ የሰለጠኑበትን የትምህርት አይነት ይግለጹ፡፡

## ክፍል ሁለት

ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች መልስ ይሆናሉ ተብለው ከቀረቡት አማራጮች መካከል መርጦ የመልሱን ፊደል በመክበብ ወይም ከመልሱ ትይዩ ባለው ክፍት ቦታ የ "X" ምልክት በማድረግ መልሱ፡፡

1) እንደሚታወቀው በአዲሱ የ8ኛ ክፍል አማርኛ የተማሪው መጽሐፍ ውስጥ የየምዕራፉ ዓላማዎች በዝርዝር ቀርበዋል፡፡ በየምዕራፉ የቀረቡት የንግግርና የጽህፈት ክሂል ይዘቶችና ይዘቶቹን ለማበልፀግ የቀረቡ መልመጃዎች ዓላማውን ከዳር ለማድረስ የሚያስችሉ ይመስልዎታል?

   ሀ) ያስችላሉ ለ) በከፊል ያስችላሉ ሐ) አያስችሉም

2) በተራ ቁጥር አንድ ለቀረበው ጥያቄ መልስዎ "ለ" ወይም "ሐ" ከሆነ ምክንያትዎ የትኛው ነው?

   ሀ) ይዘትና መልመጃዎቹ የተማሪዎቹን ችሎታ አይመጥኑም

   ለ) የይዘትና መልመጃዎቹ አደረጃጀት (ቅደም ተከተል) የተዛባ ነው፡፡

   ሐ) ዓላማና ይዘቶቹ ያልተገናዘቡ ስለሆኑ ነው፡፡

   መ) ሌላ መልስ ካለዎት ይግለፁ

3) የጽህፈትና የንግግር ክሂሎት የይዘት መምረጫ መስፈርቶችን ምን ያህል የጠበቁ ናቸው ብለው ያምናሉ? 3 = ከፍተኛ ነው 2 = መካከለኛ ነው 1 = ዝቅተኛ ነው፡፡

| ተቁ | የይዘት መምረጫ መስፈርቶች | አማራጭ መልሶች | | |
|---|---|---|---|---|
| | | 3 | 2 | 1 |
| ሀ | ተገቢነት | | | |
| ለ | አስፈላጊነት | | | |
| ሐ | ዘላቂነት | | | |
| መ | አስደሳችነት | | | |
| ሠ | ለመማር ያላቸው አመቺነት | | | |
| ረ | ወቅታዊነት | | | |
| ሰ | ሌላ ካለ ይገለጽ | | | |

4) የጽህፈትና የንግግር ክሂል መልመጃዎች የአደረጃጀት መስፈርቶችን ምን ያህል የተጠበቁ ናቸው ብለው ያምናሉ?

3 = ከፍተኛ 2 = መካከለኛ 1 = ዝቅተኛ

| ተቁ | የይዘት አደረጃጀት መስፈርቶች | አማራጭ መልሶች | | |
|---|---|---|---|---|
| | | 3 | 2 | 1 |
| ሀ | ተከታታይነት | | | |
| ለ | ተለጣጣቂነት | | | |
| ሐ | ውህደት | | | |

5) የጽህፈትና የንግግር ክሂል ይዘቶችና መልመጃዎች የተማሪውን የትምህርት ደረጃ የሚመጥኑ ይመስልዎታል?

ሀ) ይመጥናሉ ለ) አይመጥኑም

6) ለጥያቄ አምስት መልስዎ “አይመጥንም” ከሆነ ምክንያትዎ የትኛው ነው?

ሀ) የተማሪውን የቀደመ ችሎታ ስለማያገናዝቡ ለ) የተማሪን ፍላጎት ስላላማከሉ

ሐ) የክሂሎቹን ባህሪያት በመዘንጋቱ መ) የዝግጅቱ መጠን ከተማሪዎች አቅም በላይ ስለሆነ ሠ) ሌላ መልስ ከለዎት ይግለፁ

7) እንደሚታወቀው በመፃህፍት ዝግጅት ወቅት ለአራቱም ክሂሎች ተመጣጣኝ ትኩረት ተሰጥቶ ሊዘጋጁ ይገባል፡፡ ታዲያ አዲስ በተዘጋጀው የ8ኛ ክፍል አማርኛ መጽሐፍ በየምዕራፉ ለክሂሎችና ክሂሎቹን ለማበልፀግ ለተዘጋጁ መልመጃዎች የተሰጠው ትኩረት ተመጣጣኝ ነው ብለው ያምናሉ?

ሀ) አዎን ተመጣጣኝ ነው፡፡ ለ) ተመጣጣኝ አይደለም

8) ለጥያቄ ቁጥር 7 መልስዎ “ለ” ከሆነ ምክንያትዎ የትኛው ነው?

ሀ) ለንግግር ክሂል ከፍተኛ ትኩረት ስለተሰጠ

ለ) ለመፃፍ ክሂል ከፍተኛ ትኩረት ስለተሰጠ

ሐ) ለማንባብ ክሂል ከፍተኛ ትኩረት ስለተሰጠ

መ) ለማዳመጥ ክሂል ከፍተኛ ትኩረት ስለተሰጠ

9) እባክዎ የ8ኛን ጥያቄ ምላሽ መሠረት በማድረግ ከመጽሐፉ ጠቅላል ያለ ዳሰሳ በኋላ የሚከተለውን ሠንጠረዥ በተገቢው ቦታ የ“X” ምልክት በማድረግ ይሙሉ፡፡

| ተቁ | የክሂሉ አይነት | ከሽፋን አንፃር የተሰጠው ትኩረት | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም ከፍተኛ | ከፍተኛ | ዝቅተኛ | በጣም ዝቅተኛ |
| ሀ | ማዳመጥ | | | | |
| ለ | ንግግር | | | | |
| ሐ | ማንባብ | | | | |
| መ | መፃፍ | | | | |

10) የመማሪያ መጽሐፍ አዘጋጅተው ያውቃሉ?

ሀ) አዘጋጅቻለሁ ለ) አላዘጋጀሁም

11) ከአዲሱ የ8ኛ ክፍል አማርኛ መጽሐፍ ዝግጅት በፊትም ሆነ በኋላ በአጋጣም ቢሆን ስለዝግጅቱ አስተያየት የመስጠት ዕድል አግኝተው ያውቃሉ?

ሀ) አግኝቻለሁ ለ) አላገኘሁም

## ክፍል ሦስት

ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ያለዎትን የተብራራ መልስ ፃፉ

1) አዲሱ የ8ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ የአፍልቆት ክሂሎችን በተመለከተ የተዘጋጀ መልመጃዎች አደረጃጀትና የመልመጃዎች አቀራረብ ከቀደመው የክፍሉ መፅሐፍ አሻሽሎታል የሚሉት ነገር ካለ ቢገልጹልኝ፡፡ ______________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

2) ስለ አፍልቆት ክሂሎች መልመጃዎች አመራረጥም ሆነ አደረጃጀት ያለዎትን ተጨማሪ አስተያየት ቢገልጹልኝ፡፡ ______________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

__________________________________________________________________፡፡

አባሪ 2

<u>ሠንጠረዥ 4፡-</u> *የንግግር ትምህርት መልመጃዎች አደረጃጀትና አቀራረብ*

| *ምዕራፍ* | *የንግግር ክሂል ይዘት መልመጃዎች አደረጃጀትና አቀራረብ* |
|---|---|
| 1 | **ትምህርት**.2. በታክስ ጉዳይ ላይ የመምህር ማብራሪያ ካዳመጣችሁ በኋላ … ጥንድ በመሆን ተወያዩ |
| 2 | **<u>ትምህርት 2</u>**. ሚና ጨዋታ<br><br>…. አስቀድማችሁ ያነበባችሁትን የሚና ጨዋታ መሠረት በማድረግ ታሪክ ፈ ጥራችሁ የታካሚው አባት፣ እናት፣ ወንድም ወይም እህት በመሆን ሚና ተጫወቱ፡፡<br><br>**<u>ትምህርት 8</u>** …ዘገባውን ለጓደኛችሁ በንግግር መልክ አቅርቡ<br><br>**<u>ትምህርት 9.</u>** መምህራችሁ በሚነግሯችሁ መሠረት በቡድን በመቀመጥ ልምዳችሁን ተካፈሉ፡፡ |
| 3 | **<u>ትምህርት 2፡</u>** … ከስርዓተ ፆታ አንፃር የአካባቢያችሁ ማህበረሰብ ያለውን የተዛባ አመለካከትና ሚና በቡድን ተወያዩበት፡፡<br><br>**<u>ትምህርት 3፡</u>** … ያደረጋችሁትን ውይይት አጭር ማስታወሻ በመያዝ በንግግር ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡<br><br>**<u>ትምህርት 4፡</u>** ከዚህ በታች የቀረበውን አጭር ታሪክ መነሻ በማድረግ እናንተም በርዕስ ጉዳይ ላይ በአነስተኛ ቡድን በመደራጀት ተከራከሩ፡፡<br><br>**<u>ትምህርት 5፡</u>** በትምህርት አራት ያደረጋችሁትን ክርክር በማስታወስ … ስለመፍትሄው በመነጋገር የደረሳችሁበትን ድምዳሜ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ<br><br>**<u>ትምህርት 7፡</u>** … የሰው ልጆች አቅም የሚለውን ምንባብ ዋና ሀሳብ … ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ፡፡ |
| 4 | **<u>ትምህርት 2፡-</u>** የሚከተሉትን ጥያቄዎች አንብባችሁ ጥንድ ጥንድ በመሆን ተወያዩባቸው |
| 5 | **<u>ትምህርት 2፡-</u>** … የናንተን የህይወት ተሞክሮ በምሳሌው መሠረት ጥንድ ጥንድ |

| | |
|---|---|
| | በመሆን ተነጋገሩ፡፡ |
| 6 | <u>**ትምህርት 2፡-**</u> … ቀጥሎ በቀረበላችሁ ጥያቄ ላይ በመወያየት ንግግር ታደርጋላችሁ፡፡<br><br><u>**ትምህርት 6፡-**</u> የፃፋችሁትን ድርሰት … ገምግሙ፡፡ |
| 7 | <u>**ትምህርት 2፡-**</u> ከዚህ በላይ ካሉት ምስሎች ምን እንደተረዳችሁ ለጓደኞቻችሁ ተናጋሩ፡፡<br><br><u>**ትምህርት 3፡-**</u> ያደረጋችሁትን ውይይት በመከለስ በተወካያችሁ አማካኝነት ለጓደኞቻችሁ ግለጹ፡፡<br><br><u>**ትምህርት 4፡-**</u> በትምህርት ቤታችሁ በጎ አድራጎት ክበብ በሚደረጉ ተግባራት ላይ ተወያዩ፡፡<br><br><u>**ትምህርት 5፡-**</u> … በቡድን ተወካያችሁ አማካኝነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ፡፡<br><br><u>**ትምህርት 7፡-**</u> … በጻፉት አመዛዛኝ ድርሰት አፃፃፍ ሥርኣት ላይ መወያየት<br><br><u>**ትምህርት 10፡-**</u> በልቦለድ ታሪኩ በታዩ አዳዲስ ነገሮች ዙሪያ ተወያዩ |
| 8 | <u>**ትምህርት 2፡-**</u> እናንተና ከዚህ በታች ያሉትን መመሪያዎች ተከትላችሁ ሀሳብ በማፍለቅ በፍጥነት ተናገሩ፡፡ |
| 9 | <u>**ትምህርት 2፡-**</u> ከላይ ስላነበባችሁት ጽሑፍ በግል ካሰላሰላችሁ በኋላ አምስት ሆናችሁ ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ፡፡<br><br>ትምህርት 7፡- ግጥሙ በሚያስተላልፈው መልዕክት ዙሪያ ተወያዩ፡፡ |
| 10 | <u>**ትምህርት 1፡-**</u> በሆነ አጋጣሚ የደረሰባችሁን ችግር ጥንድ ጥንድ በመሆን ተናገሩ፡፡<br><br><u>**ትምህርት 2፡-**</u> … የቀረበውን ሀሳብ ወስዳችሁ ተከራከሩ፡፡<br><br><u>**ትምህርት 3፡-**</u> በትምህርት ሁለት ላይ በተነሳው ሀሳብ ከየቡድኑ የተመረጣችሁ ተወካዮች በሁለት በመከፈል ተከራከሩ፡፡<br><br><u>**ትምህርት 4፡-**</u> … ርዕስ ወስዳችሁ የኮንትሮባንድ ነጋዴ፣ የፖሊስ፣ የፊታሻ፣ የዳኛ ሚና ተጫወቱ፡፡ |

| | |
|---|---|
| | **<u>ትምህርት 5፦</u>** በትምህርት አራት የተለማመዳችሁትን በተማሪዎች ፊት ተጫወቱ፡፡<br><br>**<u>ትምህርት 7፦</u>** የሰበሰባችሁትን ተረት በየቡድናችሁ በተራ አቅርቡ፡፡<br><br>**<u>ትምህርት 8፦</u>** በሚከተሉት ምሳሌያዊ አባባሎች ላይ በጋራ ተወያይታችሁ አባባሎቹን አስረዱ፡፡<br><br>**<u>ትምህርት 9፦</u>** ምሳሌያዊ አነጋገሮችን በመሰብሰብ የተነገሩበትን ሁኔታ በቃል ለጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡ |

## <u>ሠንጠረዥ 6፡-</u> የጽህፈት መልመጃዎች ሥርጭት

| ምዕራፍ | የየምዕራፉ የመፃፍ ክሂል መልመጃዎች ስርጭት |
|---|---|
| 1 | **<u>ትምህርት 4፡-</u>** አረፍተ ነገር መመስረትና አንቀጽ ማዋቀር<br><br>**<u>ትምህርት 5፡-</u>** አንቀጽ መፃፍ "ገጠመኛችሁን በአንድ አንቀጽ ፃፉ፡፡ |
| 2 | **<u>ትምህርት 4፡-</u>** … በቡድን ተወያይታችሁ ምላሻችሁን ፃፉና ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡<br><br>**<u>ትምህርት 7፡-</u>** … የትናንት ወሏችሁን በዘገባ መልክ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡ |
| 3 | **<u>ትምህርት 8፡-</u>** ከዚህ በታች የቀረበውን ማመልከቻ በማድረግ ማመልከቻ መፃፍ ተለማመዱ፡፡<br><br>**<u>ትምህርት 9፡-</u>** የጠፋባችሁን የልደት ካርድ እንዲሰጣችሁ ለቀበሌያችሁ ማመልከቻ ፃፉ፡፡<br><br>የጥሪ ደብዳቤ ፃፉ፡፡ |
| 4 | **<u>ትምህርት 4፡-</u>** የመንገዣ አይነቶች በሚል ርዕስ ተጀምሮ ያልተጠናቀቀውን አንቀጽ ራሳችሁ እየፃፋችሁ አሟሉ፡፡ |
| 5 | **<u>ትምህርት 4፡-</u>** የህይወት ታሪክ መፃፍ<br><br>**<u>ትምህርት 5፡-</u>** በትምህርት አራት የቀረበውን የህይወት ታሪክ መሠረት በማድረግ የህይወት ታሪክ ፃፉ፡፡ |
| 6 | **<u>ትምህርት 4፡-</u>** ቀደም ሲል ባነበባችሁት ተራኪ ድርሰት መሠረት በግል አንድ ተራኪ ድርሰት ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡ |
| 7 | **<u>ትምህርት 6፡-</u>** አመዛዛኝ ድርሰት መፃፍ የአካባቢያችሁን የሥራ ባህል መሠረት በማድረግ አንድ አመዛዛኝ ድርሰት ፃፉ፡፡ |
| 8 | **<u>ትምህርት 6፡-</u>** የጽህፈት ሂደት መመሪያዎችን መሠረት በማድረግ አንድ አንቀጽ ፃፉ፡፡ |

| | |
|---|---|
| 9 | **<u>ትምህርት 3፡-</u>** ቀጥሎ የቀረቡትን አያያዦች ተጠቅማችሁ ዐረፍተ ነገሮቹን አሟልታችሁ ፃፉ፡፡<br><br>**<u>ትምህርት 4፡-</u>** የሚከተሉትን አያያዦች በመጠቀም ዐረፍተ ነገሮች መስርቱ፡፡ |
| 10 | የጽህፈት ክሂል የለም፡፡ |

አባሪ 4

<u>*ሠንጠረዥ 8፡-*</u> *የክፍል ሁለት ጥያቄ መልሶች ትንተና*

| ተቁ | ለመ/ራን የቀረቡት የጽሑፍ መጠይቅ ጥያቄዎች | የተመለሱ መልሶችና የመላሾች ብዛት በቁጥርና በ% | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የተመለሱ መልሶች | የመላሾች ብዛት | | | | | |
| | | | ወንድ | | ሴት | | ድምር | |
| | | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 1 | በ8ኛ ክፍል አማርኛ መጽሐፍ የቀረቡት የንግግርና የጽህፈት ክሂል መልመጃዎች ዓላማን ከግብ ለማድረስ የሚያስችል ይመስልዎታል፡፡ | ሀ) ያስችላል | 5 | 100% | 4 | 100% | 9 | 100% |
| | | ለ) በከፍል ያስችላል | 0 | | 0 | | 0 | |
| | | ሐ) አያስችልም | 0 | | 0 | | 0 | |
| 2 | አልተሠራም፡፡ የጥያቄ 1 መልስ ሀ ነው፡፡ | | | | | | | |
| 3 | የጽህፈትና የንግግር ክሂሎች የይዘት መምረጫ መስፈርቶች ምን ያህል የጠበቁ ናቸው ብለው ያምናሉ? | ሀ) ተገቢነት | | | | | | |
| | | ከፍተኛ | 5 | 100% | 4 | 100% | 9 | 100% |
| | | ለ) አስፈላጊነት | | | | | | |
| | | ከፍተኛ | 5 | 100% | 4 | 100% | 9 | 100% |
| | | ሐ) ዘላቂነት | | | | | | |
| | | ከፍተኛ | 4 | 80% | 4 | 100% | 8 | 88.8% |
| | | መካከለኛ | 1 | 20% | | | 1 | 11.2% |
| | | መ) አስደሳችነት | | | | | | |
| | | ከፍተኛ | 3 | 60% | 2 | 50% | 5 | 55.5% |
| | | መካከለኛ | 2 | 40% | 2 | 50% | 4 | 44.5% |
| | | ሠ) ለመማር ያላቸው አመቺነት | | | | | | |
| | | ከፍተኛ | 4 | 80% | 3 | 75% | 7 | 77.7% |
| | | መካከለኛ | 1 | 20% | 1 | 25% | 2 | 22.3% |
| | | ረ) ወቅታዊነት | | | | | | |
| | | ከፍተኛ | 5 | 100% | 4 | 100% | 9 | 100% |

<table>
<tr><th rowspan="4">ተቁ</th><th rowspan="4">ለመ/ራን የቀረቡት የጽሑፍ መጠይቅ ጥያቄዎች</th><th colspan="7">የተመለሱ መልሶችና የመላሾች ብዛት በቁጥርና በ%</th></tr>
<tr><th rowspan="3">የተመለሱ መልሶች</th><th colspan="6">የመላሾች ብዛት</th></tr>
<tr><th colspan="2">ወንድ</th><th colspan="2">ሴት</th><th colspan="2">ድምር</th></tr>
<tr><th>በቁጥር</th><th>በ%</th><th>በቁጥር</th><th>በ%</th><th>በቁጥር</th><th>በ%</th></tr>
<tr><td rowspan="5">4</td><td rowspan="5">የጽህፈትና የንግግር መልመጃዎች የአደረጃጀት መስፈርቶች ምን ያህል የተጠበቁ ናቸው ብለው ያምናሉ?</td><td>ሀ) ተከታታይነት</td><td></td><td></td><td></td><td></td><td></td><td></td></tr>
<tr><td>ከፍተኛ</td><td>5</td><td>100%</td><td>4</td><td>100%</td><td>9</td><td>100%</td></tr>
<tr><td>ለ) ተለጣጣቂነት</td><td></td><td></td><td></td><td></td><td></td><td></td></tr>
<tr><td>ከፍተኛ</td><td>2</td><td>40%</td><td>3</td><td>75%</td><td>5</td><td>55.5%</td></tr>
<tr><td>መካከለኛ</td><td>3</td><td>60%</td><td>1</td><td>25%</td><td>4</td><td>44.6%</td></tr>
<tr><td rowspan="2">5</td><td rowspan="2">የጽህፈትና የንግግር ክሂል ይዘቶችና መልመጃዎች የተማሪውን የትምህርት ደረጃ የሚመጥኑ ይመስልዎታል?</td><td>ሀ) ይመጥናሉ</td><td>5</td><td>100%</td><td>4</td><td>100%</td><td>9</td><td>100%</td></tr>
<tr><td>ለ) አይመጥኑም</td><td></td><td></td><td></td><td></td><td></td><td></td></tr>
<tr><td>6</td><td>ጥያቄ 5 ስለተመለሰ አልተሠራም</td><td></td><td></td><td></td><td></td><td></td><td></td><td></td></tr>
<tr><td rowspan="2">7</td><td rowspan="2">አዲስ በተዘጋጀው የ8ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ለክሂሎች ተመጣጣኝ ትኩረት ተሰጥቷል?</td><td>ሀ) አዎን</td><td>1</td><td>20%</td><td>1</td><td>25%</td><td>2</td><td>22.3%</td></tr>
<tr><td>ለ) አልተሰጠም</td><td>4</td><td>80%</td><td>3</td><td>75%</td><td>7</td><td>77.7%</td></tr>
<tr><td>8</td><td>ለጥያቄ 7 መልስዎ ለ ከሆነ ምክንያትዎ ምንድነው?</td><td>ሀ) ንግግር ከፍተኛ ትኩረት ስላገኘ</td><td>4</td><td>100%</td><td>3</td><td>100%</td><td>7</td><td>100%</td></tr>
</table>